አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በ9ኛ ክፍል የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

በ

መዓዛ ደጀኔ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሰኔ 1999 ዓ.ም

በ9ኛ ክፍል የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ለአማርኛ ማስተማር (TEAM) ኤም.ኤ.ዲግሪ

በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

መዓዛ ደጀኔ

ሰኔ 1999 ዓ.ም

በ9ኛ ክፍል የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

በ

መዓዛ ደጀኔ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ	ፊርማ
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ
የውጭ ፈታኝ	ፊርማ

ማውጫ

አርእስት ገጽ

ምስጋና.....i

የሠንጠረዥ ማውጫ.....ii

የአባሪ ማውጫ.....iv

አጠቃሎ v

ምዕራፍ አንድ፡-መግቢያ.....1

1.1. የጥናቱ ዳራ.....1

1.2. የጥናቱ ዓላማ.....2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ.....3

1.4 የጥናቱ ገደብ.....3

1.5. የቁልፍ ቃላትና ምህጻረ ቃላት ፍቺ.....4

ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት.....5

2.1 ንባብ ምንድን ነው?.....6

2.2. አንብቦ መረዳት.....6

2.3. የንባብ ጠቀሜታ.....8

2.4. የንባብ ዓላማ.....8

2.5. የንባብ አይነቶች.....9

2.5.1 የአሰሳ ንባብ.....10

2.5.2. የገረፍታ ንባብ.....10

2.5.3. ጥልቅ ንባብ.....10

2.5.4. ሰፊ ንባብ.....10

2.6. የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ አቀራረቦች.....10

2.6.1. ክሂል-ተኮር አቀራረብ.....11

2.6.2. ስልት-ተኮር አቀራረብ.....11

2.7. የንባብ ንዑሳን ክሂሎች.....12

2.8. በመማሪያ ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ.....16

2.8.1. ልማዳዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ.....16

2.8.2. ዘመናዊ የንባብ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ.....17

2.8.2.1. ቅድመ-ንባብ ደረጃ.....18

2.8.2.2. ጊዜ-ንባብ ደረጃ.....19

2.8.2.3. ድህረ-ንባብ ደረጃ.....20

2.9. በንባብ ትምህርት ሂደት የመምህራን ድርሻ.....20

2.10. በንባብ ትምህርት ሂደት የተማሪዎች ድርሻ.....21
2.11. የንባብ ሂደት ሞዴሎች.....22
2.11.1 ከዝርዝር ወደ ጥቅል ንባብ ሂደት ሞዴል.....22
2.11.2 ከጥቅል ወደ ዝርዝር ንባብ ሂደት ሞዴል.....22
2.11.3 መስተጋብራዊ የንባብ ሂደት ሞዴል.....23
2.12. የቀድሞ ስራዎች ቅኝት.....23
ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ዘዴ.....26
3.1 የናሙና አመራረጥ ዘዴ.....26
3.1.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ.....26
3.1.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ.....26
3.1.3. የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ.....27
3.1.3.1. የተጠኝ መምህራን ናሙና አመራረጥ.....27
3.3.1.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ.....27
3.1.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች.....27
3.1.4.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ.....27
3.1.4.2. የቪዲዮ ቀረጻ.....28
3.1.4.3. የጽሑፍ መጠይቅ.....28
3.1.4.3.1. የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ.....28
3.1.4.3.2. የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ.....29
3.1.4.4. ቃለመጠይቅ.....29
ምዕራፍ አራት፡-የጥናቱ ትንተናና ውጤት.....30
4.1 የተጠኝ መምህራን ዳራዊ መግለጫ.....30
4.2. የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አጠቃላይ መረጃ.....31
4.3 የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ.....36
4.3.1 ቅድመ-ንባብ ደረጃ.....37
4.3.1.1. በቅድመ ንባብ ደረጃ መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት.....37
4.3.1.2. በቅድመ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት.....42
4.3.2. ጊዜ-ንባብ ደረጃ.....45
4.3.2.1. በጊዜ ንባብ ደረጃ መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት.....45
4.3.2.2. በጊዜ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች.....48
4.3.3. ድህረ-ንባብ ደረጃ.....48
4.3.3.1. በድህረ ንባብ ደረጃ መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት.....58

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS-LIBRARY

4.3.3.2. በድህረ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት.....60
4.3.4. ተጠኝ መምህራን ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ.....64
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት.....65
5.1. ማጠቃለያ.....65
5.2. አስተያየት.....66
ዋቢ ጽሑፎች.....69
ሙዳየ ቃላት.....73
አባሪዎች.....74

ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሞ ለዚህ ጊዜ ያደረሰኝ አምላክ ምስጋና ይግባው። ከጥናቱ ርዕስ መረጣ ጀምሮ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ደክመኝና ሰለቸኝ ሳይሉ ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍና ምክር በመለገስ ጥናታዊ ጽሑፉ አሁን የያዘውን ቅርፅ እንዲያገኝ ላደረጉት መምህራና አማካሪዬ ለአቶ ጌታቸው እንዳላማው (ረዳት ፕሮፌሰር) ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ይህን የትምህርት ዕድል ለሰጠኝ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ እንዲሁም ለጥናቱ የሚሆን ገንዘብ ለፈቀደልኝ በአ.አ.ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍለ-ትምህርት ምስጋና አቀርባለሁ።

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የቪዲዮ ቀረጻው የተሳካ እንዲሆን በገንዘብ የማይተመን ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአቶ አለማየሁ ነጋሽ፣ ቀረጻውን ወደ ካሴት በመገልበጥ ለተባበሩኝ ለአቶ ዳዊት ባሳዝነው፣ መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ለቦሌ፣ ድላችንና ጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራንና ሠራተኞች እንዲሁም የጽሑፍ መረጃ ለሰጡኝ መምህሬ፣ መምህርት መሰሉ መንግስቱ ምስጋና አቀርባለሁ።

ትምህርቴን እስካጠናቅቅ በገንዘብና በማቴሪያል እገዛ ከጎኔ ለነበርከው ባለቤቴ አቶ ወንድወሰን ብርሃኑ እንዲሁም ጊዜ በማጣት ፍቅርና እንክብካቤዬን ላጓደልኩባችሁ ልጆቼ ጽዮን ወንድወሰንና ቤዛዊት ወንድወሰን ለትዕግስታችሁ ብድር መላሽ ያድርገኝ።

የጽሑፉን ረቂቅ በማንበብና በማረም፣ አስፈላጊውን ማበረታቻ በማድረግ ለተከታተሉልኝ ወንድሜ አቶ ብርሃነ መስቀል ደጀኔ፣ ከፍተኛ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ በመስጠት ከጎኔ ለነበርከው ወንድሜ አቶ ፈለቀ ደጀኔ እና ማበረታቻ ላደረግክልኝ ወንድሜ አቶ አክሊለብርሃን ደጀኔ በሀሳብ ከኔ ጋር ለነበራችሁት እህቶቼ ወ/ሮ ፍጽምት ደጀኔ፣ ወ/ሮ የምስራች ደጀኔ፣ ወ/ት ዘነበች ደጀኔ እና ወ/ት ሂሩት ተፈረደኝ ጥሩ ለተመኛችሁልኝ ዘመዶቼና ጓደኞቼ በሙሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

በትምህርት ላይ በነበርኩበት ጊዜ ለልጆቼ ፍቅርን በመስጠት ከጎኔ ለነበርሽው እናቴ እማሆይ ጽጌ ኢሳያስ፣ የልጄን ትምህርት ለተከታተልሽልኝ ተማሪ ፍሬህይወት ፍሰሐ፣ ልጆቼን ስትንከባከቢልኝ ለነበርሽው ወ/ት በቀለች ሙሉነህ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

በመጨረሻም ይህን ጽሑፍ በትግዕስት በኮምፒውተር ጽፈው ለንባብ እንዲበቃ ላደረጉት ወ/ት ጤናዬ ታደሰ እና ትዝታ ከበደ ምስጋና አቀርባለሁ።

የሠንጠረጉች ዝርዝር

ሠንጠረዥ ገጽ

አንድ፡- የተጠኝ መምህራን ዳራ ከጸታ፣ ከዕድሜና ከትምህርት ደረጃ አንጻር----------30

ሁለት፡-የተጠኝ ተማሪዎች ዳራ ከጸታ፣ ከዕድሜ አንጻር----------31

ሶስት፡- ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ----------31

አራት፡- ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ----------32

አምስት፡- የተማሪዎችን ንባብ የመማር ፍላጎት በተመለከተ
ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ----------32

ስድስት፡- የተማሪዎችን ንባብ የመማር ፍላጎት በተመለከተ
ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ----------33

ሰባት፡- የማስተማሪያ ጽሑፍን በተመለከተ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ----------34

ስምንት፡-የማስተማሪያ ጽሑፍን በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ----------35

ዘጠኝ፡- መልመጃዎችን በተመለከተ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ----------36

አስር፡- የንባብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ክክፍል ምልከታ የተገኘ ----------37

አስራአንድ፡- የንባብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን
የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ----------38

አስራ ሁለት፡-የንባብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ
መጠይቅ የተገኘ----------40

አስራ ሶስት፡- በቅድመ ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከክፍልምልከታ
የተገኘ----------42

አስራ አራት፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኘ ----------43

አስራ አምስት፡-ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኘ----------44

አስራ ስድስት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል
ምልከታው የተገኘ ----------45

አስራ ሰባት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራትን ከመምህራን የጽሑፍ
መጠይቅ የተገኘ----------46

አስራ ስምንት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከተማሪዎች የጽሑፍ
መጠይቅ የተገኘ ----------47

አስራ ዘጠኝ፡- ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ----------49
ሃያ፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ስለሚሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን
የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ----------52
ሃያ አንድ፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ስለሚሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኘ----------55
ሃያ ሁለት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በተመለከተ በክፍል
ምልከታ የተገኘ----------58
ሃያ ሶስት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በተመለከተ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኘ----------59
ሃያ አራት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኘ----------59
ሃያ አምስት፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከክፍል
ምልከታው የተገኘ----------60
ሃያ ስድስት፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን
የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ----------61
ሃያ ስባት፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎት
የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ----------62

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የአባሪዎች ማውጫ

አባሪ ገጽ

1ሀ. ከቪዲዮ ቀረጻ ወደ ጽሑፍ የተገለበጠ ምልከታ ኮድ 01.....74

1ለ. ከቪዲዮ ቀረጻ ወደ ጽሑፍ የተገለበጠ ምልከታ ኮድ 02.....78

2ሐ. ከቪዲዮ ቀረጻ ወደ ጽሑፍ የተገለበጠ ምልከታ ኮድ 03.....84

1መ. ከቪዲዮ ቀረጻ ወደ ጽሑፍ የተገለበጠ ምልከታ ኮድ 04.....88

1ሠ. ከቪዲዮ ቀረጻ ወደ ጽሑፍ የተገለበጠ ምልከታ ኮድ 05.....90

1ረ. ከቪዲዮ ቀረጻ ወደ ጽሑፍ የተገለበጠ ምልከታ ኮድ 06.....99

2. መከታተያ ቅጽ (Checklist).....105

3. የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ.....106

4. የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ.....110

5. ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች.....113

አጠቃሎ

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ንባብ ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በንባብ ትምህርት ሂደት ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸውን ትኩረት መፈተሽ ነው። ዝርዝር አላማውም ለየትኞቹ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ይሰጣል? የጥናቱ ተተኳሪዎች መምህራን ናቸው። ስለዚህ መምህራንስ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ነው። በመሆኑም እነዚህ የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ በጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በቪዲዮ ቀረጻ የታገዘ ምልከታ፣ የመምህራንና የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም ቃለመጠይቅ መጠይቅ ናቸው።

ጥናቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት የተካሄደ ሲሆን ተጠኝ መምህራን ሲያስተምሩ አንድ ነፃ ምልከታና ሁለት ጊዜ በቪዲዩ ቀረጻ የታገዘ ምልከታ ተከናውኗል። ከዚህም በተጨማሪ መምህራንና ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል። ለመምህራንና ለክፍለ ትምህርት ሀላፊዎችም ቃለ መጠይቅ ቀርቧል። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖ የተገኘው ውጤት የሚከተለው ነው።

ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በተጠኝ መምህራኑ የተሰጣቸው ትኩረት አነስተኛ ነበር። ተጠኝ መምህራኑም ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን የሚያስተምሩት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባሉት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ላይ ብቻ የተወሰነ ሆኖ ታይቷል። በንባብ ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎች ቅድመ-ንባብ ደረጃ በተሻለ ሁኔታ የተተገበረ ሲሆን፣ በጊዜ-ንባብ ደረጃ ያሉ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በአብዛኛው ተዘንግተው ታይተዋል። ለምሳሌ የዝምታ ንባብ፣ የአሰሳ ንባብ፣ የገረፍታ ንባብ ባለመተግበራቸው የንባብ ትምህርቱ ይሰጥ የነበረው በተማሪዎች ወይም በመምህራን እየተነበበ ነበር። በድህረ-ንባብ ደረጃ መዳበር ካለባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ መረዳት ንዑስ ክሂል እና የንባብ ትምህርት ከሌሎች ጋር ማጣመር ንዑስ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን የቀረበውን ምንባብ መገምገም ደግሞ አነስተኛ ትኩረት እንደተሰጠው ጥናቱ አመላክቷል። መምህራኑም ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በመጨረሻም የታዩትን ድክመቶች ለማሻሻል ሊያግዙ ይችላሉ የተባሉ የመፍትሔ ሐሳቦችን በመሰንዘር ጥናቱ ተቋጭቷል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ንባብ ነው። ንባብ የመቀበያ ክሂል (Reseptive skill) በመባል ይታወቃል። ስለ ንባብ ምንነት በርካታ ፀሐፍት የራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል። ከእነዚህ መካከል Davies (1995:1) ሲገልጹ ንባብ ግላዊና የአእምሮ ተግባር ነው ሲሉ May (1990:10) በበኩላቸው ንባብ ከተጻፉ ምልክቶች ውስጥ ፍቺን ማግኘት ወይም በፅሁፍ የቀረበን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው በማለት ገልጸውታል። ከዚህ በተጨማሪ Grellet (1981:3)፣ Nuttal (1982:2)፣ Simth (1985:102)፣ Wallace (1992:4)፣ ሲገልጹ ንባብ አንድ ጽሁፍ በውስጡ የያዘውን መረጃ በበቂ ሁኔታ መገንዘብ ነው። ይህም ከቀረበው አነስተኛ ጽሁፍ ግንኙነት መፍጠር ነው። ይህን ለመፍጠር ደግሞ የአንባቢውን የመገንዘብ ችሎታ ይጠይቃል። ይህም የሚያሳየው ንባብ ግላዊና አእምሮአዊ ተግባር መሆኑን ነው። በተጨማሪም አለም (1995) Alderson et.al. (1984:1)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት "የንባብን ምንነት በቀላሉ መመለስ የዋህነት ነው፤ ንባብ በራሱ ውስብስብ የሆነ አእምሮታዊ ሂደት ነው"።

ከላይ የተገለጸው የንባብ ምንነት በተመለከተ ምሁራን የሰነዘሩትን ሃሳብ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የንባብ ትምህርትን በክፍል ውስጥ በማስተማር ረገድ ያለውን ችግር ለመፍታት Celce-Murcia (1991:202) የራሳቸውን ንድፍ ሀሳባዊ ትንተና ሰጥተዋል። የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ በዘመናዊ የማስተማር ዘዴ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ነው ለንባብ ትምህርት ለውጥ የተሻሻሉ የማስተማር ዘዴዎች እጅጉን አስፈላጊ ናቸው በማለት Atkins et-al. (1996:55) አበክረው የገለጹት።

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የንባብን ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አሉ።እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በጣም ጠቃሚና ተማሪዎች ችግር ፈቺዎች እንዲሆኑ የሚያግዙ ናቸው። በንባብ ትምህርት ጊዜ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጠው ትኩረት የንባብ ትምህርት የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን እገዛ ይሰጣል (Hosenfel፣ 1979 እና Rivers፣ 1987)። በንባብ ትምህርት ሂደት የመምህሩ ተግባር ተማሪዎች ለንባብ ማስተማሪያ የተዘጋጁ ጽሑፎችን አንብበው የተለያዩ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ መርዳት ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተለያዩ ፀሐፍት የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንዳንዶቹ እስከ ሰላሳ ስድስት ይደርሳሉ ሲሉ፣ አንዳንዶቹ ምሁራን ለምሳሌ (Grellet 1981:4-5) እና Munby (1978፡ 256) ደግሞ ወደ አስራዘጠኝ ያደርሷቸዋል።) ከድረ ገጽ(2007) የተገኘው መረጃ ደግሞ አስራ ሁለት እንደሚደርሱ ይጠቁማል። ከዚህ በተጨማሪ Greenall and Swan (1986፣2) ንባብን በተሳካ መልኩ ለማካሄድ የሚያስችሉ አስራ ሁለት ያህል ንዑሳን ክሂሎችን በመዘርዘር አስፍረዋል።

በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጠው ትኩረት ምን ይመስላል? የሚለውን በዝርዝር ማየት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ነው። የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የንባብ ትምህርት የዳበረ እንዲሆን ተማሪዎች ንባብን ከህይወታቸው ጋር በማያያዝ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል የመምህራን ድርሻ ከፍተኛ መሆን አለበት። በዚህ ረገድ ለተማሪዎች የሚመረጡ የንባብ ማስተማሪያ ጽሁፎች ተማሪዎችን ለንባብ የሚያነሳሱ መሆን ይገባቸዋል። ይህም የንባብ ትምህርቱን የተሳካ እንዲሆን ያደርገዋል። መምህራንም ራሳቸውን ከዘመናዊ የንባብ ትምህርት አቀራረቦች ጋር በማዋሀድ በዘርፉ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል (Atkins et.al. 1996:56) ።

ከዚህ በመነሳት በንባብ ትምህርት ዙሪያ መምህራን "ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጧቸው ትኩረት" በሚል ርእስ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ መነሻ የሆነኝ በአንዳንድ የጥናት ጽሑፎች ውስጥ የተሰጡት ጥቆማዎች፣ ለሴሚናር ኮርስ ማሟያ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ትግበራን ለማጥናት በሞከርኩበት ጊዜ የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ያስተዋልኩት የንባብ ትምህርት አቀራረብ ችግር ነው። ከችግሮቹ መካከል የንባብ ትምህርት በተለምዷዊ (በጮክታ ንባብ) ሁኔታ የሚሰጥ መሆኑ፣በንባብ ትምህርት ጊዜ የንባብ አይነቶችን እንደአስፈላጊነታቸው አለመጠቀማቸው፣ የተማሪዎች ተሳትፎ ውስን መሆኑ፣ የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

1.2. የጥናቱ አላማ

በአዲስ አበባ መስተዳድር በመንግሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ክሂል ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል? መምህራንስ ያላቸው ግንዛቤ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጉዳዮች መመርመር የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶ ፍተሻ የሚደረገው ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በተመለከተ ነው። ይህ ጥናት በሂደት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል።

1. በንባብ ትምህርት ወቅት ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ምን ያህል ነው?
2. በንባብ በትምህርት ወቅት ለየትኞቹ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ይሰጣል?
3. መምህራንስ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል ?

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ትምህርቱ መሰረት የሚያደርገው በተዘጋጀው የማስተማሪያ መፅሐፍ ላይ ነው። መፅሐፉ ላይ የቀረቡ የንባብ ትምህርት ይዘቶች ደግሞ የሚተገበሩት በመምህሩ ነው። መምህሩ የቀረቡለትን የትምህርት ይዘቶች የሚያቀርብበት የማስተማር ዘዴ የታሰበውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያስችለዋል። ስለዚህ ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል።

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ክሂል ትምህርት ሲሰጡ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን መሆን እንዳለበት ጥቆማ ይሰጣል።
2. በቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት ወሳኝ ሚና ያላቸው የመማሪያ መጻሕፍት ንባብን ለማስተማር ምን ሁኔታን ይዘው መገኘት እንዳለባቸው ይህ ጥናት ለመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የማስተማሪያ መጻሕፍትን ለማሻሻልም ሆነ ለማዘጋጀት የበኩሉን መረጃ ይሰጣል ።
3. ይህ ጥናት ወደፊት በንባብ ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ለሚነሳሱ ጥናት አቅራቢዎች መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን በመጠቆም ጠቃሚታ ይኖረዋል ።
4. የመምህራን ስልጠና ለሚሰጡ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ተቋማት ሀሳብ ይሰጣል።

1.4. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚገኙ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተከናወነ ነው። ጥናቱ በነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚወሰነው የጊዜና የገንዘብ አቅም ውስንነት በመኖሩ ነው። ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገው በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚገኙ ጥቁር አንበሳ፣ ቦሌ አጠቃላይ እና ድላችን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ የክፍል ደረጃ ናሙናነት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል? የሚለውን መፈተሽ ብቻ ይሆናል ጥናቱ መምህራን ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡትን ትኩረት ከመፈተሽ ሌላ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ፣ የተማሪዎች ንባብን የማነበብ ተነሳሽነትና የመሳሰሉት ላይ ፍተሻ አያደርግም።

1.5. የቁልፍ ቃላትና ምህጻረ ቃላት ፍቺ

1. ተራ ቁ.= የሚወክለው በምልከታ መከታተያ ቅጹና በመጠይቆቹ ላይ ይዞ የነበረውን ቁጥር ነው።
2. መለያ ቁጥር= ለተጠኝ መምህራኑ የተሰጠ መለያ ቁጥር ነው።
3. "መ"= መምህር
4. "ተ"= ተማሪ



ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1. ንባብ ምንድን ነው?

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ንባብ ነው። ይህም ክሂል የመቀበያ ክሂል (Receptive Skill) በመባል ይታወቃል። ክሂሉም እንደ ጽህፈት ክሂል በትምህርት የሚቀሰም ልምድ ነው። ንባብን በተመለከተ በርካታ ጸሐፍት ብያኔ ለመስጠት ሞክረዋል። ቀጥሎ ባሉት አንቀጾች እነዚህ ጸሐፍት የሰጡትን ብያኔዎች በዝርዝር በመቃኘት ስለንባብ ምንነት ለመግለጽ ይሞክራል።

በንባብ ዙሪያ ምርምር ካደረጉት ምሁራን መካከል Smith (1985:102) ሲገልጹ "ንባብ ለሚለው ቃል በቀላሉ ብያኔ መስጠት አይቻልም፤ ምክንያቱም ለአንድ ቃል ፍቺ ለመስጠት አውድ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ለንባብም ፍቺ ለመስጠት የምንነጋገርበት አውድ ይወስነዋል። በዚህም መሠረት ከትምህርት ጋር በተያያዘ ከሆነ ፍቺው ከአንድ ውህድ አሀድ (text) መረጃን ለይቶ ማውጣት ነው ብለዋል።" በተመሳሳይ መልኩ አለም (1995) Alelderson et.al.(1984:1)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት «ንባብ ምንድነው የሚለውን ጥያቄ በቀላሉ ለመመለስ መሞከር የዋህነት ነው።»

ይሁንና ምሁራን ስለንባብ ምንነት መግለጽ ቀላል አለመሆኑን ቢገልጹም የራሳቸውን ሀሳብ መሰንዘራቸው አልቀረም። ለምሳሌ Grellet (1981:3) "አንድን ጽሑፍ ማንበብ ማለት በውስጡ የያዘውን መረጃ በበቂ ሁኔታ መገንዘብ ነው። በቂ የሆነ መረጃ ለማግኘት ደግሞ የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን እንጠቀማለን ለምሳሌ ማስታወቂያ ለማንበብና በአንድ መጽሔት ላይ የወጣን የሳይንስ ግኝት ለማንበብ አንድ ዓይነት ስልት አንጠቀምም፤" በማለት ይገልጻሉ።

May (1990:10) እንዲሁ ንባብ በጽሁፍ የቀረበን ሐሳብ የመረዳት ሂደት ነው። በዚህ ሂደትም አንባቢው በጽሁፍ ያገኘውን ሃሳብ በመከተል የራሱን ግምት በመስጠት ጽሁፉን ለመገንዘብ የሚያከናውነው ተግባር ነው፤ በማለት ያስረዳሉ። William (1990:2) በተመሳሳይ መልኩ ስለንባብ ሲገልጹ ንባብ የተጻፈን ጽሁፍ የመገንዘብ ሂደት ነው። ነገር ግን አንድን ንባብ ድምጽ እያሰሙ ወይም በዝምታ መልዕክቱን ሳይረዱ ማነብነብ ንባብ አይባልም ይላሉ።

Wallace (1992:4) እና Weaver (1990:201) በበኩላቸው ከላይ የቀረበውን የንባብ ምንነት በማጠናከር እንደሚከተለው ይገልጻሉ። ንባብ የቀረበን አነስተኛ ጽሁፍ በመተርጎም ከጸሀፊው ጋር ግንኙነትን መፍጠር ነው። ስለዚህም የጸሀፊውን ሐሳብ ለመረዳት አንባቢው የመገንዘብ ችሎታ

ሊኖረው ይገባል። በተመሳሳይ መልኩ ንባብ በጽሁፍ የቀረበን መልዕክት ለመረዳት አንባቢው በግሉ የሚያከናውነው ተግባር ነው። ይህም የአንባቢውንና ያሚነበበውን ጽሁፍ መስተጋብር የሚፈልግ ነው። ለዚህም ነው ንባብ አእምሯዊና ግላዊ ተግባር ነው ለማለት የሚቻለው። መሰሉ (1994) በበኩላቸው ሲያስረዱ ማንበብ በጽሁፍ የቀረበን መልዕክት ለመረዳት አንባቢው በግሉ የሚያከናውነው ተግባር ነው። አንድ አንባቢ ንባብን የሚያከናውነው የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ነው። በመሆኑም የአነባበቡ ሁኔታ እንደሚፈለገው የመረጃ አይነትና ሁኔታ ይለያያል።

በተጨማሪም አለም (1995:5) Nuttal (1996:2)ን ዋቢ በማድረግ የንባብን ምንነትን የሚገልጹት በሦስት ደረጃዎች ነው።

በዚህም መሰረት፡-

ሀ. መነጠል፣ መለየት፣ መቁጠር፣(ለፊደል ወይም ለምልክት)

ለ. ከአንደበት ማፍለቅ፣ንበት፣ የድምጽ አፈላለቅ፣ መናገር ወዘተ ...

ሐ. መረዳት፣ መገንዘብ፣ ትርጉም መጨበጥ፣ ስሜት መከተል ወዘተ...

እነዚህ ከለይ የተዘረዘሩት በንባብ ትምህርት ሂደት ውስጥ የሚታለፍባቸው ደረጃዎች ናቸው። ይህም ሁኔታ ንባብ በተለያየ መንገድ ሊከናወን እንደሚችል ያመላክታል።

በአጠቃላይ ከላይ በምሁራኑ እንደተገለጸው ለንባብ ቀጥተኛ ፍቺ መስጠት ቀላል አይደለም። ከትምህርት ጋር በማያያዝ ፍቺ ለመስጠት ሲሞከር ግን ንባብ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ መረጃን ለይቶ ለማውጣት የሚከናወን አእምሮአዊና ግላዊ ድርጊት ነው። ይህም በመሆኑ አንድ አንባቢ ሊያነብ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ሙሉ በሙሉ ሀሳቡን በሚያገኘው ጽሁፍ ላይ ማድረግ አለበት። ለዚህም ነው ንባብ ማነብነብ አይደለም ተብሎ የተገለጸው።

2.2. አንብቦ መረዳት

አንብቦ መረዳት ከቀረበ ጽሁፍ ውስጥ ያለውን ሀሳብ መገንዘብ ነው (Williams 1993፡15፣ Greenwood 1981፡89)። አንብቦ መረዳትን በተመለከተ ምሁራን የራሳቸውን ንድፈ ሀሳባዊ ትንተና ሰጥተዋል። ከነዚህም መካከል Cooper (1997፡11) አንብቦ መረዳት በጽሁፍ ውስጥ የሚገኘውን ፍንጭ ሰጪ ጠቋሚዎችን በመጠቀም አንባቢው የራሱን ግንዛቤ የሚያዳብርበት ሂደት ነው በማለት ይገልጹታል።

በሌላ በኩል Carrell and Eskey (1988፡70) በበኩላቸው አንብቦ መረዳትን የሚገልጹት አዕምሮአዊ ምስል (Schemata) ጋር በማያያዝ ነው። አንድን ጽሁፍ አንብቦ መረዳት ማለት በጽሁፍ ውስጥ

የቀረበውን ሀሳብ በአእምሮ ውስጥ ቀድሞ ከነበረው ምስል ጋር በማቀናጀት ትርጉም የመስጠት ሂደት ነው። አዕምሮአዊ ምስል ትወራ እንደሚያስረዳው ለንባብ የሚቀርበው ጽሁፍ ለአንባቢው ፍንጭ ሰጪ ነው እንጂ በራሱ ትርጉም ሰጪ አይደለም።

በተጨማሪም Lange (1981:444) የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሰው እንደገለጹት አዕምሮአዊ ምስል ትወራ አእምሮ የሚያመነጨው እውቀት መነሻው አሁን የሚቀርበው ሀሳብ ነው። ይህም በአንብቦ መረዳት ጋር በተያያዘ ሲገለጽ አንድ አንባቢ ጽሁፉን በሚያነብበት ጊዜ የሚገነዘበው አጠቃላይ ሀሳብ የሚመነጨው አእምሮ ቀድሞ የነበረውን ምስል አሁን ከሚነበበው ጋር አያይዞ ግምት በመስጠት ግምቱ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ወይም በማስተካከል የመገንዘቢያ መንገድ ነው። አዕምሮአዊ ምስል ትወራ በአንባቢውና በቀረበው ጽሁፍ መካከል በሚፈጠረው ግንኙነት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህም ሂደት አንብቦ የመረዳት ሂደት ነው።

በምሁራኑ እንደተገለጸው አንብቦ መረዳት ማለት ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኘውን ፍንጭ በመጠቀም አዕምሮአዊ ምስል ጋር አዋህዶ ትርጉም የመስጠት ሂደት ነው። ትርጉም ለመስጠትም አንባቢው የቀደመ እውቀት ሊኖረው ይገባል። ይህን የቀደመ ዕውቀት በመጠቀም አሁን ከሚያነበው ጋር አያይዞ ንባብን ለመገንዘብ የሚያደርገው ጥረት ነው ማለት ይቻላል።

አንብቦ መረዳት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ ያለውን ሀሳብ የመገንዘብ ሂደት መሆኑ በምሁራን ተገልጿል። አንብቦ መረዳት በውስጡ የሚይዛቸው ችሎታዎች አሉ። ከዚህ ቀጥሎ Heaton (1975:103)፣ Grellet (1981:4)፣ Greenwood (1981:89)፣ Cooper (1997:11) ባቀረቧቸው ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ቀጥሎ ያሉት አንብቦ የመረዳት ችሎታዎች ተዘርዝረዋል።

1. የቃላትን ፍቺ መገንዘብ፡- በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ቃላት መሠረት ናቸው። በጽሁፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ ለመስጠት በሁለት መንገድ መጠቀም ይቻላል። ይህም ቀጥተኛ ፍቺና ከአውዱ በመረዳት ነው።
2. ሰዋስዋዊ አያያዦችን አንብቦ መረዳት፡- አንድ አንባቢ በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን አያያዦች ትርጉም መገንዘብ የጽሁፉን ይዘት ለመረዳት ከፍተኛ እገዛ ያደርግለታል።
3. በጽሁፉ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ወይም የሰፈሩ መልዕክቶችን መረዳት፡- በዕሁፉ ውስጥ ሁሉም ሀሳቦች በቀላሉ በግልጽ ሰፍረው ላይገኙ ይችላሉ። ስለዚህ አንባቢው በተዘዋዋሪ የቀረቡ ይዘቶች ቢኖሩ በንባቡ ሂደት በመመርመር ሊደርስበት ይገባል።
4. የጽሁፉን ተዋረዳዊ የሀሳብ አደረጃጀት መረዳት፡- በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ለዐረፍተ ነገሮች በተናጠል ትርጉም በመስጠት መልዕክቱን መገንዘብ አያስችልም። ስለዚህ አንዱ ዐረፍተ

ነገር ከቀድሞውና ከሚከተለው ጋር ያለውን ግንኙነት በመመርመር መረዳት አስፈላጊ ነው።

5. **የጽሁፉን መልዕክት ከዳራዊ እውቀት ጋር (background knowledge) በማቀናጀት የመረዳት ችሎታ፡-** በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚቀርቡ ሀሳቦች የቀደመ እውቀት የሚጠይቁ ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ በጽሁፉ ውስጥ ከቀረቡት ፍንጭ ሰጭ ጉዳዮች በመነሳት ከዳራዊ እውቀት ጋር በማጣመር ለመገንዘብ መሞከር ትልቅ እገዛ ይሰጣል።

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ችሎታዎች መዳበር አንድን ጽሁፍ በሚገባ አንብቦ ለመረዳት የሚያግዙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

2.3. የንባብ ጠቀሜታ

ንባብ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ይህም ሲባል አንድ ሰው አዲስ እውቀት ለማግኘት ወይም የነበረውን እወቀት የበለጠ ለማዳበር ንባብን ይጠቀምበታል። ከዚህም በተጨማሪ በአጠቃላይ በአካባቢው ያለውን ነገርና የሚኖርባትን ዓለም ጠልቆ ለመረዳት ንባብ አይነተኛ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል (Davies 1995:5)።

Abersold and Field (1997:28) ከላይ የቀረበውን የ Davies (1995) ሀሳብ በማጠናከር ሲገልጹ ንባብ ሁለተኛ ቋንቋን ለሚማሩ ተማሪዎች የተለያዩ የባህል ልዩነቶችን ለመገንዘብ ያስችላቸዋል። እንዲሁም ከራሳቸው ውጭ ያለውን ባህል ለመገንዘብ ንባብ ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣል። መሰሉ (1994)ም እንደገለጹት እንዲሁ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ጽሁፎችን በተለያዩ የአነባበብ ዘዴዎች በመጠቀም በሚያነቡበት ጊዜ የቋንቋ ችሎታቸውን ከማዳበር አልፈው ለሌሎቹም ክሂሎች መሠረት መጣል እና በራሳቸው የመተማመን ችሎታቸውን ለማዳበር ንባብ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

2.4. የንባብ ዓላማ

ንባብ በሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ አንድ የሕይወት ገጽታ ነው። በተለይ በተማረ ማህበረሰብ ውስጥ ካለንባብ የሚከናወን ድርጊት አይኖርም። ንባብ በሚነበብበት ጊዜ እያንዳንዱ የንባብ ተግባር የራሱ የሆነ አላማ አለው። Wallace (1992:6-7) እና Harmer (1991:182) ስለ ንባብ ዓላማ ሲገልጹ፣ በሶስት ዋና ክፍሎች ይፈርጇቸዋል። እነዚህም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

ሀ. ንባብ፡-ለመጠንቀቅ

ንባብ የአካባቢያችንን ሁኔታ ለመገንዘብ ትልቅ እገዛ ያደርጋል። በዚህ መሠረት በንባብ አማካኝነት የሚተላለፉ መልዕክቶች በመገንዘብ ራሳችንን ከአደጋ ለመታደግ እንችላለን። ለምሳሌ በንባብ የሚተላለፉ መልዕክቶች በሰዎች ዘንድ የሞትና የመኖር ምርጫ ውስጥ የሚያስገቡ ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህም መካከል "በዚህ ማለፍ ክልክል ነው"፣ "ለሴቶች ብቻ"፣ "ለወንዶች ብቻ"፣ "አደገኛ"፣ "መውጫ"፣ "መግቢያ" የሚሉ ጽሁፎች ከሰው ልጅ ህልውና ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው፤ ለዚህም ነው ንባብ ለመጠንቀቅ የሚባለው።

ለ. ንባብ፡- ለመደሰትና ለመዝናናት

ከንባብ አላማዎች አንዱ ለመደሰትና ለመዝናናት ነው። ንባብን ለመጠንቀቅ ስናነብ ለሁኔታዎች (ቁም፣ማለፍ ክልክል ነው) ወዲያውኑ ምላሽ የሚሰጥባቸው ነገሮች ላይ የሚያተኩር ነው።ንባብን ለመደሰትና ለመዝናናት ስናውለው የራሱ ዓላማ አለው። ከአላማዎቹም መካከል ስነጽሑፍን ለማጣጣም ማንበብ አንዱ ነው። ከዚህም በላይ አንባቢ የሆኑ ወጣቶችን ለማፍራት ንባብን ለመዝናናት በማንበብ እንዲለማመዱ ማድረግ ይቻላል።በተጨማሪም ንባብን ለመደሰትና ለመዝናናት አላማ ሲያውሉትም በማንኛውም ቋንቋ ያላቸውን ችሎታ በማዳበር ጥሩ ብቃት እንዲኖራቸው ያደርጋል።ጥሩ ብቃት ያለው አንባቢ ደግሞ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ በቀላሉ ንባብን ለማከናወን ይችላል።

ሐ. ንባብ፡- አዲስ ነገር ለማወቅ (እውቀትን ለማስፋት)

የንባብ አላማዎች ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል አንዱ አዲስ ነገርን ለማወቅ ወይም ለመማር የምናከናውነው ነው። ንባብ አካባቢያችንን ተገንዝበን ራሳችንን ከአደጋ ለመጠበቅ፣ ለመደሰትና ለመዝናናት እንደምናነብ ሁሉ አዲስ ነገር ለማወቅም እናነባለን። ይህም ስለ አለም ያለን እውቀት እንዲዳብር እገዛ ያደርጋል። ከዚህም በተጨማሪ በንባብ አማካኝነት አዳዲስ የትምህርት ይዘቶችን ለመረዳት ንባብ ሊካሄድ ይችላል።

2.5. የንባብ አይነቶች

ንባብ የሚነበብበት አላማ የተለያየ እንደመሆኑ ሁሉ ሲነበብም የተለያዩ የንባብ አይነቶችን በመጠቀም ነው። እነዚህም የተለያዩ የንባብ አይነቶች የአሰሳ ንባብ፣ የገረፍታ ንባብ፣ ጥልቅ ንባብ እና ሰፊ ንባብ ናቸው (Nuttal 1982:23፣ Williams 1984:100)። ስለንባብ አይነቶች ምሁራኑ ያሰፈሩትን ፅንስ ሀሳብ ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል።

2.5.1 የአሰሳ ንባብ

የአሰሳ ንባብ የፍጥነት ንባብ ሲሆን፣ ከአንድ ጽሁፍ የተወሰኑ መረጃዎችን ለማግኘት የሚከናወን ንባብ ነው። የአሰሳ ንባብ አይንን በፍጥነት በማንቀሳቀስ የሚፈለገውን ነጥብ ለማውጣት ይካሄዳል፡ ስለዚህ በዚህ የንባብ አይነት በጽሁፍ ውስጥ እንደ ስም፣ ዓመተ ምህረት፣ ቁጥሮች የመሳሰሉትን መረጃዎችን በፍጥነት ለማግኘት ሊከናወን ይችላል።

2.5.2. የገረፍታ ንባብ

የገረፍታ ንባብ እንደ አሰሳ ንባብ ሁሉ በፍጥነት የሚከናወን ንባብ ሲሆን የአንባቢው ዓላማ የጽሁፉን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳት ነው። በዚህ የንባብ ሂደትም ትኩረት የሚደረገው በጽሁፉ ውስጥ የየአንቀጹን መንደርደሪያ ዐረፍተ ነገር ለይቶ በማውጣት የጽሁፉን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ነው። በመሆኑም የጽሁፉ አጠቃላይ ሀሳብ ከተገኘ በኋላ የንባቡ ሂደት ሊገታ ይችላል።

2.5.3. ጥልቅ ንባብ

ጥልቅ ንባብ አንድን ፅሑፍ በትኩረትና በጥንቃቄ የምናነብበት መንገድ ነው። ስለዚህም የጥልቅ ንባብ ትኩረቱ የምንባቡን ዋና ሀሳብ በዝርዝርና በጥልቀት መመርመር ነው። በዚህም ሂደት አንባቢው ጸሐፊው ትኩረት የሰጠበትን ሁኔታና ለማስተላለፍ የፈለገውን ሀሳብ ለይቶ ማውጣት ይጠበቅበታል። ተፈላጊውን ሀሳብ ለማግኘት ደግሞ በዝርዝር ማንበብ የግድ ይላል።

2.5.4. ሰፊ ንባብ

ይህ የንባብ አይነት ከአሰሳ፣ ከገረፍታ እና ጥልቅ የንባብ አይነቶች የሚለየው ሰፊ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ ነው። በዚህ የንባብ አይነት ሰፋ ያሉ ለምሳሌ እንደ ረጅም ልብወለድ የመሳሰሉ ጽሁፎች የሚነበቡበት ሁኔታ ነው። ረዘም ያሉ ጽሁፎች በሚነበቡበት ጊዜ ደግሞ የንባብ ችሎታ እየዳበረ ይሄዳል።

ከላይ የተገለጹትን አራቱን የንባብ አይነቶች እንደአስፈላጊነታቸው መጠቀም ይችላል። የንባብ አይነቶቹም እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው። አንድ አንባቢ ከአላማው በመነሳት አንዱን የንባብ አይነት ነጥሎ መጠቀም ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ እንደጽሁፉ አይነትና ባህሪ የንባብ አይነቱ የሚወሰንበት አጋጣሚም አለ። ለምሳሌ ያህል አንድ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ ለማንበብ መጠቀም የሚቻለው የአሰሳ ንባብ ነው፤ ምክንያቱም ተፈላጊውን መረጃ ለማውጣት ብቻ የምናከናውነው ንባብ በመሆኑ ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ከአራቱ የንባብ አይነቶች መካከል አንዱን ለመምረጥና ለመጠቀም የሚያስችለው እንደንባቡ አላማ ወይም እንደጽሁፉ አይነትና ባህሪ መሆኑን ነው።

2.6. የንባብ ክሂልን ማስተማሪያ አቀራረቦች

ንባብ ካሉት ጠቀሜታዎች አንዱ የተለያዩ አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅና ለመገንዘብ መሆኑ በዚህ ጥናት 2.2 ላይ ተገልጿል። Haverson (1991:85) እና Wallace (1992:54) እስከአሁን ድረስ በንባብ ትምህርት ዙሪያ የሚታወቁትን የማስተማር አቀራረቦች በሁለት ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ይገልጻሉ። እነዚህም አቀራረቦች ክሂል-ተኮር እና ስልት-ተኮር በመባል ይለያሉ። ከዚህ በመቀጠልም አቀራረቦቹን ለመቃኘት ይሞከራል።

2.6.1. ክሂል-ተኮር አቀራረብ

በክሂል-ተኮር አቀራረብ መሠረት የንባብ ትምህርት የሚሰጠው ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ለማዳበር ነው። Wallace (1992:54) Cook (1989)ን ጠቅሰው እንደገለጹት በዚህ በክሂል-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠው ተማሪው ምን መማር አለበት? ለሚለው እንጂ ትምህርቱ እንዴት መሰጠት አለበት? ለሚለው አይደለም፣ ለምሳሌም ድምጾችን በትክክል መጥራት (እንደ አፍ-ፈት)፣ ቃላት መለየት፣ ለቃላት ትርጉም መስጠት (በአውድ ወይም ከአውድ ውጭ) የመሳሰሉት ችሎታዎች እንዲዳብሩ ትኩረት ይሰጣቸዋል እንጂ ትምህርቱን በምን አይነት አቀራረብ መማር አለባቸው ለሚለው ትኩረት አይሰጥም።

በሌላ በኩል Haverson (1991:185) በበኩላቸው ሲገልጹ ክሂል-ተኮር አቀራረብ የሚከተለው ከትንሹ የቋንቋ ቅንጣት (ድምፅ) በመነሳት ማለትም ድምፅ-ቃል-ሐረግ-ዐረፍተ ነገር ወይም ከዐረፍተ ነገር መዋቅር ወደ እያንዳንዱ ድምጽ በመከፋፈል የማስተማርና ማሳወቅ ሂደት ነው። ከዚህም ሌላ ክሂል-ተኮር አቀራረብ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው በድምጾችና ድምጾችን በሚወክሉ ትዕምርቶች መካከል ያለውን ግንኙነት በመለየት ላይ ነው። ይህን ግንኙነት መለየት በጽሁፍ የቀረበውን ሀሳብ ለመገንዘብ ያስችላል። በዚህ መሠረት ክሂል-ተኮር አቀራረብ ለድምጽና ትዕምርቶች ግንኙነት፣ ለቃላት፣ ለሰዋስው እና አንብቦ ለመረዳት ችሎታዎች መዳበር ትኩረት ይሰጣል። በተለይ በዚህ አቀራረብ የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው የተቀናጁ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መዳበር ጽሁፍን አንብቦ ለመረዳት መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ ነው።

2.6.2. ስልት-ተኮር አቀራረብ

ንባብን ለማስተማር በስራ ላይ ውለው ከነበሩት አቀራረቦች አንዱ ስልት-ተኮር አቀራረብ ነው። Wallce (1992:57) እንደገለጹት ለክሂል-ተኮር አቀራረብ እንደ አማራጭ መጠቀም የሚቻለው ስልት-ተኮር አቀራረብን ነው።

ስልት-ተኮር አቀራረብ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በማቀናጀት አንድን ጽሁፍ የምንረዳበትን መንገድ በማለማመድ ላይ ያተኩራል። ለዚህም ምክንያቱ አንድ ጽሁፍ እንደ አንባቢው አላማና እንደ ጽሁፉ ባህሪ ሊለያይ ስለሚችል ነው። በዚህ መሠረት አንድ አንባቢ ጽሁፍን ለመረዳት የራሱን የአነባበብ ስልት በመቀየስ የሚያነብበትን መንገድ የሚያለማምድ አቀራረብ ነው ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ Haverson (1991:186) በበኩላቸው በስልት-ተኮር አቀራረብ ንባብ ማለት በተሳካ ሁኔታ አንብቦ የመረዳት ሂደት ነው። ይህንን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ደግሞ አንባቢው የራሱን የቀደመ እውቀት ይጠቀማል። በስልት-ተኮር አቀራረብ አንባቢው የቀደመ እውቀቱን በመጠቀም ስለሚያነበው ነገር ግምት በመስጠት በንባቡ ሂደት ግምቱ ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል፤ ወይም ግምቱ ትክክል ካልሆነ እንደገና ንባቡን በመከለስ ሀሳቡን ለመገንዘብ ጥረት ያደርጋል። የአንባቢው ትኩረትም አንብቦ መረዳት ነው።

በአጠቃላይ ክሂል-ተኮርም ሆነ ስልት-ተኮር አቀራረብ የራሳቸው ንባብን የማስተማሪያ አቀራረብ አላቸው። ክሂል-ተኮር አቀራረብ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችለው የተቀናጀ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መዳበር ነው በሚል ትኩረት የሚያደርገው ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በማዳበር ወደ ውጤት ማድረስን ነው። ስልት-ተኮር አቀራረብ ደግሞ አንባቢው አንብቦ ለመረዳት የቀደመ እውቀቱን መሠረት በማድረግ አዲስ ከሚያነበው ሀሳብ ጋር አዋህዶ ግምት በመስጠት አንብቦ ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበትን ሂደት የሚያለማምድ አቀራረብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

2.7. የንባብ ንዑሳን ክሂሎች

ንባብ ሲባል በጽሁፍ የቀረበን ሀሳብ መረዳት እንደሆነ በዚህ ጽሁፍ 2.1. ተገልጿል። ይህንንም ለማከናወን መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አሉ። እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች እርስ በርስ በመዋሃድ አንብቦ የመረዳትን ሂደት ያጠናክራሉ። በንባብ ትምህርት ዙሪያ ጥናት ካደረጉት ምሁራን መካከል ለምሳሌ Alderson and Urqunent eds. (1984) በመጽሐፋቸው መግቢያ ላይ እንደገለጹት የንባብ ችሎታ መዳበር የንባብ ንዑሳን ክሂሎች መዳበር ውጤት ነው።

Geenalls and Swan(1986: 3-4) ደግሞ በበኩላቸው ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ እንደገለጹት ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያዳብሯቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አሉ። እነዚህም ያልተለመዱ ቃላትን ፍቺ ከምንባቡ አውድ መረዳት መቻል፣ የጽሁፉን አደረጃጀት መረዳት፣ አጠቃላይ ግንዛቤን ማግኘት መቻል፣ የመገመት ችሎታ፣ የጽሑፉን መልዕክት መረዳት እና ጽሑፉን መገምገም የመሳሰሉት ናቸው።

ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ብዛት በተመለከተ ምሁራን የተለያየ ዝርዝር ሲያወጡ ይስተዋላል። አንዳንዶቹ ምሁራን ለምሳሌ Alderson and Urequnent (Eds.) (1984) Lunzer and Grardner (1979:42)ን ዋቢ አድርገው እንደጠቀሱት ከሶስት እስከ ሰላሳ ስድስት ይሆናሉ። ከድረ ገጽ (2007) የተገኘው መረጃ ደግሞ አስራ ሁለት መሆናቸውን ይጠቁማል። እነሱም፡-

- የመገመት ችሎታ፣
- ዋናውን ሃሳብ ማግኘት፣
- የቀደመ እውቀትን መጠቀም፣
- ዋናው ነጥብ ላይ በማተኮር ማንበብ፣
- በርጋታ ማንበብ፣
- የቃላትን ፍቺ ከአውዱ ለመረዳት መሞከር፣
- አንብቦ ለመረዳት የቃላትን አገባብ ለመረዳት መሞከር፣
- ንባብን በፍጥነት ማከናወን፣
- በንባብ ጊዜ ለማንዛቤ ጊዜ መውሰድ፣
- ያነበቡትን ጽሑፍ በአጭሩ ማስፈር፣
- የንባቡን ዓላማ መለየት፣
- የጽሑፉን አይነት መለየት፣

ከዚህም ሌላ እንደ Grellet (1981:4-5) ገለጻ ንባብ በርካታ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በውስጡ ይዟል ዋና ዋናዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው በማለት አክለውም ሲገልጹ እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ዝርዝር የተወሰዱት "Munby's Communicative Syllabus Design" ከሚሰኘው መጽሐፍ ነው። ዝርዝሩም በመጽሐፉ እንደቀረበው የሚከተለው ነው።

- የቋንቋውን የአጻጻፍ ስርዓት መለየት፣
- የቃላትን ፍች ከቀረበው አውድ ለመረዳት መሞከር፣
- በግልጽ የተነገሩ መረጃዎችን መረዳት፣
- በተዘዋዋሪ የተነገሩ መረጃዎችን መረዳት፣
- የቀረበውን ጽንሰ ሀሳብ መረዳት፣
- የዐረፍተ ነገሮችን ተግባርና አገላለጻቸውን መረዳት፣
- በዐረፍተ ነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት፣
- በጽሁፉ አካልና በሰዋስው አያያገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት መረዳት፣
- የጽሁፉን ጠቃሚ ነጥቦች በአጭሩ መናገር፣ መጻፍ፣
- ጽሁፉን በሌላ አመለካከት ለመተርጎም መሞከር፣

- በዲስኩር ውስጥ ያሉትን አመልካቾች መለየት፣
- ዋናና ዝርዝር ነጥቦችን መለየት፣
- የጽሁፉን ዋና ነጥብ በአጭሩ መግለጽ፣
- ከጽሁፉ ጠቃሚ ነጥቦችን ለይቶ ማውጣት፣
- የአሰሳ ንባብ፣
- የገረፍታ ንባብ፣
- የቀረበውን መረጃ በስዕላዊ ሁኔታ ለመግለጽ መሞከር፣

Grellt (1981፡4-5) ሀሳባቸውን ሲያጠቃልሉ ከላይ የተዘረዘሩት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመመለስ ወይም የንባብ ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ።

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የተገለጹት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ቁጥር የተለያዩ ስለመሆናቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከምክንያቶቹ መካከል የሚጠቀሱት አንዳንዶቹ ምሁራን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አንዳቸው በአንዳቸው ስር ሊጠቃለሉ ይችላሉ የሚል አስተያየት አላቸው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ንዑሳን ክሂሎች ተብለው በመነጣጠል መጠቀስ የሌለባቸው ነገር ግን የንባብ ሂደት ናቸው የሚል የመከራከሪያ ነጥብም ያነሳሉ። በተጨማሪም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች እንደ አንባቢው የችሎታ ደረጃ ሊለያዩ ይችላሉ የሚል ነጥብም አለ። ይህን ሀሳብ ከሚያነሱት ምሁራን መካከል ለምሳሌ Alderson and Urequnet (Eds.) (1984) Lunzer and Gardner (1979) ዋቢ አድርገው እንደገለጹት የተለያዩ የጥያቄ አይነቶች የሚመለሱት በተለያየ የንባብ ንዑስ ክሂል ችሎታ ነው። ለዚህም ምሳሌ ሲጠቅሱ የቃላትን ፍቺ የመለየት ንዑስ ክሂልና በተዘዋዋሪ የቀረበ ጽሁፍን መልዕክት መረዳት አንድ አይነት ችሎታን የሚለካ አይደለም። በዚህም ምክንያት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ቁጥር የተለያየ መሆን የተለያዩ ምሁራን ከሚነሱበት የመገምገም ደረጃ ሊመነጭም የሚችል መሆኑን ይገልጻሉ።

በዚሁ መሰረት ስንቃኘው መሰሉ (1994፡55) በስራ ላይ ላሉ ሰልጣኞች ባዘጋጁት ማስተማሪያ ጽሁፍ ውስጥ እንደገለጹት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በንባብ ትምህርት እንዲያዳብሩ የሚፈለጉ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አሉ። እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ከዚህ ቀጥሎ በመዘርዘር ቀርበዋል።

1. የመገመት ችሎታ፡- ቅድመ ንባብ ተግባር ውስጥ አንዱ የመገመት ችሎታ ነው ጥሩ ችሎታ ያላቸው አንባቢዎች ርዕሱን በማየት በምንባቡ ሂደት ውስጥ ምን ሊመጣ

እንደሚችል ቀድሞ ግምት ይሰጣሉ። በንባቡ ሂደት ከግምቱ ጋር ምን ያህል እንደተጣጣመ በመመዘን የመገንዘብ ደረጃቸውን ያጠናክራሉ።

2. **የተወሰኑ መረጃዎችን ለይቶ ማውጣት፡-** አንድ ፅሁፍ የተወሰነ ተፈላጊ ነጥብን ብቻ ለይቶ መረጃን ለማግኘት የሚከናወን ንባብ ነው። መረጃዎቹም አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህንን ተግባር ለማከናወን መረጃን ለይቶ የማውጣት ችሎታን ማዳበር ይቻላል።
3. **በአጠቃላይ ግንዛቤ ማግኘት መቻል፡-** አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት የሚነበብ ንባብ የገረፍታ ንባብ ይባላል። ይህን ንዑስ ክሂል ለማዳበር የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ ያህል ስዕልን ሰጥቶ ከጽሁፍ ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግን መጥቀስ ይቻላል።
4. **ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ማንበብ፡-** በዚህ ስር ሊካተቱ የሚችሉ ነገሮች ከቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ዝርዝር መረጃን የመፈለግ ሂደት ነው። በዚህም ሂደት የደራሲውን ስሜት፣ ስንት? ምን ያህል እና ሌሎችም በዝርዝር የቀረቡ መረጃዎችን ለማግኘት የሚደረግ ንባብ ነው።
5. **ያልተለመዱ ቃላትን ፍቺ ከምንባቡ አውድ መረዳት መቻል፡-** ያልተለመዱ ቃላትን ፍቺ ከአውድ መረዳት መቻል ጥሩ አንባቢ ከሚኖረው ችሎታ አንዱ ነው። ይህም ለቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከመፈለግ ይልቅ ከገቡበት አውድ በመነሳት ግምት የመስጠት ሂደት ነው። ይህም ያልተለመዱ ቃላት ሲያጋጥሙ ትርጉማቸውን ለመረዳት መዳበር ያለበት ችሎታ ነው።
6. **የጽሁፉን አደረጃጀት መረዳት፡-** አንድ ጽሁፍ ውስጥ ያለውን አደረጃጀት መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም ከዐረፍተ ነገር አንስቶ ጽሁፉ እንዴት እንደተዋቀረና ለማዋቀርም በጥቅም ላይ የዋሉ አያያገሮችን አጠቃቀም ለማወቅ ይረዳል። የንዑስ ክሂሉ መዳበር አስፈላጊነትም በተዘዋዋሪ የቀረቡ አገላለጾችን ተገንዝቦ ጽሁፉን ለመረዳት ስለሚያስችል ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት በሚቀርብበት ጊዜ ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው ናቸው። የነዚህ ንዑሳን ክሂሎች መዳበር የጽሁፉን መልዕክት ለመረዳት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ይህን ሁኔታም በመረዳት የመምህራን ተግባር ተማሪዎቹ ለንባብ ማስተማሪያ የተዘጋጁ ጽሁፎችን አንብበው የተለያዩ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን እንዲያዳብሩ መርዳት ነው። እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በመማሪያ በክፍል ውስጥ እንዴት ማለማመድ እንደሚቻል የተለያዩ ምሁራን የራሳቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል። ከዚህ በመነሳት በዚህ ጥናት ውስጥ ከድረ ገጽ(2007) የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ አስራ

ሁለት ያህል ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ላይ በማተኮር ጥናት ለማድረግ ተሞክሯል። እነዚህን የንዑሳን የንባብ ክሂሎች፡-

በቅድመ-ንባብ ደረጃ፡-

- በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል የመገመት ችሎታ፣
- ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት፣

በጊዜ-ንባብ ደረጃ፡-

- የአሰሳ ንባብ፣
- የገረፍታ ንባብ፣
- የዝምታ ንባብ፣
- ስዕልን ማገናዘብ ወይም ዝርዝር መረጃዎችን በሰንጠረዥ መመላት፣
- ከንባቡ ዝርዝር መረጃን ማውጣት፣
- የጽሑፉን አደረጃጀት መረዳት፣
- የቃላትን ፍቺ ከአውድ መረዳት፣

በድህረ-ንባብ ደረጃ፡-

- አጠቃላይ የምንባቡን ሃሳብ መረዳት፣
- ምንባቡን መገምገም፣
- ንባብን ከሌሎች ክሂሎች ጋር ማጣመር፣

2.8. በመማሪያ ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ

የንባብ ትምህርት የታሰበለትን ዓላማ እንዲይዝ የተሻለ የማስተማር ዘዴን በመምረጥ ትምህርቱን ህይወታዊ ማድረግ ያስፈልጋል። የንባብ ትምህርት ቀድሞ ይቀርብበት የነበረውን አቀራረብ በመገምገም ምሁራን ለምሳሌ Celce-murcia (1991) የራሳቸውን ንድፈ ሀሳባዊ ትንተና ሰጥተዋል። እነዚህም ትንተናዎች ልማዳዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ እና ዘመናዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ተብለው ይለያሉ።

2.8.1. ልማዳዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ

የልማዳዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ የንባብ ትምህርት ይቀርብ የነበረው ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች በማሰራት ነበር። በመማሪያ ክፍል ውስጥ አንድን ተማሪ ምንባብ አስነብቦ እንደጨረሱ መልመጃዎችን ማሠራት የሚደገፍ ዘዴ አይደለም፤ ይህ ሁኔታ ንባብን ከማስተማር ይልቅ ወደ ምዘና ያደላ ነው።

በተመሳሳይ መልኩ በድሉ (1996፡29) በመጽሐፋቸው እንደገለጹት "ተማሪዎች በየተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የሚያነቡበት ዘዴ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የበለጠ ጠቃሚ ነው።" ከአንደኛ ደረጃ ባሻገር በዚህ ዘዴ መጠቀም የሚከተሉት ደካማ ጎኖች እንዳሉት በመዘርዘር አቅርበዋል።

- በአንድ ጊዜ የሚያሳትፈው አንድ ተማሪ ብቻ ነው። በዚህ የተነሳ በርካታ ተማሪዎችን በያዘ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ነው።
- የተማሪዎች ትኩረት በሚያዳምጡት ተማሪ የአነባብ ስልትና የድምጽ ሁኔታ ስለሚሳብ ውህድ አሀዱ ይዘት ላይ እንዳያተኩሩ ያደርጋል።
- ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ ህይወታዊ አይደለም። ይህ ልምድ ሰዎች እውናዊ ኑሮአቸው ውስጥ ንባብን ከሚጠቀሙበት መንገድ የተለየ ነው።
- በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሲያነቡ ፍጥነታቸው ዝቅተኛ ስለሚሆን ጊዜ ይፈጃል።

ከላይ እንደተገለጸው ልማዳዊ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ የጮክታ (ድምጽን በማውጣት ማንበብ) ንባብን የሚያዘወትር በመሆኑ አብዛኛው ተማሪ ከአንባቢነት ይልቅ አድማጭነትን እንዲያዳብር የሚያደርግ ነው። በዚህም ምክንያት በተለይ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዙ የማይደገፍ ዘዴ ነው። ነገር ግን እዚህ ላይ ግን መጤን ያለበት ጉዳይ አለ። ይኸውም ድምጽን ከፍ አድርጎ የማንበብ አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ይህም የሚከናወነው በተለያዩ ምክንያቶች ነው። ለምሳሌ ያህል መምህሩ የተማሪዎቹን የንባብ ደረጃና የንባብ ፍጥነት ደረጃ ለመወሰን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሊያደርገው ይችላል። ንባብን በልማዳዊ ሁኔታ ማስተማር የሚደገፍ አይደለም ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ዘመናዊ የንባብ ማስተማሪያ ዘዴ መከተል እንደሚገባ ምሁራኑ ይመክራሉ። ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ዝርዝር ሁኔታ ይህን ይመለከታል።

2.8.2. ዘመናዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ

የዚህ ጥናት አላማ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጠውን ትኩረት መፈተሽ በመሆኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብን በዝርዝር ማየት የግድ ነው። ምክንያቱም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚተገበሩት በንባብ ትምህርት ውስጥ በመሆኑ ነው። በዚህ መሠረት የንባብ ትምህርት በዘመናዊ መንገድ በክፍል ውስጥ የሚቀርብበት ደረጃዎች እንዳሉት በርካታ ምሁራን ለምሳሌ Grellet (1981:4-5)፣ Nuttal (1982:166)፣ Williams (1984:10)፣ Harmer (1991፡151)፣ Wallace (1992:86)፣ Ur (1996 :146)፣ Atkin et.al. (1996:81)፣ Pupalia (2000:76)፣ Celce-Murcia (1991:200) እና BBC (2007) በዝርዝር ገልጸዋል። በዚህም መሠረት የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ ሶስት ደረጃዎች እንደአሉት ምሁራኑ

ይገልጻሉ። እነዚህም የንባብ ማቅረቢያ ደረጃዎች ቅድመ-ንባብ ደረጃ፣ ጊዜ-ንባብ ደረጃ እና ድህረ-ንባብ ደረጃ ናቸው።

በነዚህ ሶስት ንባብን በክፍል ውስጥ የማቅረቢያ ደረጃዎች በሚከናወኑበት ጊዜ የንባብ ንዑሳን ክሂሎች ይዳብራሉ። የንባብ ንዑሳን ክሂሎች መዳበር ደግሞ ጥሩ አንባቢ ለመሆን የሚያስችል ክህሎት ነው። ስለዚህ ከዚህ በመቀጠል የሚቀርበው በሶስቱ ደረጃዎች ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን በመዘርዘር ነው። ዝርዝሩ የቀረበው Williams(1984:37-40)፣ Nunan(1991:76-80) እና መሰሉ(1994:58-61) እንዳመለከቱት ነው።

2.8.2.1 ቅድመ ንባብ ደረጃ

በዚህ የንባብ ደረጃ ከንባብ በፊት የሚከናወኑ ተግባሮች ይተገበራሉ። ከእነዚህም ተግባሮች መካከል መምህራን ተማሪዎችን ለንባብ የሚያዘጋጁበት፣ ሰሜታቸውን ለንባብ የሚያነቃቁበት፣ የተማሪዎችን ትኩረት ወደ ትምህርቱ እንዲሆን የሚያደርጉበት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ የሚከተሉት ተግባራት ሊከናወኑ ይችላሉ።

1. ተማሪዎችን ምንባብን የሚያነቡበትን ምክንያት ማሳወቅና የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ፣
2. ለንባብ የሚቀርበው ምንባብ ርዕስ ዙሪያ ያላቸውን የቀደመ ዕውቀት አሁን አዲስ ከሚማሩት ይዘት ጋር በማገናኘት እንዲገነዘቡት ማድረግ፣
3. የሚቀርበውን ርዕስ ማስተዋወቅ፣
4. በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ ይችላሉ ብለው እንደሚያስቡ በመጠየቅ እንዲገምቱ ማድረግ፣

በዚህ ደረጃ መምህሩ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን ይችላል።

ሀ. ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ አደራጅቶ ምንባቡ የሚያነሳቸውን ሀሳቦች በመወያየት እንዲገምቱ ማድረግ፣

ለ. ከተማሪዎቹ የተነሱትን ጥያቄዎች ለክፍሉ በማቅረብ ማወያየት

5. ምንባቡን ሲያነቡ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ የሚላቸውን ቁልፍ ቃላት ከምንባቡ በማውጣት ፍቺ መስጠት፣

2.8.2.2. ጊዜ-ንባብ ደረጃ

በዚህ የንባብ ደረጃ የሚከናውኑት የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት የሚያስችሉ ተግባራት ናቸው። ይህንንም ለማከናወን ሁለት የንባብ አይነቶችን እንጠቀማለን። የአሰሳ ንባብ፣ የገረፍታ ንባብ እና ጥልቅ ንባብ ናቸው።

በዚህ ደረጃ የሚዳብሩት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች

- መገመት መቻል፣
- አጠቃላይ መልዕክትን ማግኘት መቻል፣
- ውስን መረጃዎችን ማግኘት መቻል፣

እነዚህንም ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር ሶስት ተግባራትን በቅደም ተከተል ማከናወን ያስፈልጋል።

I. የአሰሳ ንባብ

1. መልመጃ (ጥያቄ) መስጠት፡- በዚህ ደረጃ መምህሩ ማዳበር በሚፈልገው ክሂል ላይ የተመሠረተ አንድ ወይም ሁለት ጥያቄ ይሰጣል።እነዚህም ጥያቄዎች የሚመለሱት የአሰሳ ንባብ በማካሄድ ነው። ስለዚህ የአሰሳ ንባብ እንዲያደርጉ ያበረታታል።
2. በዝርዝር ማስነበብ፡- በዚህ ደረጃ ቀደም ሲል የተሰጡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንባቡን በፍጥነት ያነባሉ። በዚህም የገረፍታ ንባብ ያከናውናሉ። ተማሪዎች ንባቡን የሚጨርሱበት ጊዜም ተወስኖ መሰጠት አለበት።
3. ምጋቤ ምላሽ መስጠት፡- ምጋቤ ምላሽ የሚሰጠው ተማሪዎቹ በግል፣ በጥንድና በቡድን ካከናወኗቸው ተግባራት ላይ ነው። መጀመሪያ በግል ይሰራሉ፤ በጥንድ (በቡድን) ይወያያሉ። ከዚያም መምህሩ ከተማሪዎች ጋር በሚደረግ ውይይት መልመጃዎችን ያሰራል።

II. ጥልቅ ንባብ

ሁለተኛው ጥልቅ ንባብ የሚካሂድበት ሂደት ሲሆን ለእያንዳንዱ ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ ምንባቡን በዝርዝር የማስነበብ ስራ የሚከናወንበት ነው። በሚከተለው ቅደም ተከተላዊ ሁኔታ ትምህርቱ መካሄድ አለበት።

1. መልመጃ መሰጠት፡- በዚህ ደረጃ ላይ መምህሩ ዝርዝር ጉዳዮችን የሚጠይቁ በርካታ ጥያቄዎችን ይሰጣል። ለምሳሌ ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽ መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙላት ሊሆን ይችላል።
2. በዝርዝር ማስነበብ፡- በዚህ ደረጃ ቀደም ሲል ምንባቡን በዝርዝር እንዲረዱ የተሰጧቸውን ጥያቄዎች ለመስራት በዝምታ የሚያነቡበት ደረጃ ሲሆን ንባቡ በርጋታ ይከናወናል።

በንባቡ ሂደት ዝርዝር መረጃ ማገኘት መቻል፣ የጽሁፍን አደረጃጀት መረዳት መቻልና፣የቃላትን ፍቺ ከገቡበት አውድ አንጻር መገመት የመሳሰሉት ክሂሎችን ያዳብራሉ።

3. ምጋቤ ምላሽ መስጠት፡- ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በግል ከሰሩ በኋላ እርስ በርስ እየተወያዩ በምላሾቻቸው ላይ እንዲነጋገሩና መልሶቻቸውን እንዲያነጻጽሩ፣ መልሶቻቸው የተለያዩ ከሆኑም ምንባቡን ተመልሰው እየተመለከቱ እንዲያረጋግጡ ይደረጋል። በዚህም ደረጃ የመምህሩ ተግባር የሚከተሉትን ነጥቦች ሊይዝ ይችላል።
   - ተማሪዎቹን በመልሶቹ ላይ ማወያየት፣
   - ለጥያቄዎች መልስ በቃል መስጠት፣ እርማት መስጠት፣
   - ግልጽ ያልሆኑ አስፈላጊ ቃላትን ማብራራት፣

2.8.2.3 ድህረ -ንባብ ደረጃ

በዚህ የንባብ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት በመስጠት ነው።

1. አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣
2. ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲይዙት ማድረግ፣
3. ምንባቡን እንዲገመግሙ ማበረታታት (ጥሩነቱን፣ ተአማኝነቱን፣ በሀሳቡ መስማማት አለመስማማታቸውን ወዘተ...) መጠየቅ፣
4. ራሳቸውን ከምንባቡ ሁኔታ ውስጥ አስገብተው እንዲመልሱ ማድረግ፣
5. ንባብን ከሌሎች ክሂሎች ጋር እንዲያጣምሩ ለማስቻል መልመጃዎችን መስጠት፣ ለምሳሌ መጽሐፍ አንብበው ሪፖርት እንዲጽፉ ማድረግ ሊሆን ይችላል።

ከላይ በዝርዝር የቀረቡት ሁኔታዎች የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ መከተል የሚገባውን ቅደም ተከተላዊ ሁኔታና በውስጡም ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን የሚዳብሩበት የንባብ ደረጃ ተገልጿል። ይህን ሁኔታ ተከትለው መምህራን ተግባራዊ ቢያደርጉ የንባብ ትምህርት የተሳካ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል።

2.9 በንባብ ትምህርት ሂደት የመምህራን ድርሻ

በንባብ ትምህርት ሂደት የመስኩ ባለሞያዎች የሚስማሙበት ሀሳብ ተማሪው በራሱ ጥረት የንባብ ችሎታውን እንዲያዳብር ማድረግ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የንባብ ልምድ ማጣት ችግር የሚከሰተው መምህራን ለተማሪዎቻቸው ከሚያደርጉት አላስፈላጊ እርዳታ የመነጨ ነው።

ለምሳሌ ያህል ተማሪው በሚያነብበት ጊዜ ፊደላትን ሲገድፍ ንባብን አቋርጦ እርማት መስጠት ተማሪውን በራሱ እንዳይተማመን ያደርጋል (Ur 1996: 149)።

ከዚህ ጋር በተያያዘ Nuttal (1982:22) እንደገለጹት መምህራን ማድረግ ያለባቸው ተስማሚ የሆነ ምንባብ መምረጥና የተማሪዎችን ቀልብ ሊስቡ የሚችሉ መልመጃዎችን ማዘጋጀት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች የንባብ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ንባብን በዘመናዊ መንገድ በማስተማር የተማሪዎቻቸውን የንባብ ችሎታ እንዲሻሻል ማድረግ አለባቸው። የንባብ ችሎታ እንዲኖራቸው ከመማሪያ ክፍል ውጭ እንዲያነቡ መጠቆም የመምህራን ትልቅ ድርሻ ነው።

በተጨማሪም Celce-marcia (1991:20) በበኩላቸው እንደገለጹት በንባብ ትምህርት ጊዜ መምህራን ከፍተኛ ሀላፊነት አለባቸው። ስለዚህ መምህራን ከክፍል ውስጥ አመቺ የሆነ ሁኔታን መፍጠር ይገባቸዋል። በንባብ ትምህርት ጊዜ መምህራን ስለንባብ አወንታዊ አመለካከት ያላቸው መሆኑ ጠቀሜታ አለው። ከዚህም ሌላ ተማሪዎቹ ስለሚያነቡት ጽሁፍ ሀሳብ ማስተዋወቅ የመምህራን ድርሻ ነው። ለተማሪዎቹ የሚቀርበው ጽሁፍ ከህይወታቸው ጋር ያለውን ግንኙነት ማመላከት ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም መምህሩ አጋዥ የሆኑ ጽሁፎችን ከታወቁ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች እና ሌሎች የታተሙ ጽሁፎችን በማስተማሪያነት በመጠቀም ተማሪዎችን ከእውናዊው አለም ጋር ማዛመድ ይጠበቅባቸዋል።

በአጠቃላይ መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት፣ በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን እየተዘዋወሩ መከታተል፣ መልመጃዎችን ማሰራት፣ ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ላይ ማወያየት የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናወን ሊዘነጋ የማይገቡ ናቸው።

2.10. በንባብ ትምህርት ሂደት የተማሪዎች ድርሻ

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ትምህርቱ የተሳካ እንዲሆን መምህራንና ተማሪዎች በመግባባት መስራት አለባቸው። የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ ተማሪዎች ተሳታፊ በመሆን የንባብ ትምህርት መለማመድ ይጠበቅባቸዋል። የንባብ ትምህርትን ህይወታዊ ለማድረግ በጥንድና በቡድን ስራ በመሳተፍ ሊለማመዱ ይገባል።

ይህን ሀሳብ በተመለከተ Williams (1986:43) እንዳስረዱት የተማሪዎች ሚና የሚጠናከረው የተሰጣቸውን ስራ በጥንድም ሆነ በቡድን ማከናወን ሲችሉ ነው። ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር Richard (1990:13) ደግሞ የተማሪዎች ሚና ምን መሆን አንዳለበት በመዘርዘር አቅርበዋል።

- ራሳቸውን ለመማር ዝግጁ አደርገው መገኘት፣
- የሚሰጣቸውን መልመጃዎች ከጓደኞቻቸው ጋር ማከናወን፣
- በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ መሆን፣

በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ ያለው የመማር ማስተማር ስራ የተሳካ የሚሆነው መምህራንና ተማሪዎች በሚፈጥሩት መስተጋብራዊ ግንኙነት ነው። በድሉ (1996) በበኩላቸው Collie and Slater (1987)ን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት "ተማሪዎች ለስራው የሚኖራቸው የመጀመሪያ ግምት በሚከናወነው የክፍል ውስጥ ተግባር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው። ሰራውን በጉጉትና በአድናቆት ከተቀበሉት በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ተግባር ውጤታማ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው።" ስለዚህ መምህራንና ተማሪዎች አንድ ላይ ሆነው የንባብ ትምህርቱን ህይወታዊ ማድረግ አለባቸው።

2.11. የንባብ ሂደት ሞዴሎች

በመማር ማስተማር ሂደት ከመምህሩ ሀላፊነቶች አንዱ ተስማሚ የሆነ የማስተማሪያ ሞዴሎችን መጠቀም ነው። በዚህ አንጻር በንባብ ትምህርት ሂደትም የተለያዩ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴሎች አሉ። እነዚህም የንባብ ሂደት ሞዴሎች ሶስት ሲሆኑ በየትኛውም የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ልምምድ ቢያደርጉባቸው የታሰበው የንባብ ክሂል ሊዳብር ይችላል። እነዚህን ሶስት ሞዴሎች ከዝርዝር ወደ ጥቅል ከጥቅል ወደ ዝርዝር እና ሶስተኛው ሁለቱን ሞዴሎች በማጣመር እንደ አንድ ሞዴል የሚወሰድ መስተጋብራዊ የንባብ ሂደት ሞዴል ናቸው (Dubin and David 1991:196፣ Nuttal 1982፣ May 1990:11) ። ቀጥሎ ስለሞዴሎቹ በዝርዝር ቀርቧል።

2.11.1. ከዝርዝር ወደ ጥቅል ንባብ ሂደት ሞዴል

በቀድሞ ጊዜ የንባብ ትምህርት ተደርጎ ይታሰብ የነበረው ሆሄ-ቃል-ሐረግ-ዐረፍተ ነገርን ደረጃ በደረጃ የመረዳት ሂደት ነበር። በዚህ የንባብ ሂደት ግንዛቤ መሰረት መጀመሪያ ንበትን መለየት አስፈላጊ ነው። ከዚህ ሞዴል ውስጥ ትልቅ ትኩረት ይሰጥ የነበረው ለንበት በመሆኑ የንባብን ትምህርት ይጠቀሙበት የነበረው ለንበት ማለማመጃ ነው።

የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎች ምንባቦችን በተማሪ ፊት ጮክ ብለው በማንበብ የንበት ችሎታቸውን (ድምጾችን በትክክል መጥራት) በሚያዳብሩበት ሁኔታ ነው። ከዚህ ሌላ በዚህ ሞዴል ምንባብ የቃላትን ፍቺ ለማስተማር የቀረበ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ተማሪዎች ስለ ንባብ ያላቸው ግምት አሉታዊ እንዲሆን አድርጓል። ይህም በመሆኑ ይህ ሞዴል በሌሎች በተሻሻሉ ሞዴሎች ለምሳሌ ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሂደት ሞዴል የመተካት ሁኔታ አጋጥሞታል።

2.11.2. ከጥቅል ወደ ዝርዝር ንባብ ሂደት ሞዴል

ከጥቅል ወደ ዝርዝር የንባብ ሂደት ሞዴል ቀድሞ የነበረውን የንባብ ሂደት ሞዴል በማሻሻል የመጣ ነው። በዚህ ሞዴል የንባብ ዋናው ጉዳይ አጠቃላይ የንባቡን መልዕክት ለመገንዘብ ነው።

ንባቡም ሲካሄድ አንባቢው የቀደመ እውቀቱን በመጠቀም ሀሳቡን ለመረዳት ጥረት ያደርጋል። በአጠቃላይ በዚህ ሞዴል አንብቦ መረዳት ውጤታማ የሚሆነው ከጥቅል ጉዳይ ተነስቶ ወደ ዝርዝር ጉዳዩች በመሄድ ነው የሚለውን መርህ ተከትሎ ነው። .

2.11.3. መስተጋብራዊ የንባብ ሂደት ሞዴል

መስተጋብራዊ የንባብ ሂደት ሞዴል ከላይ የተገለጹትን ሁለት ሞዴሎች ማለትም ከዝርዝር ወደ ጥቅል ሂደት እና ከጥቅል ወደ ዝርዝር ሂደት ሞዴል አንድ ላይ በማጣመር እንደ አንድ ሞዴል የተመሠረተ ነው። ሞዴሉ ተግባራዊ የሚሆነው የንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ የሚያመላክቱ ፍንጮች ከምንባቡ ተለቅመው ከወጡ በኋላ ወደተማሪው እንዲደርሱ በማድረግ ነው። ይህም ሁኔታ ተማሪው አዲስ የቀረበለትን ይዘት ከቀደመው እውቀት ጋር በማዛመድ የሚገነዘብበት ሂደት ነው።

2.12. የቀድሞ ጥናቶች ቅኝት

በንባብ ትምህርት ዙሪያ ከዚህ በፊት የተሰሩ ስራዎችን ለመቃኘት ተሞክሮአል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት ከተሰሩት ለምሳሌ ያህል ተፈራ ጋሻው (1990)፣ "በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ"፣ የመዝገበ ስዩም (1993) "የንባብ ትምህርት ትግበራ በአስረኛ ክፍል በተመረጡ ሶስት የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቤቶች"፣ ሂሩት አመሀ (1996) በንባብ ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች ትግበራ በአስረኛ ክፍል በተመረጡ ሶስት አዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች (የግል)" መጥቀስ ይቻላል። በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ከተሰሩት ለምሳሌ የማርታ ነጋሽ (1992) "የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ" የእስጢፋኖስ ብስራት (1993) "አስራ አንደኛ ክፍል የንባብ ትምህርት አሰጣጥ"፣ በነዚህ የዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ የተደረጉ ምርምሮች ትኩረት የነበረው የንባብ ትምህርት አቀራረብ ነው። በጥናታዊ ጽሑፎቹ ማጠቃለያም ላይ ትምህርቱ የሚሰጠው በተለምዶአዊ አቀራረብ ስልት በመሆኑ የጮክታ ንባብን እንደሚጠቀሙ፣ ዘመናዊ አቀራረብ ስልትን እንደማይከተሉ ተጠቁሟል። በተጨማሪም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎች መካከል የማስተዋል ውበቱ (1989) " የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደው ጥናት"፣ አስናቀች ሙሉጌታ (1992) "በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ግምገማ" በሚል

የተከናወኑ ተመሳሳይ ጥናቶች ይጠቀሳሉ። የጥናቶቹም ውጤት እንዳመለከቱት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ በማጠቃለያቸው ላይ ተገልጿል።

ሌላው ከዚህ በተለየ መልኩ በንባብ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች የገመገሙት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች ብቃት፣ የንባብ ክሂል መልመጃዎች አቀራረብ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብን በተመለከተ ነው። ከጥናቶቹ መካከል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡት የጌታቸው አዱኛ (1986)"በአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ፣ ማስተማሪያ ምንባቦች ብቃት" በኦሮሚያ ክልል ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት" እና በወንድ አጥር ደነቀ (1993) " በማስተማሪያ ቋንቋነት በኦሮሚያ ክልል ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት" ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው። በተለይ ወንድአጥር (1993) በጥናታዊ ፅሁፉም እንደገለጸው ያለው የአማርኛ የንባብ ክሂል ትምህርት የንባብ ክሂልን በየደረጃው ለማዳበር ብቁ ሆኖ አልተገኘም።

በዘመናዊ መንገድ ንባብን የማስተማሪያ ሞዴሎችን ጠቀሜታ ለመፈተሽ ከተሰሩት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች ውስጥ የኔሰው ደሴ (1990) "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጾኦ"፣ እንግዳ ዘውዴ (1992) የ "ቶኘዳውን" (Top-down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፡ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት" በሚል የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ይገኛሉ። የጥናታዊ ጽሑፎቹ አላማም በሞዴሎቹ በመጠቀም የንባብ ክሂልን ለማስተማር ይረዳል ወይ በሚል በቁጥጥር ቡድን እና በሙከራ ቡድን መካከል ያለውን የጎላ የችሎታ መበላለጥ ማሳየት ነበር። የጥናቶቹ ውጤትም ሞዴሎቹን በመጠቀም የንባብ ክሂልን ማስተማር ውጤታማ እንደሆነ አመልክተዋል።

ከዚህም ሌላ በቅርብ በንባብ ዙሪያ ከተሰሩት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች መካከል ተክሉ ዕቁር (1996) "በዘጠነኛ ክፍል፣ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትንተና፡-መንግስታዊ በሆኑና መንግስታዊ ባልሆኑ የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ ጥናት ነው። ተክሉ (1996) የጥናቱ ዓላማ የነበረው ዘጠነኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መንግስታዊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና መንግስታዊ ካልሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንብቦ መረዳት ትምህርት በተመለከተ የተሻለ የንባብ አቀራረብ የሚታየው በየትኛው ዓውድ እንደሆነ ለመመርመር ነበር። ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም በሁለቱም አውዶች የንባብ ትምህርት ከጥንታዊ አቀራረብና ዘዴ

የተላቀቁ አልነበሩም። ትምህርቱ በንባብ-ጊዜ ደረጃ የተመሰረተ ነው። ቅድመ -ንባብና ድሕረ-ንባብ ደረጃዎች ትምህርት ነበር ለማለት እንደማይቻል ያመለክታል።

በሌላ በኩል ጌትነት ታፈረ (1998) የሰራው ጥናታዊ ጽሑፍ "ልብ ወለድ በመጠቀም በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ በትግራይ ክልል፣ ማዕከላዊ ዞን፣ በተመረጡ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች" በሚል ርዕስ ነው። የጥናቱ ዓላማም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ልብወለድን በመጠቀም የክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ለመፈተሽ ነበር። በጥናቱ የተገኘ ውጤትም መምህራኑ የአቀራረብ ደረጃዎች አላማ በአግባብ ለይተው ተግባራዊ እንደማያደርጉ፣ ሶስቱን የንባብ ደረጃዎች በወጉ እንደማይተገብሯቸው እና የአንብቦ መረዳት የማስተማሪያ ስልቶችን ተጠቅመው ተማሪዎችን እንደማያለማምዷቸው ታውቋል።

ይህ ጥናት ከተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች አንድ የሚያደርገው በንባብ ትምህርት ዙሪያ የተሰራ በመሆኑ ነው። በቅርብ ጊዜ ከተሰሩት ከተክሉ ዕቁር (1996) ጥናታዊ ጽሑፍ አንድ የሚያደርገው ሁለቱም ጥናቶች የንባብ ትምህርትን አቀራረብ መፈተሻቸው ሲሆን፣ የተጠቀሙበት መርጃ መሣሪያ ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅ እና የመምህራንን ዳራ ተመልክቷል። ይህ ጥናት በመንግስት ትምህርት ቤቶች ብቻ በመሰራቱ ከተክሉ ይለያል። እንዲሁም የዚህ ጥናት ዋና አላማ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጧቸውን ትኩረት በዝርዝር በማየቱ፣ መምህራን ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸውን ግንባቤ በመፈተሹ ከቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ይለያል። ከዚህ በተጨማሪም በቪዲዮ ቀረጻ በመታገዙ በመረጃ መሳሪያዎች ልዩነት ያሳያል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ጌትነት ታፈረ (1998) ልብወለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ በሚል ያቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ከዚህ ጥናት የሚለየው በተሰራበት ክልል እና የንባብ ትምህርት ልብወለድ በሆኑ ጽሑፎች ብቻ ሲሰጥ በማጥናቱ ነው።

ከላይ በአጭሩ ቅኝት ለማድረግ የተሞከረው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በተማሪዎች የተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ ነው። ከዚሁ በመነሳት "በ9ኛ ክፍል የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ ለማድረግ ፍላጎት አሳድሮብኛል። ጥናቱ እስከአሁን በንባብ ትምህርት ዙሪያ ከተሰሩት ጥናቶች የሚለይበት ነጥብ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በንባብ ትምህርት ጊዜ የሚሰጣቸው ትኩረት ምን ያህል ነው? የሚለውን በንባብ ትምህርት አተገባበር ውስጥ በጥልቀት ለመመርመር የታሰበ በመሆኑ ነው።

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት መሰረት ያደረገው ዘዴ አይነታዊ ምርምር(Qualitative Research) እና መጠናዊ ምርምር (Quantitative Research)ነው። ከጥናቱ የተገኙትን መረጃዎችና ውጤቶች በአይነትና በመጠን አቅርቧል። አቀራረቡም የሚከተለው የገለፃን (Descriptive) ዘዴ ነው። በርዕሰ ነገሩ ላይ ምሁራን ለንባብ ያበቋቸውን መጻሕፍት በመመርኮዝ በክለሳ ድርሳን የተነሱ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ ማለትም መምህራን ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል? ለየትኞቹ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ይሰጣሉ? መምህራንስ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸውን ግንዛቤ ምን ይመስላል? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘት ነው። የጥናቱን መረጃዎች ለማሰባሰብ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በስራ ላይ ውለዋል። በአጠቃላይ ከጥናቱ የሚገኘው ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

3.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

3.1.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳድር ነው። የጥናቱ ክልል የተመረጠው አመቺ ናሙና (Convenience Sampling) አመራረጥን በመጠቀም ነው። አዲስ አበባ መስተዳድር የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ወካይ ናሙና በዓይነትም በመጠንም ሊገኝ ይችላል የሚል እምነት ስላላት ነው።

በዚህ ጥናት የተካተቱት በአዲስ አበባ መስተዳድር ከሚገኙ ሃያ አንድ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ሶስት ብቻ ናቸው። በዚህ መሠረት ቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ጥቁር አንበሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ድላችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዕጣ የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። ይህም የተደረገው ሶትምህርት ቤቶቹ እኩል ዕድል ይሰጣል ተብሎ ስለታሰበ ነው።

3.1.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት የዘጠነኛ ክፍል ደረጃ በአመቺ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል። በዚህ ምክንያት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ በታሰበበት ጊዜ በትምህርት ላይ ስለሚገኙ በቂ ጊዜ እንዲኖራት ስለሚያስችላት ነው። በተጨሪማም የ9ኛ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ የሚጀመርበት በመሆኑ ችግሩን ከስሩ ጀምሮ ለመለወጥ ጥረት በማድረግ ለቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ ነው።

3.1.3. የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

3.1.3.1 የተጠኚ መምህራን ናሙና አመራረጥ

በሶስቱ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩ 13 የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርት ደረጃቸውና በማስተማር ልምዳቸው ተቀራራቢነት ያላቸው ሁለት ሁለት መምህራን ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ 6 መምህራን ተመርጠዋል። ይህም የተከናወነው መረጃው ከየትምህርት ቤቶቹ የትምህርት አስተዳደር ቢሮዎች ከተወሰደ በኋላ ነው።

3.1.3.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ከሶስቱ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማር ላይ ካሉት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ተጠኚ መምህራኑ በሚያስተምሩባቸው በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ ከ65-70 ተማሪዎች በአማካይ ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል ከእያንዳንዱ ምልከታ ከተደረገበት ክፍል ወካይ ተማሪዎችን ለመምረጥ ከክፍሉ ተማሪዎች አንድ ሶስተኛው ያህል ተወስደዋል። የተማሪዎቹ መረጣም የተካሄደው በአንደኛ ወሰነ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ከፍተኛ፣ አማካይ እና ዝቅተኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ከተለዩ በኋላ ከየምድቡ በአማካይ ሰባት ተማሪዎችን በመውሰድ ነው። የተፈለገውን ያህል ለመውሰድ የዕጣ ናሙና ጥቅም ላይ ውሏል። ለዚህም ምክንያቱ በተለያየ የችሎታ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን በጽሑፍ መጠይቁ ለማካተት ሲባል ነው። በዚሁ መሠረት የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ 70 ሴት ተማሪዎችና 62 ወንድ ተማሪዎች በአጠቃላይ 132 ተማሪዎች ናቸው።

3.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

3.1.4.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

የክፍል ውስጥ ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ነው። የክፍል ወስጥ ምልከታ የተካሄደው ውስን (Fixed) የምልከታ ስልት በመጠቀም ነው። ውስን ምልከታ የሚባለው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከሚታዩት ክንውኖች ለጥናቱ አሰፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ቀደም ብሎ የመከታተያ ቅፅ አዘጋጅቶ መከናወኑን ወይም አለመከናወኑን በማየት መመዝገብ ነው (Weir and Robert 1994፡164፣ Richards and Nunan 1990:47)።

የመከታተያ ቅጹ (Checklist) ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት አስቀድሞ በአጥኝዋ ተዘጋጅቶ በአማካሪዋ ተገምግሞና አስተያየት ተሰጥቶበት አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበታል። ይህንንም የምልከታ መከታተያ ቅጽ በመጠቀም በናሙናነት በተመረጡት 6 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንዋኔ ለሶስት ጊዜ ያህል

የምልከታ ግምገማ ተካሂዷል። ምልከታውም የተካሄደው በአጥኝዋና በሶስት ረዳት ተመልካቾች አማካኝነት ነው። ረዳት ተመልካቾች ሶስት የሆኑበት ምክንያት ሁሉንም አንድ ረዳት ተመልካች መከታተል ስለማይችል ነው። በምልከታውም የተለያዩ ሰዎችን አሰራር ለማካተት ሲባል የተለያየ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት በአመቺ ሁኔታ በመመደብ ምልከታው ተካሂዷል። ረዳት ተመልካቾች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢዱኬሽን የአራተኛ ዓመት የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ናቸው። ከምልከታው በፊትም ከአጥኚዋ ጋር በቂ የጋራ ውይይት ተደርጎ ስለ አሰራሩ በቂ መረጃ ተሰጥቷቸዋል። በዚህ አይነት መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ሶስቱ የምልከታ ውጤቶች ተደምረው አማካይ ውጤታቸውን በመውስድ ለትንተናው በጥቅም ላይ ውለዋል።

3.1.4.2 የቪዲዮ ቀረጻ

የክፍል ውስጥ ምልከታው በቪዲዮ ቀረጻ የታገዘ ነበር። የቪዲዮ ቀረጻው ተጠኝ መምህራን ሲያስተምሩ ለሁለት የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ያህል የተከናወነ ነው። ከተከናወኑት ሶስት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች የመጀመሪያው ቀን የማስመሰል ቀረጻ ተደርጎ ነባ ምልከታ ተካሂዷል። የቪዲዮ ቀረጻው በአጋዥነት በምልከታ ያልታዩ ሁኔታዎችን እንደገና ለማጤን አስችሏል። የመጀመሪያው ዙር የ6ቱ ተጠኝ መምህራን የቪዲዮ ቀረጻ ወደ ጽሁፍ ተገልብጦ በአባሪነት ተያይዟል።

3.1.4.3 የጽሁፍ መጠይቅ

3.1.4.3.1. የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ

ጥናቱን ለማካሄድ በጥቅም ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ነው። ይህ የጽሑፍ መጠይቅ የተዘጋጀው የመስኩ ምሁራን በተለያየ ጊዜ ካነሱዋቸው ትወራዎች በመውስድ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መረጃ ያስገኛሉ በተባለበት ሁኔታ ተደራጅተው ነው። መጠይቆቹ ከተዘጋጁ በኋላ ከአማካሪ ጋር በመነጋገር የማሻሻያ ሐሳብ ተሰጥቶባቸው በስራ ላይ ውለዋል። የጽሑፍ መጠይቁ አራት ክፍሎች አሉት። በክፍል አንድ ስር የተካተቱት አጠቃላይ መረጃን የሚጠይቁ 7 ጥያቄዎች ናቸው። በክፍል ሁለት 4 ዝግ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በክፍል ሶስት ከቀረቡት 21 ጥያቄዎች ደግሞ 10 ጥያቄዎች የንባብ ትምህርት አቀራረብን ሲመለከቱ ቀሪዎቹ 11 ጥያቄዎች ደግሞ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በተመለከተ የቀረቡ ናቸው። በክፍል አራት እንዲሁ 3 ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል (አባሪ 3 ይመልከቱ)። እነዚህም በተጠኝ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሙሉ ለሙሉ ተሞልተው ተመልሰዋል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

3.1.4.3.2 የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ

የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በተመሳሳይ መልኩ በአራት ክፍል የተከፈለ ነው። በውስጡም ክፍል አንድ የተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቁ ናቸው። በክፍል ሁለት አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት መረጃን የሚጠይቁ 3 ዝግ ጥያቄዎችንና 1 ክፍት ጥያቄ ይዟል። በክፍል ሶስት የቀረቡት ጥያቄዎች ደግሞ የንባብ ትምህርት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አቀራረብን ይመለከታሉ። የጽሑፍ መጠይቆቹ የተዘጋጁት በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ዝግጅት እንደተገለጸው በመስኩ ያሉ ምሁራን ስለ ንባብ ትምህርት የሰነዘሩትን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ነው። በውስጡም 7 የንባብ ትምህርት አቀራረብን የሚጠይቁና 11 ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ስለሚሰጣቸው ትኩረት መረጃን የሚጠይቁ ናቸው። በክፍል አራት እንዲሁ 2 ክፍት ጥያቄዎችን ይዟል (አባሪ 4) ይመልከቱ። በአጠቃላይ ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ 3 ክፍት ጥያቄዎችና 21 ዝግ ጥያቄዎችን ይዟል።

የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በሶስቱም ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ተማሪዎች ተበትኗል። የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች የተመረጡት ተጠኝ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከሚያስተምሩባቸውና ምልከታው ከተካሄደባቸው 6 የመማሪያ ክፍሎች ማለትም በአማካኝ 22 ተማሪዎችን ከየክፍሉ በናሙናነት በመውሰድ ነው። በዚህ መሠረት የጽሑፍ መጠይቁ (6x22) በ132 ተማሪዎች ተሞልቶ ተመልሷል።

3.1.4.4 ቃለመጠይቅ

ከጽሑፍ መጠይቁ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። ቃለ መጠይቁ ለመምህራንና ለአማርኛ ክፍለ-ትምህርት ኃላፊዎች የቀረበ ነው። በዚህም መሰረት አንዱ ለተጠኚዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ነው። ምንም እንኳን ለመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተሰጠ ቢሆንም በጽሑፍ መጠይቁ ያልተገለጹ ሀሳቦች ካሉ በቃለ መጠይቅ ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ቃለ መጠይቁም በውስጡ 6 ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ሁለተኛው ቃለመጠይቅ ለአማርኛ ቋንቋ የክፍለ-ትምህርት ኃላፊዎች የቀረበ ነው። በውስጡም 3 ጥያቄዎች አካቷል (አባሪ 5 ተመልከቱ) ። በቃለመጠይቁም መልስ መምህራን ከሚያነሱት ሀሳብ ጋር ለማመሳከሪያነት በመዋል መረጃውን አጠናክሯል።

ምዕራፍ አራት

የጥናቱ ትንተናና ውጤት

በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች በየመልካቸው ተጠናቅረው ተተንትነዋል። ትንተናው መሠረት የሚያደርገው በክፍል ምልከታ፣ በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ፣ በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ፣እንዲሁም ለመምህራን እና ለአማርኛ ቋንቋ ክፍለ-ትምህርት ኃላፊዎች በቀረበው ቃለመጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ነው። የትንተናው አደረጃጀትም በመረጃዎቹ ላይ የተመሰረተ ነው።

4.1 የተጠኝ መምህራን ዳራዊ መግለጫ

ሠንጠረዥ አንድ፡- የተጠኝ መምህራን ዳራ ከጾታ፣ ከዕድሜና ከትምህርት ደረጃ አንጻር

መለያ ቁጥር	ጾታ	ዕድሜ	የትምህርት ደረጃ	የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት		የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ	የአገልግሎት ዘመን
				ዋና	ንዑስ		
01	ወንድ	41	ዲግሪ	አማርኛ	እንግሊዘኛ	9ኛ	22
02	ሴት	52	ዲግሪ	አማርኛ	-	9ኛ	32
03	ወንድ	34	ዲግሪ	አማርኛ	እንግሊዘኛ	9ኛ	15
04	ወንድ	57	ዲግሪ	አማርኛ	-	9ኛ እና 10ኛ	33
05	ሴት	32	ዲግሪ	አማርኛ	እንግሊዘኛ	9ኛ እና 10ኛ	9
06	ሴት	43	ዲግሪ	አማርኛ	እንግሊዘኛ	9ኛ እና 10ኛ	25

በሠንጠረዥ አንድ እንደተመለከተው ተጠኝ መምህራን ስድስት ናቸው። በጾታ ረገድ ሲታይ እኩል ቁጥር ያላቸው ሶስት ወንድ (50%) እና ሶስት ሴት (50%) መምህራን ናቸው። የተጠኝ መምህራንም ዕድሜ ደረጃ ከ32 እስከ 57 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል የሚገኝ ነው። በትምህርት ደረጃ አንጻር ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው። በስልጠና ደረጃም ሲታይ 4(66.7%) መምህራን አማርኛ በዋናነት እና እንግሊዝኛን በንዑስ ትምህርትነት አጥንተዋል። 2 (33.3%) መምህራን ደግሞ አማርኛን ብቻ በዋነኛነት ያጠኑ ናቸው።

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የተማሪዎች ዳራ ከጾታ፣ ዕድሜና

ጾታ				ዕድሜ			
ሴት		ወንድ		14-16		17-19	
ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
70	53	62	47	110	83	22	17

የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች 132 ሲሆኑ 70 (53%) ሴት ተማሪዎች እና 62 (47%) ወንድ ተማሪዎች ናቸው። የዕድሜ ክልላቸው ሲታይ ከ14-16 ዓመት 110 (83%) ተማሪዎች እና ከ17-19 ዓመት 22 (17%) ተማሪዎች ነው።

4.2. የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አጠቃላይ መረጃ

አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ከሚባሉት አንዱ የንባብ ክሂል ነው። ይህ በትምህርትነት መሰጠቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ከጠቀሜታዎችም አንዱ ንባብን በሚያነቡበት ጊዜ የንባብ ችሎታቸውን ማዳበር ማስቻሉ ነው። ከዚህም ሌላ ለሌሎቹም ክሂሎች መሠረት እንዲጥሉና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ንባብ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። በዚሁ መሰረት የንባብ ክሂል በክፍል ውስጥ ስለመሰጠቱ ለመምህራን ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ የሚከተለው ነው።

ሠንጠረዥ ሶስት፡- ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	ሀ		ለ	
		አዎ ይሰጣል		አይሰጥም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.1	በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ይሰጣል።	6	100%	0	0%

በሠንጠረዥ ሶስት ላይ እንደተመለከተው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ስለመሰጠቱ ለቀረበው ጥያቄ 6ቱም (100%) መምህራን የሰጡት ምላሽ "አዎ ይሰጣል፤" የሚል ነው። መምህራኑ እንዳሉትም የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲሰጥ በተደረጉት ምልከታዎች ለማስተዋል ተችሏል። ስለዚህ የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ ይሰጣል። በተመሳሳይም ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው ምላሽ የሚከተለው ነው።

ሠንጠረዥ አራት፡- ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ

ተ.ቁ	ጥያቄ	ሀ		ለ	
		አዎ ይሰጣል		አይሰጥም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.1	በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ይሰጣል።	128	97%	4	3%

በሠንጠረዥ አራት እንደተመለከተው በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንባብ ትምህርት ይሰጥ እንደሆነ ለማወቅ ለተማሪዎች በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት 128(97%) ተማሪዎች አዎ ይሰጣል፤ 4(3%) ተማሪዎች አይሰጥም፤ በማለት መልሰዋል። ይህም ምላሽ የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ መሰጠቱን ያስገነዝባል። ከመምህራኑም ከተገኘው ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይሁንና 4(3%) ተማሪዎች የንባብ ትምህርት አይሰጥም ያሉትን፤ በክፍል ሶስት እና አራት ለተካተቱት ለቀሪዎቹ መጠይቆች በተገቢው ሁኔታ መረጃ በመስጠታቸው ነው። በመጠይቆቹ የቀረቡ ጥያቄዎች የንባብ ትምህርት አሰጣጥን የሚመለከቱ በመሆናቸው ለመጠይቆቹ መረጃ በመስጠታቸው የንባብ ትምህርት ይሰጣል ብለው ከመለሱት ጋር ተመሳሳይ ናቸው ለማለት ይቻላል። በመሆኑም ከመምህራኑና ከተማሪዎች መጠይቆች ከተገኙ መረጃዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው የንባብ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ይሰጣል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

ከላይ እንደተገለጸው የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ይሰጣል፤ ትምህርቱ ሲሰጥ ደግሞ ተማሪዎች ለመከታተል ያላቸውን የፍላጎት ደረጃ ለማወቅ በቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አምስት፡- የተማሪዎችን ንባብ የመማር ፍላጎት በተመለከተ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄ	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መጠነኛ		ዝቅተኛ	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.2	ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ፍላጎታቸው ምን ያህል ነው።	0	0%	2	33.3%	4	66.7%	0	0%

የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት የመማር ፍላጎት ደረጃ በተመለከተ (በሠንጠረዥ አምስት) እንደተገለጸው 2 (33%) መምህራን ከፍተኛ፤ 4 (67%) መምህራን ደግሞ መጠነኛ

ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል። ከምላሾቹ ውስጥ በጣም ከፍተኛ እና ዝቅተኛ በማለት ምላሽ የሰጠ የለም። ከዚህ ምላሽም በመምህራኑ እይታ የተማሪዎች የፍላጎት ደረጃ መጠነኛ ነው ማለት ይቻላል። ተማሪዎች በበኩላቸው የሰጡት ምላሽ ደግሞ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ስድስት፡- የተማሪዎችን ንባብ የመማር ፍላጎት በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄ	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		በጣም ከፍተኛ		ከፍተኛ		መጠነኛ		ዝቅተኛ	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.3	በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለመከታተል ያለህ/ሽ ፍላጎት ደረጃ ምን ያህል ነው?	68	51%	43	33%	18	14%	3	2%

ተማሪዎች የንባብ ትምህርት ለመከታተል ያላቸው ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ በቀረበላቸው መጠይቅ 68 (51%) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ፣ 43 (33%) ተማሪዎች ከፍተኛ 18 (14%) ተማሪዎች መጠነኛ፣ 3 (2%) ተማሪዎች ደግሞ ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ስድስቱም መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም።

68 (51%) ተማሪዎች የሰጡት ምለሽ በጣም ከፍተኛ የሚል ሲሆን ይህ ደረጃ በ6ቱም መምህራን አልተመረጠም። ይህ መረጃ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር መምህሩ የተማሪዎችን የፍላጎት ደረጃ በወጉ አልተረዱም ወይም ደግሞ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የተጋነነ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም በምልከታ ወቅት እንደታየው አብዛኞቹ ተማሪዎች ትምህርቱን ሲከታተሉ የነበረው በጸጥታና በእርጋታ አልነበረም። ብዙን ጊዜ ሀላፊነቱ ንባብን በጮክታ በሚያነበው ተማሪና በመምህሩ/ሯ ተወስኖ ነበር። በመሆኑም ሌሎቹ ተማሪዎች ስለማያዳምጡ መምህሩ/ሯ ጠረጴዛ በማንኳኳት፣ "ዝም በሉ" በማለት ጊዜያቸውን ሲያባክኑ ለማስተዋል ተችሏል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ከመምህራን ሃላፊነቶች አንዱ ተስማሚ የመማስተማሪያ ሞዴሎችን በመጠቀም የተማሪውን የፍላጎት ደረጃ ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ነው። ቢሆንም መምህራኑ ይህን ለማከናወን የሚገጥሟቸው ችግሮች እንዳሉ በጽሑፍ መጠይቁ 4.1 ተጠይቀው ከገለጿቸው ችግሮች መካከል ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ ዝቅተኝነት፣ ከተወሰኑ ተማሪዎች በስተቀር ለማንበብ ፍላጎት ማጣት እና የመማሪያ መጽሐፋቸውን ይዘው

አለመምጣት የሚሉት ይገኝባቸዋል። ስለዚህ ተማሪዎቹ በጣም ከፍተኛ ፍላጎት አለን ብለው የሰጡት መልስ ከምልከታውም ሆነ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ባለመገኘቱ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው ብሎ ለማጠቃለል አያስደፍርም።

የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት ለማሳደግ መምህራን የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ፅሑፍ ወሳኝነት እንዳለው በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። ከመምህራን ሀላፊነት አንዱ ተስማሚ ምንባብ በመምረጥ ተስማሚ የሆነ መልመጃ ማዘጋጀት ነው። በተጨማሪም Celce-Marcia (1991:20) እንደገለጹት መምህሩ አጋዥ የሆኑ ጽሑፎችን ከታወቁ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና የታተሙ ጽሑፎች በማስተማሪያነት በመጠቀም ተማሪዎችን ከእውናዊ አለም ጋር ማዛመድ ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ሁኔታ መምህራኑ ያከናውኑ እንደሆነ ለማወቅ በቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ ሰባት፡-የማስተማሪያ ጽሑፍን በተመለከተ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ

ሀ. የመማሪያ መጽሐፍ
ለ. በመጽሔት የሚታተሙ ወቅታዊ ጽሑፎች
ሐ. ጋዜጣ
መ. የራስን ጽሑፍ በማዘጋጀት

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	አማራጮች	ብዛት	መቶኛ
2.4	የአማርኛ ቋንቋ ንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ጽሑፍ ምንጭ የትኛው ነው? (ከአንድ በላይ መምረጥ ይቻላል።)	ሀ	3	50%
		ሀ ና ለ	1	16.7%
		ሀ ና ሐ	1	16.7%
		ሀ፣ለ፣ሐ ና መ	1	16.7%

የንባብ ማስተማሪያ ጽሑፍ ምንጭን በሚመለከት ከመምህራኑ የተገኘው ምላሽ 3 (50%) መምህራን የመማሪያ መጽሐፍ ብቻ ይጠቀማሉ፤ 1 (16.7%) መምህር መማሪያ መጽሐፍና መጽሔት የሚታተሙ ወቅታዊ ጽሑፎችን ይገለገላሉ፤ 1(16.7%) መምህር የመማሪያ መጽሐፍ እና በመጽሔት የሚወጡ ጽሑፎችን ይጠቀማሉ፤ 1 (16.7%) መምህር የመማሪያ መጽሐፍ፣ በጋዜጣና መጽሔት የሚታተሙ ወቅታዊ ጽሑፎች ጋዜጣ እና የራስን ጽሑፍ በማዘጋጀት የንባብን ትምህርት ይሰጣሉ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው 3 (50%) መምህራን የመማሪያ መጽሐፍን ብቻ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ሶስት መምህራን የመማሪያ መጽሐፍንና ተጨማሪ የማስተማሪያ ጽሑፎችን እንደሚጠቀሙ ነው። ይህንኑ በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ስምንት፡- የማስተማሪያ ጽሑፍን በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ

ሀ. የመማሪያ መጽሐፍ ለ. በመጽሔት የሚታተሙ ወቅታዊ ጽሑፎች

ሐ. ጋዜጣ መ. የራስን ጽሑፍ በማዘጋጀት

ተ.ቁ	ጥያቄ	አማራጮች	ብዛት	መቶኛ
2.2	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የንባብ ትምህርት ለማስተማር የሚጠቀሙበት የጽሑፍ ምንጭ የትኛው ነው?	ሀ	64	48.6%
		ሀ ና ለ	13	10%
		ሀ ና ሐ	4	3%
		ሀ ና መ	41	31%
		ሀ ፣ ለ ፣ ሐ ና መ	5	3.7%
		ሀ ፣ ለ ና መ	5	3.7%

ከሠንጠረዥ ስምንት መረዳት እንደሚቻለው 64 (48.6%) ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፉን ብቻ ይጠቀማሉ በማለት መልሰዋል። 13 (10%) ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ እና በመጽሔት የሚታተሙ ወቅታዊ ጽሑፎች ይጠቀማሉ፣ 4(3%) ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍና ጋዜጣ፣41(31%) ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍና የራሳቸውን ጽሑፍ ይጠቀማሉ፣ 5 (3.7%) ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ፣ በመጽሔት የሚታተሙ ወቅታዊ ጽሑፎች እና የራሳቸውን ጽሑፍ በማዘጋጀት ይጠቀማሉ 5 (3.7%) ተማሪዎች ደግሞ ሁሉንም የጽሑፍ ምንጮች በመጠቀም ትምህርቱን ይሰጣሉ የሚል ምላሽ ሰጠዋል። ይሁን እንጂ ግማሽ ያህሉ ደግሞ የመማሪያ መጽሐፉን ብቻ መጠቀማቸው ተማሪዎችን ከእውኑ አለምና ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር እንዳይተዋወቁና ተምህርቱን የህይወታቸው ጋር ለማዛመድ እንዳይችሉ ያደርጋል። ስለዚህ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ ሌሎች አጋዥ መጻሕፍትን መጠቀሙ ተመራጭ ነው።

ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ ጋር ተመሳሳይነት አለው። የመማሪያ መጽሐፍን ብቻ እንዲጠቀሙ 3 (50%) መምህራን የገለጹ ሲሆን እንዲሁ 64 (48.6%) ተማሪዎች ይህንኑ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚህ መረጃ ማጠቃለል የሚቻለው ግማሽ ያህሉን መምህራን የመማሪያ መጽሐፉንና ሌሎች አጋዥ መጻሕፍትን ለማስተማሪያነት እንደሚገለገሉበት ነው። ይሁን እንጂ ግማሽ ያህሉ ደግሞ የመማሪያ መጽሐፍን ብቻ መጠቀማቸው ተማሪዎችን ከእውኑ አለምና ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር እንዳይተዋወቁ ትምህርቱን ከህይወታቸው ጋር ለማዛመድ እንዳይችሉ ያደርጋል። ስለዚህ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ ሌሎች አጋዥ መጻሕፍትን መጠቀሙ ተመራጭ ነው። ይህም ሁኔታ ተማሪዎች ከእውኑ አለም እንዲተዋወቁ እገዛ ያደርግላቸዋል።

ቀደም ብሎ መምህራኑ ለማስተማሪያነት የሚጠቀሙበት ጽሑፍ ምንጭ ምን እንደሆነ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ገሚሱን በመማሪያ መጽሐፍ ብቻ፣ ገሚሱ ደግሞ ከመማሪያ መጽሐፍ በተጨማሪም ልዩ ልዩ የጽሑፍ ምንጮችን መጠቀማቸው ተገልጿል። በተጨማሪም የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ከመማሪያ መጽሐፉ መልመጃ ውጭ የራሳቸውን ተጨማሪ ጥያቄዎች ያዘጋጁ ወይም አዘጋጁ እንደሆነ ለማወቅ ለተጠየቁት ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ ዘጠኝ ፡- መልመጃዎችን በተመለከተ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄ	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር አዘጋጃለሁ		አብዛኛውን ጊዜ አዘጋጃለሁ		አልፎ አልፎ አዘጋጃለሁ		ፈፅሞ አላዘጋጅም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.5	የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ ከመማሪያ መጽሐፉ መልመጃ ውጭ የራስዎን ተጨማሪ ጥያቄዎች ያዘጋጃሉ።	1	16.7%	2	33.3%	3	50%	0	0%

ከላይ በሠንጠረዥ ዘጠኝ እንደተገለጸው ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ መልመጃዎችን ማዘጋጀት አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት 2 (33.3%) መምህራን ሲሆኑ አልፎ አልፎ ደግሞ የሚጠቀሙት 3 (50%) መምህራን ናቸው። 1 መምህር ደግሞ ዘወትር እንደሚያዘጋጁ ገልጸዋል። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በተለያየ ደረጃም ቢሆን መምህራኑ የራሳቸውን ተጨማሪ ጥያቄዎች በማዘጋጀት ያስተምራሉ። ይሁን እንጂ ከክፍል ምልከታው እንደተረዳነው ይህን ሲተገብሩ የታዩት አንድ መምህር ብቻ ናቸው። አብዛኛዎቹ መምህራን አንዳንድ ጥያቄዎችን ቢያቀርቡም ተዘጋጅተው ሳይሆን በአጋጣሚ የሚሰነዝሯቸው ጥያቄዎች ነበሩ። ስለዚህ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ያዘጋጃሉ ለማለት አያስደፍርም።

4.3 የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው የንባብ የትምህርት በዘመናዊ መንገድ ሲሰጥ ሶስት የማቅረብያ ደረጃዎችን ሊከተል ይገባል። እነዚህም ደረጃዎች የቅድመ ንባብ፣ ጊዜ ንባብና ድህረ ንባብ ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ ሶስቱ የንባብ ደረጃዎች ከተሰበሰቡት መረጃዎች አንጻር በቅደም ተከተል በዝርዝር ተተንትነው ቀርበዋል።

4.3.1 ቅድመ-ንባብ ደረጃ

4.3.1.1 በቅድመ-ንባብ ደረጃ መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት

ቅድመ-ንባብ ደረጃ መምህራን ተማሪዎችን ለንባብ የሚያዘጋጁበት፣ ስሜታቸውን የሚያነቃቁበት፣ ትኩረታቸው ወደሚቀርበው ንባብ እንዲሆን የሚያደርጉበት ነው። በተጨማሪም መምህራን የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎችን በቡድንና (በጥንድ) አደራጅተው ማወያየት ይጠበቅባቸዋል። ይህን በተመለከተ ተጠኝ መምህራኑ ያከናወኑትን ተግባር ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የሚከተለውን ለማስተዋል ተችሏል።

ሠንጠረዥ አስር፡- የንባብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ

ተ.ቁ	የክፍል ውስጥ አቀራረብ	ተከናውኗል		አልተከናወነም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
1.1	ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት አሳውቀዋል።	5	83 %	1	17 %
1.2	ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲኖራቸው ጥረት አድርገዋል።	6	100 %	0	0 %
1.3	ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያይዙት አነቃቅተዋቸዋል።	6	100 %	0	0 %
1.4	የዕለቱን ርዕስ አስተዋውቀዋል።	6	100 %	0	0 %
1.6	ተማሪዎችን በቡድን አደራጅተው እንዲወያዩ አድርገዋል።	1	17 %	5	83 %
1.7	ተማሪዎች እንዲወያዩ አድርገዋል።	3	50 %	3	50 %

በሠንጠረዥ አስር በተ.ቁ 1.1 እንደቀረበው መምህራን በቅድመ-ንባብ ደረጃ ለተማሪዎቻቸው ንባብ የሚያነቡበትን ምክንያት ስለማሳወቃቸው በተደረገው ምልከታ በ5 (82.3%) መምህራን ተከናውኗል፤ በ 1 (16.7%) መምህር አልተከናወነም።

በሌላ በኩል በተራ ቁጥር 1.2 እንደተጠቆመው ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አድርገዋል ለሚለው 6ቱም (100%) መምህራን ተማሪዎች ስለንባብ ፍላጎት እንዲኖራቸው የበኩላቸውን እንቅስቃሴ አከናውነዋል። ይሁን እንጂ በምልከታው ወቅት እንደታየው ተማሪዎቹ የመምህራኑን ጥረት የተገነዘቡ አይመስልም። በመሆኑም አንዳንድ ክፍሎች ጫጫታ የበዛባቸው ነበሩ። መምህራንም ይህን ሁኔታ ለመቆጣጠርና ሀሳባቸው ወደ ንባብ ትምህርት እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ለመመልከት ተችሏል።

በጥያቄ ተ.ቁ 1.3 ለተመለከተው ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያይዙት ማነቃቃታቸውን በሚመለከት በተደረገው ምልከታ 6ቱም (100%) መምህራን

ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህም የንባብ ትምህርትን የተቃና ለማድረግ የተማሪዎች የቀደመ እውቀት አሁን ከሚማሩት ጋር በማያያዝ ማቅረብ በሁሉም መምህራን ተግባራዊ መደረጉን ያመለክታል።

እንዲሁም የዕለቱን ርዕስ በማስተዋወቅ ስለማቅረባቸው በምልከታው እንደታየው በ6ቱም (100%) መምህራን ተከናውኗል። ይህም መምህራኑ የዕለቱን ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎቻቸው በርዕሱ ዙሪያ ያላቸውን የቀደመ እውቀት ተጠቅመው ስለ ዕለቱ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ጥረት ማድረጋቸውን ያሳያል። ይሁንና በተ.ቁ 1.6 የቀረበው ተማሪዎችን በቡድን አደራጅቶ እንዲወያዩ የማድረግ ንዑስ ክሂል በ6ቱም (100%) መምህራን ሲከናወን አልታየም። ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀትና እንዲወያዩ ማድረግ ጠቀሜታ እንዳለው በክፍል ሁለት መገለጹ ይታወሳል። ይህም ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀትና እንዲወያዩ ማድረግ ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲወያዩ፣ ያላቸውን ሀሳብ እንዲሰጡ፣ የሌላውን እያመዛዘኑ እንዲቀበሉ እንዲሁም የራሳቸውን ሐሳብ ከሌላው ጋር እንዲያነጻጽሩ ከማድረጉም በላይ ሀሳቦቻቸው የተለያዩ እንኳን ቢሆኑ ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ ትክክለኛውን እንዲያረጋግጡ ዕድል ይሰጣቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ ተግባር በመምህራኑ ምንም ትኩረት አልተሰጠውም።

በተ.ቁ 1.7 ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩ አድርገዋል የሚለው በምልከታው እንደታየው በ3 (50%) መምህራን ሲተገበር፣ በ3 (50%) መምህራን አልተተገበረም። መረጃው የሚያመለክተው ግማሾቹ መምህራን አንጻር ተማሪዎቹን በማሳተፍ በቡድን እንዲወያዩ የማድረግ መሆኑን ከግማሾቹ መምህራን አንዳንዱ ደግሞ የትምህርት ሂደት የሚከናወነው በመምህሩ የበላይነት መሆኑን ነው። ከዚህ ጋር በተያየዘ ለመምህራን በቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራአንድ፡- የንባብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር እጠቀማለሁ		አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ		አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ		ፈፅሞ አልጠቀምም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
.1	ተማሪዎች ንባብ የሚያነቡበትን ምክንያት ያሳውቃሉ።	3	50%	2	33.3%	1	16.7%	0	0%
.2	ተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ጥረት ያደርጋሉ።	3	50%	3	50%	0	0%	0	0%
.3	የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋውቃሉ።	6	100%	0	0%	0	0%	0	0%
.5	ተማሪዎችን በቡድን ያደራጃሉ።	2	33.3%	1	16.7%	2	33.3%	1	16.7 %

ILS LIBRARY

ከላይ በሠንጠረዥ አስራአንድ እንደቀረበው መምህራን ለተማሪዎች ንባቡን ለምን ዓላማ እንደሚያነቡ ስለማሳወቃቸው ለቀረበው መጠይቅ 3 (50%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤1(16.7%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ከተሰጠው ምላሽ መረዳት የሚቻለው በተለያየ ደረጃ ይሁን እንጂ ምንባቡን የሚያነቡበትን ዓላማ ለተማሪዎቻቸው በማሳወቅ ትምህርቱን እንደሚጀምሩ ነው።

በቅድመ-ንባብ ከሚከናወነው ተግባር አንዱ ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማነቃቃት በመሆኑ ይህንን ስለማድረጋቸው በቀረበላቸው መጠይቅ 3 (50%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 3 (50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። እንዲሁም የትምህርቱን ርዕስ በማስተዋወቅ ዘወትር ትምህርቱን እንደሚጀምሩ 6ቱም (100%) መምህራን ዘወትር እንዲሚጠቀሙ ገልጸዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ሁሉም መምህራን የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ መጀመራቸውን እንዲም ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸውን ነው። ይህም በቪዲዩ ቀረጻ በታገዘው ተከታታይ ምልከታጋር የሚጣጣም ነው።

በሌላ በኩል ተማሪዎችን በቡድን የማደራጀት ተግባርን 2 (33.3%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%) መምህር አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%) መምህር ፈጽሞ አልጠቀምም፤ በማለት መልሰዋል። ሆኖም ይህ መረጃ በክፍል ምልከታ ከተገኘው መረጃ ይለያል። መምህራኑ የሰጡት ምላሽ ከምልከታው ጋር

የተጣጣመ ሆኖ አልተገኘም። ይህም የሚያሳየው መምህራኑ መረጃውን የሰጡት ምንአልባት ከክፍል ውጪ በቡድን ተደራጅተው እንዲያከናውኑ የሚሰጡትን ተግባራት በማስታወስ ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪም ተማሪዎችን እንዲወያዩ ስለማድረጋቸው 2 (33.3%) መምህራን ዘወትር ፤2 (33.3%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1(16.7%)መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%) መምህር ደግሞ ፈጽሞ አልጠቀምም፤ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም መረጃ ከክፍል ምልከታ ጋር መጠነኛ ልዩነት ያሳያል። በክፍል ምልከታ እንደታየው በ3 (50%) መምህራን ሲከናወን አልታየም፤ በመምህራኑ መጠይቅ እንደማያከናውኑ የገለጹት አንድ መምህር ብቻ ናቸው።ስለዚህ መምህራኑ የሰጡት መረጃ ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ተማሪዎች

እንዲወያዩ አድርገዋል ብሎ ማጠቃለል አይቻልም። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለተማሪዎች በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፡- የንባብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር ይጠቀማሉ		አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ		አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ		ፈፅሞ አይጠቀሙም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
1.1	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባብን የምትማሩበትን ዓላማ ያሳውቋችኋል።	41	31%	54	41%	31	24%	6	4%
1.2	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባብን የማንበበ ተነሳሽነት እንዲያድርባችሁ ያነቃቋችኋል።	64	48%	42	32%	23	18%	3	2%
1.3	የዕለቱን ምንባብ ርዕስ ያስተዋውቃሉ።	100	76%	22	16.5%	8	6%	2	1.5%
1.5	የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከንባብ ትምህርት በፊት በቡድን (በጥንድ)እንድትወያዩ ያደርጋሉ።	28	21%	24	18%	54	41%	26	20%

ከላይ በሠንጠረዥ አስራ ሁለት የቀረበው ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሲታይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባቡን የምትማሩበትን ዓላማ ያሳውቋችኋል ለሚለው 41 (31%) ተማሪዎች ዘወትር ፤ 54 (41%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ፤ 31 (24%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ፤ 6 (4%) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት መልሰዋል። ከዚህ መረጃም አብዛኞቹ መምህራን የምንባቡን አላማ ለተማሪዎቻቸው እንደሚያሳውቁ መገንዘብ ይቻላል። ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም ከክፍል ምልከታውም ሆነ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባብ የማንበብ ተነሳሽነት እንዲያድርባችሁ ያነቃቋችኋል፤ ለሚለው የጽሁፍ መጠይቅ 64 (48%) ተማሪዎች ዘወትር፤ 42 (32%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ፤ 23 (18%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 3 (2%) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን ትኩረት ሰጥተው ተማሪዎችን በማነቃቃት የንባብ ትምህርቱን መጀመራቸውን ነው። ይህም ከክፍል ምልከታው እና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙት መረጃዎች ጋር የተስማማ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ መምህራኑ የዕለቱን ምንባብ ርዕስ ያስተዋውቁ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ 100 (67%) ተማሪዎች ዘወትር፤ 22 (16.5%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 8 (6%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ፤ 2 (1.5%) ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አይጠቀሙም፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎች ለንባቡ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረጋቸውን ነው። ይህም ሁኔታ ተማሪዎች ስለሚያነቡት ምንባብ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው መረጃ ከምልከታውና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ጋር የተስማማ በመሆኑ ተጠኝ መምህራኑ በተገቢ ሁኔታ የምንባቡን ርዕስ በማስተዋወቅ ትምህርቱን ይጀምራሉ ለማለት ያስደፍራል።

የመምህራን ቅድመ-ንባብ ተግባር ከሆነው አንዱ ተማሪዎችን በቡድን (በጥንድ) ማደራጀት በመሆኑ ይህን ተግባራዊ ስለማድረጋቸው በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ 28 (21%) ተማሪዎች ዘወትር፤ 24(18%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ፤ 54(41%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ፤ 26(20%) ተማሪዎች ደግሞ ፈፅሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። በዚሁ ጉዳይ ላይ መምህራን የሰጡት ምላሽ ተቀራራቢነት አለው። ይሁንና በክፍል ምልከታ እንደተረጋገጠው ተማሪዎችን በቡድን (በጥንድ) ማደራጀት በተጠኝ መምህራኑ ምንም ትኩረት አልተሰጠውም።

የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ በመሆን የንባብ ትምህርትን መከታተል አለባቸው። ይህን ሁኔታ አስመልክተው መምህራኑ በቃለመጠይቁ እንደገለጹት ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ይዘው የሚመጡት ዝቅተኛ የንባብ ችሎታ ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። ስለዚህ ለዚህ ችግር እንደ አማራጭ መፍትሔ የወሰዱት ክክፍል ውጭ አንዳንድ በቡድን የሚያከናውኑት ተግባር መስጠት ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ የሚከናወነው ከመምህሩ ቁጥጥር ውጭ በመሆኑ የቡድን ሥራው ተከናውኗል ለማለት አያስደፍርም።

በጥቅሉ ሲታይ በቅድመ ንባብ ደረጃ መምህራን ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ተማሪዎች ምንባቡን የሚያነቡበትን ምክንያት ማሳወቅ፣ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ማድረግ፣የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ መጀመር፣ አዲስ የሚማሩትን ትምህርት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማያያዝ ማቅረብ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ ሲደረግ ተስተውሏል። በሌላ በኩል ተማሪዎችን በቡድን (በጥንድ) በማደራጀት ማወያየትና ተማሪዎችን ማወያየት በተገቢው ሁኔታ ያለመተግበራቸውን መገንዘብ ተችሏል።

4.3.1.2. በቅድመ-ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት

ተማሪዎች የንባብ ክሂል ማዳበር ይችሉ ዘንድ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ትኩረት መሰጠት እንዳለበት በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። በዚህ መሠረት በቅድመ-ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው የመገመት ችሎታና ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ናቸው። የመገመት ችሎታ ያላቸው አንባቢዎች ርዕሱን በማየት በምንባቡ ሂደት ውስጥ ምን ሊመጣ እንደሚችል ቀድሞ ግምት ይሰጣሉ። በንባቡ ሂደትም ከግምታቸው ጋር ምን ያህል እንደተጣጣመ በመመዘን የመገንዘብ ደረጃቸውን ያጠናክራሉ። እንዲሁም ለቁልፍ ቃላት ፍቺ በመስጠት የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ። እነዚህን ንዑስ ክሂሎች በተመለከተ ተጠኝ መምህራኑ የሰጡት ትኩረት የሚከተለውን ይመስላል።

ሠንጠረዥ አስራ ሶስት፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከክፍል ምልከታ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄ	ተከናውኗል		አልተከናወነም	
		ብዛት	በመቶኛ	ብዛት	በመቶኛ
1.5	በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል እንዲገምቱ አድርገዋል።	3	50%	3	50%
1.8	ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል።	4	66.6%	2	33.3%

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነሳ እንዲሚችል መገመትን በተመለከተ 3ቱ (50%) መምህራን ሲያከናውኑ፣ 3ቱ (50%) መምህራን አላከናወኑም። ይህም የሚያሳየው ለንዑስ የንባብ ክሂሉ ግማሾቹ መምህራን ትኩረት መስጠታቸውን ነው። ይሁንና ግማሾቹ (50%) ሲያውከናውኑ ባለመታየቱ በንዑስ ክሂሉ አተገባበር ረገድ ችግር እንዳለ ያሳያል ስለዚህ በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል በመገመት ማስተማር ንዑስ ክሂል በተጠኝ መምህራኑ ትኩረት አግኝቷል ማለት ይቻላል።

ለቁልፍ ቃላት ፍቺ የመስጠትንም ንዑስ የንባብ ክሂልን በተመለከተ በ4 (66.6%)መምህራን ተከናውኗል፤ በ 2 (33.3%) መምህራን አልተከናወነም። ከዚህ መረዳት የሚቻለውን ንዑስ የንባብ ክሂሉ በአብዛኞቹ መምህራን ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ነው። ሆኖም2 (33.3%) መምህራንም ቁጥር ቀላል የሚባል ስላልሆነ የንዑስ ክሂሉ አተገባበር ፈጽሞ ከችግር የጸዳ ነው ለማለት አያስደፍርም። ይህንኑ በተመለከተ ለመምህራን በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ በማነጻጸር ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራ አራት፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር እጠቀማለሁ		አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ		አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ		ፈፅሞ አልጠቀምም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
1.4	የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ከሚማሩት ጋር በማያያዝ እንዲገምቱ ያደርጋሉ።	3	50%	3	50%	0	0%	0	0%
1.7	ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ።	4	66.6%	1	16.7%	1	16.7%	0	0%

በሠንጠረዥ አስራ አራት እንደተመለከተው በቅድመ-ንባብ ደረጃ መዳበር ካለባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አንዱ በቅድመ-ንባብ የመገመት ችሎታ ነው። ይህን በተመለከተ ለመምህራኑ በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ 3 (50%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ ሲሉ 3 (50%) መምህራን ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ ብለዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠኝ መምህራን በከፍተኛ ደረጃ ለንዑስ ክሂሉ ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መሠረት አድርጎ አዲስ ከሚማሩትን ትምህርት ጋር በማያያዝ ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በሌላም በኩል በተወሰነ ደረጃ ስለሚያቁት ነገር በስፋትና በጥቀት እንዲመለከቱ ወይም ከሚያቁት ተነስተው ሌላ አዲስ ሀሳብ የመገንዘብ ችሎታ ለማዳበር ያስችላል። ይህንኑ ሁኔታ ተጠኝ መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው ማስተማራቸው ጥሩ ጎን አለው።

ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠትንም በተመለከተ 4 (66.6%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 1መምህር (16.7%) አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ መምህር (16.7%) ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። በቅድመ ንባብ ደረጃ ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት ተማሪዎች ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ቃላትን በማወቅ ሀሳቡን ለመረዳት የሚያስችላቸው በመሆኑ ይህንኑ ክሂል ተጠኝ መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው ማስተማራቸው ትልቅ ፋይዳ አለው። በተመሳሳይ መልኩ በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነገር እንደሚችል መገመት እና ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራ አምስት፡- ንዑሳን ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር ይጠቀማሉ		አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ		አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ		ፈጽሞ አይጠቀሙም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
1.4	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነገር እንደሚችል እንድትገምቱ ያደርጋሉ።	61	46.3%	37	28%	27	20.4 %	7	5.3%
1.6	ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ።	84	63.5%	31	23.5%	15	11.4 %	2	1.5%

በሠንጠረዥ አስራ አምስት እንደተመለከተው ተጠኝ መምህራኑ በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነገር እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ በማድረግ ስለማስተማራቸው 61(46.3%) ተማሪዎች ዘወትር፤ 37 (28%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ፤ 27(20.4%) ተማሪዎች ጊዜ፤ 7(5.3%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። በዚህ መረጃ አብዛኞቹ መምህራን ለንዑስ የንባብ ክሂሉ ትኩረት መስጠታቸውን ያመለክታል። ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም ከክፍል ምልከታውም ሆነ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ ተጠኝ መምህራኑ ለንዑስ የንባብ ክሂሉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተዋል ማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል ተጠኝ መምህራኑ ለቁልፍ ቃላት ፍቺ እንደሚሰጡ ለማወቅ በቀረበው መጠይቅ 84 (63.5%) ተማሪዎች ዘወትር ፣ 31 (23.5%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ፤15 (11.4%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ፤ 2 (.5%) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።ይህም አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ለንዑስ ክሂሉ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውን ያመለክታል። ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውም ንዑስ ክሂሉ በተገቢው ሁኔታ በተጠኝ መምህራኑ መተግበሩን ያሳያል።

በአጠቃላይ በቅድመ ንባብ ደረጃ በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነገር መቻልና ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት በተጠኝ መምህራኑ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠት አዲስ ለሚቀርብላቸው ምንባብ በቂ የሆነ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መነሻ ይዘው ዝርዝር ሀሳብን ለማግኘት የሚያነቡት ንባብ የተቃና እንዲሆን ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

4.3.2. ጊዜ-ንባብ ደረጃ

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ሁለተኛው ደረጃ ጊዜ-ንባብ ነው። በዚህ ደረጃ የሚከናወኑት ተግባራት የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት የሚያስችሉ ናቸው። በዚህ ረገድ መምህራን ስለሚያከናውኗቸው ተግባራትና ተማሪው ስለሚያዳብራቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ስለሚሰጣቸው ትኩረት ተተንትኖ ቀርቧል።

4.3.2.1. በጊዜ-ንባብ ደረጃ መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት

በጊዜ ንባብ ደረጃ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ለንባቡ ጊዜ ወስኖ በመስጠት ንባቡን እንዲያነቡ ማድረግና ተማሪዎች ለሚጠይቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ትምህርቱን ማጠናከር ናቸው። ለንባቡ ጊዜ ወስነው ስለመስጠታቸው የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

ሠንጠረዥ አስራ ስድስት፦ መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ተከናውኗል		አልተከናወነም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.3	ለንባቡ ጊዜ ወስነው (ደቂቃ ወስነው) ሰጥተዋል።	0	0%	6	100%
2.4	ለተጠየቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል።	4	66.6%	2	33.3%

በምልከታው የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ለንባቡ ጊዜ ወስኖ መስጠት በ6ቱም(100%) መምህራን አለመከናወኑን ያመለክታል። ይህም ለንባብ ጊዜ ወስኖ መስጠት በተጠኝ መምህራኑ ሙሉ በሙሉ ትኩረት ያልተሰጠው ንዑስ ክሂል መሆኑን መረጃው ያሳያል። ከመረጃውም በመነሳት ተጠኝ መምህራኑ ጊዜ ወስነው አለመስጠታቸው የሚያመለክተው የተለያዩ የንባብ አይነቶችን አለመጠቀማቸው ነው። ምክንያቱም ጊዜ ወስኖ የሚሰጠው ተማሪዎች ንባቡን በፍጥነት አንብበው ከምንባቡ የተወሰኑ መረጃዎችን በመፈለግ ለማውጣት እንዲችሉ ነው።

በሌላ በኩል ተጠኝ መምህራኑ ተማሪዎች ለጠየቁት ጥያቄ ምን ያህሉ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፤ ለሚለው በ4 (66.6%) መምህራን ተከናውኗል፣ በ2 (33.3%) መምህራን አልተከናወነም፤ ይህም

አብዛኞቹ መምህራን ለተጠየቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ ያመለክታል። ይሁንና 2ቱ (33.3%) መምህራን ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ አልታየም። ይህም ሁኔታ ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም መምህራን ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት ተማሪዎች በሚያነሱት ጥያቄ ላይ ተመስርተው በመሆኑ ነው። ከላይ የተገለጹትን ተግባራት በተመለከተ ከመምህራን የተገኘውን መረጃ በማያያዝ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራ ሰባት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር እጠቀማለሁ		አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ		አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ		ፈፅሞ አልጠቀምም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.1	ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ያስነብባሉ።	2	33.3%	2	33.2%	2	33.3%	0	0%
2.3	ራስዎ ንባቡን በማንበብ ተማሪዎች እንዲያዳምጡ ያደርጋሉ።	1	16.7%	3	50%	2	33.3%	0	0%
2.4	ለንባቡ ደቂቃ ወስነው በመስጠት ተማሪዎች እንዲያነቡ ያደርጋሉ።	0	0%	3	50%	2	33.3%	1	16.7%
2.5	ተማሪዎች ለሚጠይቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ።	5	83.3%	1	16.7%	0	0%	0	0%

ከሠንጠረዥ አስራ ሰባት 2.1 ላይ በቀረበው መረጃ ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ማስነበብን 2 (33.3%) መምህራን ዘወትር፤ 2 (33.3%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ፤ 2 (33.3%) መምህራን ደግሞ አንዳንድ ጊዜ፤ እያስነሱ እንደሚያስነብቡ ምላሽ ሰጥተዋል። ፈጽሞ አላስነብብም በማለት የመለሰ የለም። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በተለያየ ደረጃ ይሁን እንጂ ሁሉም መምህራን ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ማስነበብ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ነው።

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው በሁለተኛ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የጮክታ ንባብ የሚደገፍ አይደለም። ምክንያቱም ንባብ ግላዊና አእምሯዊ ተግባር በመሆኑ ንባብን በዝምታ የማንበብ ችሎታ ሊያዳበሩ ይገባል።ስለዚህ መምህራኑ ይህን ተገንዝበው ተማሪዎች ንባብን በግላቸው እንዲያከናውኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። ይሁን እንጂ ይህን ተግባር መምህራኑ ሲተገብሩ አልታዩም።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ በተ.ቁ. 2.3 ለተመለከተው መጠይቅ ራስዎ በማንበብ ተማሪዎች እንዲያዳምጡ ያደርጋሉ፤ ለሚለው 1(16.7%) መምህር ዘወትር፤ 3(50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ፤ 2(33.3%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ፤እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ ፈጽሞ አልጠቀምም የሚል ምላሽ የሰጠ ሰው የለም። ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው መምህራን የሚጠቀሙበት ንባብን የማቅረቢያ መንገድ ዘመናዊ ማለትም ተማሪ ተኮር አለመሆኑን ነው።

ለንባቡ ደቂቃ ወስነው በመስጠት ተማሪዎች እንዲያነቡ ያደርጋሉ? ለሚለው ጥያቄ 3 (50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፣ 2 (33.3%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፣1 (16.7) መምህር ፈፅሞ አልጠቀምም፤ በማለት መልሰዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን ለንባብ ጊዜ ወስነው እንደሚሰጡ ነው። ይሁንና በምልከታው ጊዜ ወስነው በመስጠት ተማሪዎችን ሲያስነብቡ አልታየም፤ እንዲያውም አብዛኛውን ንባብ ራሳቸው በማንበብ እንዳቀረቡት ለማስተዋል ተችሏል። ይህንኑ ሁኔታ በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራ ስምንት፡-መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር ይጠቀማሉ		አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ		አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ		ፈጽሞ አይጠቀምም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.2	ምንባቡን ስታከናውኑ ደቂቃ ወስነው ይሰጣሉ።	45	34%	24	18%	37	28%	26	20%
2.8	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ በመስጠት ያስተካክላሉ።	95	73%	29	22%	5	3%	3	2%

ከሠንጠረዥ አስራ ስምንት መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ምንባቡን ሲያከናውኑ መምህሩ ደቂቃ ወስነው ስለመስጠታቸው ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ 45 (34%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 24(18%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 37 (28%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 26 (20%) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ የሚል ነው። መረጃው እንደሚያሳየው አብዛኞቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ መምህራኑ ለንባቡ ጊዜ ወስነው ይሰጣሉ

የሚል ነው። ነገር ግን በክፍል ምልከታው እንደታየው ይህ ተግባራዊ ሲደረግ አልተስተዋለም። ይህን ሁኔታ የገለጹት ግን 26 (20%) ተማሪዎች ብቻ ናቸው።

ከዚህም ሌላ የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ ይሰጡ እንደሆነ ለማወቅ በቀረበው መጠይቅ 95 (73%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 29 (22%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 5 (3%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 3 (2%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ከተማሪዎቹ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች በከፍተኛ ደረጃ ከመምህራቸው ምላሽ የሚሰጣቸው መሆኑን ነው። ይህም ሁኔታ በክፍል ምልከታውም ሆነ ከመምህራን መጠይቅ መረጃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በጥቅሉ ሲታይ ከክፍል ምልከታው፣ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ተጠኝ መምህራኑ በክፍል ውስጥ ምንባብን የሚያቀርቡበት መንገድ በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው የሚደገፍ አይደለም። ምክንያቱም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምንባብን በጮክታ ንባብ (ድምጽን በማውጣት) የሚያነቡ ከሆነ ለብዙ ተማሪዎች የማንበብ ዕድል አይሰጥም። እንዲሁም የንባብ ንዑሳን ክሂሎች የሆኑትን እንደ የአሰሳ ንባብ ወይም የገረፍታ ንባብ ተግባራዊ ለማድረግ አያስችልም። ስለዚህ አንድ ተማሪ ወይም መምህሩ የሚያነቡትን በማዳመጥ ይወሰናሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ የተማሪዎች የንባብ ልምድ እንዳይዳብር ትልቅ እንቅፋት መሆኑ የማይካድ ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መምህራን በስልጠና ወቅት ስለ ክሂሎች (የንባብ ክሂል) ማስተማሪያ ዘዴ በበቂ ሁኔታ ስልጠና አግኝቻለሁ ብለው ያስባሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ሲመልሱ 2 መምህራን በቂ ነው ብለው ሲመልሱ፣ 4 መምህራን በቂ ነው ብለው አያስቡም። ስለዚህም ምክንያታቸውን ሲገልጹ አራቱን ክሂሎች በደፈናው በአንድ ላይ የማቅረብ ሁኔታ ስለአለ ስለ እያንዳንዱ ክሂል በተናጠል በቂ ግንዛቤ መጨበጥ አይቻልም ብለዋል። በተጨማሪም ቀደም ብሎ ስልጠና የወሰዱ መምህራን ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በቅርብ እንደማያውቋቸውና የማሻሻያ ስልጠና ቢያገኙ መልካም እንደሆነ ሀሳብ ሰጥተዋል።

4.3.2.2 በጊዜ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው በጊዜ-ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የአሰሳ ንባብ፣ የገረፍታ ንባብ፣ ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅዕ መመላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን

በሰንጠረዥ መመላት፣ የዝምታ ንባብ፣ ከንባቡ ዝርዝር መረጃን ማውጣት፣ የጽሑፉን አዳረጃጀት መረዳት እና የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር መገመት ችሎታ ናቸው። እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በተመለከተ መምህራን የሚሰጡትን ትኩረት በሚከተለው ሁኔታ በዝርዝር ቀርቧል።

ሠንጠረዥ አስራ ዘጠኝ፡- ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በተመለከተ ከክፍል ምልከታው የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ተከናውኗል		አልተከናወነም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.1	ጥያቄዎችን በመስጠት የአሰሳ ንባብ እንዲያከናውኑ አድርገዋል።	0	0%	6	100%
2.2	መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ አድርገዋል።	0	0%	6	100%
2.5	ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽ መመላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መመላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድርገዋል።	0	0%	6	100%
2.6	ንባብን በዝምታ ንባብ እንዲያነቡ አድርገዋል።	0	0%	6	100%
2.7	ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል።	2	33.3%	4	66.6%
2.8	ተማሪዎች የጽሁፉን አደረጃጀት መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል።	2	33.3%	4	66.6%
2.9	የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ አድርገዋል።	6	100%	0	0%

ሠንጠረዥ አስራ ዘጠኝ እንደቀረበው ጥያቄዎችን በመስጠት የአሰሳ ንባብ እንዲከናወን አድርገዋል? በሚለው ረገድ በ6ቱም (100%) መምህራን አልተከናወነም። ይህም መረጃ የአሰሳ ንባብ በመምህራኑ ምንም ትኩረት እንዳልተሰጠው ያመለክታል።

የአሰሳ ንባብ የተወሰኑ መረጃዎችን ከምንባቡ ለማግኘት የሚደረግ ንባብ ሲሆን ይህን ችሎታ ለማዳበር መምህራኑ ምንም ያደረጉት ጥረት አለመኖሩ ደግሞ ተማሪዎች ተፈላጊ መረጃዎችን ለይቶ የማውጣት ችሎታ እንዳያዳብሩ ያደርጋቸዋል።

በሠንጠረዡ ተራ ቁጥር 2.2 እንደተመለከተው መረጃዎችን ለይቶ በማውጣት የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ ያደርጉ እንደሆነ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ በ6ቱም (100%) መምህራን አልተከናወነም። ይህም የሚያመለክተው ተጠኝ መምህራኑ ለገረፍታ ንባብ ትኩረት የነፈጉ

መሆናቸውን ነው። የገረፍታ ንባብ የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት የሚደረግ የፍጥነት ንባብ ነው። በዚህ የንባብ ሂደትም የአንቀጽን ዐ.ነገር ለይቶ ለማውጣት የምንባቡን ሀሳብ ለማግኘት የሚካሄድ ንባብ ነው። ይህም አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ከፍ የሚያደርግ ነው። ይሁንና ተጠኝ መምህራኑ ይህን ጠቃሚ ክሂል ተግባራዊ ሲያደርጉ አልተስተዋለም።

በሠንጠረዥ አስራ ዘጠኝ ተ.ቁ. 2.5 እንደተመለከተው ስዕልን ማገናዘብ ወይንም ቅጽ መሙላት ወይንም ዝርዝር ጉዳዩችን በሰንጠረዥ መሙላት የመሳሳሉ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረጋቸውን በተመለከተ 6ቱም(100%) መምህራን አለማከናወናቸውን በምልከታው ጊዜ ለማስተዋል ተችሏል። ይህም ንዑስ የንባብ ክሂሉ ምንም ትኩረት እንዳልተሰጠው ያመለክታል።

ተማሪዎች ጥልቅ ንባብ በሚያካሂዱበት ጊዜ ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅፅ መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዩችን በሰንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን መስጠት እንደሚቻል በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። ይሁን እንጂ ተጠኝ መምህራኑ ይህን ጠቃሚ የሆነ ንዑስ ክሂል ተማሪዎች እንዲያዳብሩ ያደረጉት ጥረት አልታየም።

ንባብን በዝምታ ንባብ እንዲያነቡ ስለማድረጋቸው በተደረገው ምልከታ በ6ቱም (100%) መምህራን አለመተግበሩን ለማየት ተችሏል። ነገር ግን በቪዲዮ ቀረጻ እንደታየው አንድ መምህር ለመተግበር ሞክረው ነበር። ይህም የተከናወነው ተማሪዎች የሚያነቡትን የተባዛ ፅሁፍ ለማዳረስ ተብሎ የታሰበ ይመስላል። ተማሪዎች ንባቡን በዝምታ ካነበቡ በኋላ እንደገና በአራት ተማሪዎች በጮክታ ንባብ እንዲቀርብ በማድረጋቸው የዝምታ ንባብ ተግባራዊ ሆኖአል ለማለት አያስደፍርም።

የዝምታ ንባብ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በጣም ጠቃሚ የሆነ ሊያዳብሩት የሚገባ ክሂል ሆኖ ሳለ ተጠኝ መምህራኑ የሰጡት ምንም ትኩረት እንደሌለ መገንዘብ ተችሏል። ምሁራን እንዳሉት ንባብ በጽሑፍ የቀረበን መልዕክት የመረዳት ሂደት በመሆኑ አንባቢው በግሉ የሚያከናውነው ተግባር ነው።ይህን ክሂል ለተማሪዎች የማለማመዱ ተግባር ግን በመምህራኑ ሲተገበር አልታየም።

ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል ለሚለው በ2.7 ለተመለከተው በምልከታ ወቅት በተገኘው መረጃ መሠረት በ2 (33.3%) መምህራን ተግባራዊ ሲያደርጉ ቀሪዎቹ 4 (66.6%) በመምህራን ግን ተግባራዊ ሲያደርጉ አልታየም። ይህም የሚያሳየው ከንባቡ ዝርዝር መረጃን ማውጣት የሚለው ንዑስ ክሂል የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑንና በአብዛኞቹ መምህራን ሲተገበር አለመታየቱ ነው። ከንባቡ ዝርዝር መረጃን ለማግኘት ንባብ በሚካሄድበት ጊዜ

የደራሲውን ስሜት ምን እንደሆነ እና ሌሎችም በዝርዝር የቀረቡ መረጃዎችን ለማግኘት የሚደረግ ንባብ ነው። ይህን አይነቱን ጠቃሚ የንባብ ሂደት በአብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን በወጉ ሲተገብሩ አልታየም።

በሠንጠረዥ አስራ ዘጠኝ ተ.ቁ 2.8 ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የጽሑፉን አደረጃጀት መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ስለማረጋገጣቸው በተደረገው ምልከታ 2 (33.3%) መምህራን አከናውነዋል፤ 4(66.7%) መምህራን አላከናወኑም። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የጽሑፉን አደረጃጀት መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ የማረጋገጥ ተግባር በአብዛኞቹ መምህራን አለመተግበሩንና የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ነው።

በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን አደረጃጀት መረዳት በጣም አስፈላጊ መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። ይህም ከዐረፍተ ነገር አንስቶ ጽሑፉ እንዴት እንደተዋቀረና ለማዋቀርም በጥቅም ላይ የዋሉ አያያገሮችን አጠቃቀም ለማወቅ ይረዳል። የንዑስ ክሂሉ መዳበር አስፈላጊነትም በተዘዋዋሪ የቀረቡ አገላለጾችን ተገንዝቦ ጽሑፉን ለመረዳት ስለሚያስችል ነው። ይህን ሁኔታ በመገንዘብ ተጠኝ መምህራኑ ያከናወኑት ተግባር አነስተኛ መሆኑን ተመልክቷል።

በሠንጠረዥ አስራ ዘጠኝ በተራቁጥር 2.9 እንደተመለከተው የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ በማድረግ ረገድ በምልከታ እንደታየው 6ቱም (100%) መምህራን ተግባራዊ ሲያደርጉ ለማስተዋል ተችሏል። ይህም ሁሉም ተጠኝ መምህራን ለንዑስ የንባብ ክሂሉ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውን ያሳያል።

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው ያልተለመዱ ቃላትን ፍቺ ከአውድ መረዳት መቻል ጥሩ አንባቢ ከሚኖረው ችሎታ አንዱ ነው። ይህም ያልተለመዱ ቃላት ሲያጋጥሙ ትርጉማቸውን መረዳት መዳበር ያለበት ችሎታ ነው። ይህን ችሎታ ተጠኝ መምህራኑ ሁሉም ሲተገብሩት ለማየት ተችሏል። ስለዚህ ያልተለመዱ ቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር የመገመት ችሎታ መዳበር በመምህራኑ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከላይ ከተገለፀው ሀሳብ ጋር በተያያዘ ተጠኝ መምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ መምህራኑ አዘውትረው የሚጠቀሙት የትኞቹን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች እንደሆነ ተጠይቀው 5ቱ (83%) መምህራን ለቃላትና ሐረጋት ፍቺ ከአውድ አንጻር መገመት በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ሰጥተው እንደሚያስተምሩ ገልጸዋል። ለዚህም እንደ ምክንያት የሰጡት ተማሪዎችን ስለሚከብዳቸውና ጥያቄ የሚያነሱት በዚህ ዙሪያ በመሆኑ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መምህራን በቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ በማነፃፀር ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሃያ፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ስለሚሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ይዘት	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር እጠቀማለሁ		አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ		አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ		ፈጽሞ አልጠቀምም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.2	ጥያቄዎችን በመስጠት (ከ2-3) የአሰሳ ወይም የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ።	0	0%	1	16.7%	4	66.6%	1	16.7%
2.6	ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መመላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መመላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን ተማሪዎች እንዲሰሩ ያደርጋሉ።	1	16.7%	1	16.7%	3	50%	1	16.7%
2.7	ተማሪዎች ንባቡን በዝምታ ንባብ እንዲያነቡ ያደርጋሉ።	0	0%	1	16.7%	3	50%	2	33.3%
2.8	ተማሪዎች ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ ያደርጋሉ።	0	0%	3	50%	2	33.3%	1	16.7%
2.9	ተማሪዎች የጽሑፉን አደረጃጀት እንዲናገሩ ያደርጋሉ።	2	33.3%	2	33.3%	2	33.3%	0	0%
2.10	ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ ያደርጋሉ።	4	66.6%	1	16.7%	1	16.7%	0	0%

ከሠንጠረዥ ሃያ መረዳት እንደሚቻለው ጥያቄዎችን በመስጠት የአሰሳ ወይም የገረፍታ ንባብ ያከናውኑ እንደሆነ ለተጠየቁት ጥያቄ 1(16.7%) መምህር አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 4 (66.6%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፣ 1(16.7%) መምህር ፈፅሞ አልጠቀምም፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። አብዛኞቹ መምህራን አንዳንድ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የሰጡት መረጃ በክፍል ምልከታ ከታየው ጋር የሚቃረን ሆኖ ነው የታየው። ፈጽሞ አለመጠቀማቸውን የገለጹት አንድ መምህር ብቻ ናቸው።

ሌላው ንዑስ የንባብ ክሂል ስዕልን ማገናዘብ ወይንም ቅጽን መመላት ወይንም ዝርዝር ጉዳዮችን በሠንጠረዥ መመላት የመሳሰሉትን መልመጃዎች ተማሪዎችን ስለማሰራታቸው ለቀረበላቸው መጠይቅ 1 (16.7%) መምህር ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%) መምህር አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 3(50%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%) መምህር ፈጽሞ አልጠቀምም፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። አብዛኞቹ መምህራን በሰጡት መረጃ ንዑስ ክሂሉን አንዳንድ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ነው። ይሁን እንጂ ይህ በክፍል ውስጥ ምልከታው

እንደታየው አንድም መምህር ሲተገብረው አልታየም። ስለዚህ በአብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ለንዑስ ክሂሉ ምንም የተሰጠው ትኩረት የለም ለማለት ያስደፍራል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎች የዝምታ ንባብ እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ? ለሚለው ምላሽ ሲሰጡ 1 (16.7%) መምህር አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 3 (50%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3) መምህራን በፍጹም አልጠቀምም በማለት መልሰዋል። ከመረጃው መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን የዝምታ ንባብን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ነው። ይሁን እንጂ በክፍል ምልከታው እንደታየውም ሆነ በሠንጠረዥ አስራ አምስት እንደተገለጸው አብዛኞቹ መምህራን ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነበብ ወይም ራሳቸው ንባቡን በማንበብ ትምህርቱን እንደሚያቀርቡ ከሰጡት መረጃ ጋር የሚፋለስ ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚሁ ሀሳብ ሳንወጣ በመጠይቁ ክፍት ጥያቄ ቁጥር 4.1 ተጠኝ መምህራኑ በሰጡት ምላሽ ተማሪዎችን በዝምታ ንባብ ለማስነበብ ሞክረው ምንም ውጤት ሳያገኙ በመቅረታቸው ጊዜ ለመቆጠብ ሲባል ራሳቸው መምህሩ አንብበው ወይንም ፍጥነት ያለው ተማሪ በማስነበብ የንባብ ትምህርትን ማቅረብ እንደ መፍትሔ መውሰዳቸውን አልደበቁም። ይህም እውነታ በቪዲዮ ቀረጻ በታገዘው ምልከታ በተደጋጋሚ የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ሲያነቡ ተስተውሏል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለተማሪዎች በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ በክፍት ጥያቄ 4.1 እንደገለጹት ችሎታ አላቸው ተብሎ በተደጋጋሚ የማንበብ ዕድል ለተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ መሰጠቱና ደከም ያሉ ተማሪዎች በጮክታ ንባብ ጊዜ ሲሳሳቱ ስለሚሳቅባቸው የንባብ ፍላጐታችን እየቀነሰ መጥቷል ብለዋል። በክፍል ምልከታውም ጊዜ የታየው ተማሪዎች ያነሱት ችግር ነበር። ለምሳሌ ማንበብ የጀመረውን ተማሪ በማቋረጥ ሌላ ተማሪ እንዲያነብ ሲደረግ ተስተውሏል። ይህ ሁኔታ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው ተማሪው በሚያነብበት ጊዜ ፊደላትን ሲገድፍ ንባቡን አቋርጦ እርማት መስጠት ተማሪውን በራሱ እንዳይተማመን ያደርገዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መምህራኑ በቀረባቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ተማሪዎችን ከክፍል ውጭ ለንባብ ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ በየትምህርት ቤታቸው በቂ የሆኑ መጻሕፍት አለመኖራቸውን ገልጸዋል። ይህም ችግር ጐልቶ የሚታየው በተለይ በአማርኛ ቋንቋ አጋዥ መጻሕፍት ነው። ይህን ችግር ለመቅረፍ መምህራን በግል ያላቸውን መጻሕፍት ለተማሪዎቻቸው ለማዋስ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል። ይህ ሁኔታ ግን ከተማሪው ቁጥር አንጻር የማያዋጣ መሆኑን ያምናሉ።

ሌላው በጊዜ-ንባብ ደረጃ መከናወን ካለበት ንዑስ የንባብ ክሂል አንዱ ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ ማድረግ ነው። ይህን በተመለከተ 3 (50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%)መምህር ፈጽሞ አልጠቀምም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ከንባቡ ዝርዝር መረጃን ማውጣት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ነው። ይሁን እንጂ ይህ መረጃ በክፍል ምልከታው ከታየው ጋር የተቃረነ ሆኖአል። ስለዚህ በ5 (83.3%) መምህራን ክሂሉን እንደሚተገብሩ በ.ያመለክቱም መምህራኑ በሰጡት ምላሽ ከክፍል ምልከታው ጋር ተመሳሳይነት ያለው መረጃ አይደለም ስለዚህ ምንም እንኳን መምህራኑ ይህን ምላሽ ቢሰጡም ከምልከታው ግን ይህን ማረጋገጥ አልተቻለም።

ሌላው በጊዜ-ንባብ ደረጃ ከሚዳብሩት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አንዱ ተማሪዎች የጽሑፉን አደረጃጀት መረዳታቸውን ለማወቅ ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ ነው። ይህም የሚሰጠውን ትኩረት ለመፈተሽ በቀረበው ጥያቄ 2(33.3%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን ለንዑስ ክሂሉ ትኩረት እንደሰጡት ነው። ነገር ግን ይህ መረጃ በክፍል ምልከታው ከታየው ጋር መጠነኛ ልዩነት ያሳያል። በክፍል ምልከታው ሲያከናውኑ የታዩት 2(33.3%) መምህራን ሲሆኑ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው መረጃ ደግሞ የሚያሳየው 6ቱም (100%) መምህራን ማከናወናቸውን ነው።

በዚህ ሌላ የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ ማድረግ ንዑሳን የንባብ ክሂል የተሰጠውን ትኩረት ለማወቅ በቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ 4(66.6%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 1(16.7%) መምህር አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤1(16.7%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ የሚል ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን የቃላትን ፍቺ ከአውድ መገመትን ከፍተኛ ትኩረት እንደሰጡት ነው። ይህም መረጃ በምልከታው ከታየው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ ማድረግ ንዑስ የንባብ ክሂል በአብዛኞቹ መምህራን ከፍተኛ ትኩረት እንደተከናወነ ያመላክታል። ከላይ የተዘረዘሩትን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ እንደሚከተለው ተነጻጽሮ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሃያአንድ፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ስለሚሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠየቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር ይጠቀማሉ		አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ		አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ		ፈጽሞ አይጠቀሙም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
2.1	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የንባብ አይነቶችን (የአሰሳ፣ ግርፍ) እንደአስፈላጊነታቸው እንድትቀጠሙ ያደርጋሉ።	42	32%	36	27%	41	31%	13	10%
2.3	ስዕል ማገናዘብ ወይም ቅጽ መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን እንድትሰሩ ያደርጋሉ።	24	18%	28	21%	42	32%	38	29%
2.4	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በዝምታ ንባብ እንድታከናውኑ ያደርጋሉ።	65	49%	34	26%	19	14%	14	11%
2.5	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ከንባቡ ዝርዝር መረጃዎችን ለይቶ ማውጣት ጥያቄ ያቀርባሉ።	62	47%	33	25%	26	20%	11	8%
2.6	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የጽሑፉን አደረጃጀት እንድትናገሩ ያደርጋሉ።	31	24%	44	33%	49	37%	8	6%
2.7	የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንድትገምቱ ያደርጋሉ።	52	39%	35	27%	37	28%	8	6%

ከላይ በሠንጠረዥ ሃያ አንድ እንደቀረበው በጊዜ-ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ስለሚሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸው የአሰሳ ወይም የግርፍ ንባብ እንደአስፈላጊነታቸው ስለመጠቀማቸው 42 (32%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፣ 30 (27%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 41 (31%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 13 (10%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።አብዛኞቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ የሚያመለክተው ስለንባብ አይነቶቹ በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸው ነው። ምክንያቱም በክፍል ምልከታው እንደታየው ተግባሩ ባለመከናወኑ ነው። ጥቂት ይሁኑ እንጂ 13(10%) ተማሪዎች ትክክለኛውን መረጃ ሰጥተዋል።

ምንም እንኳን ለመምህራኑም ሆነ ለተማሪዎች በተሰጠው የጽሑፍ መጠይቅ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ አብዛኞቹ መምህራን እንደሚተገብሩት ቢያመለክቱም በምልከታ እንደተስተዋለው ግን ተጠኝ መምህራኑ ንባብን ያቀርቡ የነበረው ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ወይንም መምህራን ራሳቸው በጮክታ በማንበብ ነበር።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ስዕልን ማገናዘብ ወይንም ቅጽ መሙላት ወይንም ዝርዝር ጉዳዮችን በሠንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን እንድትሰሩ ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት የጽሑፍ መጠይቅ 24 (18%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 28 (21%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 42 (32%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 38 (29%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

በተጠኝ መምህራኑም ሆነ በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ በምልከታ ከታየው ይለያል። ከምልከታው መገንዘብ እንደተቻለው ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መሙላት ወይንም ዝርዝር ጉዳዮችን በሠንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን ማሰራት በተጠኝ መምህራኑ ሙሉ በሙሉ ትኩረት አልተሰጠውም። በተጠኙ መምህራኑን ሆነ ተማሪዎች ይህን ምላሽ የሰጡት አንዳንድ መምህራን ከንባብ በኋላ የሚያሰሩዋቸውን መልመጃዎች በማስታወስ ሳይሆን አይቀርም። እነዚህ ከንባብ በኋላ የሚተገበሩ መልመጃዎች ደግሞ በመጽሐፉ ውስጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎች መሆናቸውን ለማስተዋል ተችሏል። በመሆኑም እነዚህ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በጊዜ-ንባብ ደረጃ አልተተገበሩም ለማለት ይቻላል። በሌላ በኩል 38 (29%) የሚሆኑ ተማሪዎች ፈጽሞ አለመጠቀማቸውን በማስተዋል አመልክተዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የገምታ ንባብ እንድታከናውኑ ያደርጋሉ። ለሚለው የጽሑፍ መጠይቅ 65 (49%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 34 (26%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 19 (14%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ 14(11%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። በጥናታዊ ዳሰሳው ግኝት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ከተጠኝ መምህራኑ ምላሽ ጋር አልተጣጣመም። ይህም 2 ተጠኝ መምህራን የገምታ ንባብ ፈጽሞ አልጠቀምም የሚል ምላሽ በመስጠታቸውና እንዲሁም 2 ተጠኝ መምህራን ፈጽሞ አልጠቀምም በማለታቸው ነው። በቪዲዮ ቀረጻ በታገዘው ምልከታ እንደታየው አንድ መምህር ለመተግበር ቢሞክሩም ተማሪዎችን በገምታ አንብቡ ብለው ካዘዙ በኋላ እንደገና በአራት ተማሪዎች ምንባቡን በጮክታ ንባብ አስነብበዋል።

ይህም ሁኔታ የዝምታ ንባብ ተግባራዊ ተደርጓል ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም የዝምታ ንባብ ንዑስ ክሂል ምንም ትኩረት ያልተሰጠው ነው ማለት ይቻላል።

ከንባብ ዝርዝር መረጃን ለይቶ ማውጣት ንዑስ ክሂል ስለሚሰጠው ትኩረት አስመልክቶ 62 (47%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 33 (25%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 26 (20%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 11 (8%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ መረጃ የሚያመለክተው በምልከታው ከታየው በጣም የራቀ ነው። በምልከታ እንደታየው ለክሂሉ ትኩረት የሰጡት 2(33.3%) መምህራን ብቻ ናቸው። ስለዚህ ተማሪዎች ትክክለኛውን መረጃ አመላክተዋል ለማለት አይቻልም።

በተመሳሳይ ሁኔታ የጽሑፉን አደረጃጀት እንዲናገሩ ስለመደረጉ በሰጡት መልስ 31(24%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 44 (33%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 49 (37%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 8 (6%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ አብዛኞቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በክፍል ምልከታው ከታየው ጋር አልተጣጣመም። ስለዚህ አብዛኞቹ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በትኩረት ያልታየ መሆኑን ያመላክታል።

እንዲሁም ተጠኝ መምህራኑ የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ ስለመደረጉ ተማሪዎች በሰጡት ምላሽ 52 (39%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 35 (27%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 37 (28%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 8 (6%) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይጠቀሙም በማለት መልሰዋል።

ተጠኝ መምህራን በጽሑፍ መጠይቁ ክፍል ሶስት በ2.8 እና 2.9 የተገለጸው ሀሳብ በተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በ2.5 እና በ2.6 ከተገለጸው ጋር ተቀራራቢ በሆነ መልኩ አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ከንባቡ ዝርዝር መረጃን ማውጣትና የጽሑፉን አደረጃጀት መናገር ላይ ትኩረት የሚያደርጉ መሆናቸውን ያመለክታል። ነገር ግን በክፍል ምልከታው እንደታየው ለነዚህ ንዑስ የንባብ ክሂሎች የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ነው። ከዚህ በመነሳት ከንባቡ ዝርዝር መረጃን ማውጣትና የጽሁፉን አደረጃጀት መናገር ንዑስ የንባብ ክሂል አነስተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በሌላ በኩል የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር መገመት ንዑስ የንባብ ክሂል ከክፍል ምልከታው፣ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ እና በተማሪው የጽሑፍ መጠይቅ እንደተገለጸው ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውና በአብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን የተተገበረ ነው። በተጨማሪም ተጠኝ መምህራኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ ሲመልሱ ንባብን በሚያስተምሩበት ጊዜ ትኩረት ከሚያደርጉበት ንዑስ ክሂል አንዱ የቃላትን ፍቺ ከአውድ እንዲገምቱ ማድረግ ነው። በመሆኑም ከሁሉም መረጃዎች ማጠቃለል የሚቻለው ለዚህ ንዑስ የንባብ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው ነው።

በአጠቃላይ በጊዜ ንባብ ደረጃ መዳበር ከሚገባቸው ንዑስ የንባብ ክሂሎች በተጠኝ መምህራን የተሰጣቸው የትኩረት ደረጃ የተለያየ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ለምሳሌ የአሰሳ ንባብ ፣ የገረፍታ ንባብ፣ የዝምታ ንባብ ጨርሶ ትኩረት የተነፈጋቸው ሲሆን ለቃላት ከአውድ አንጻር ፍቺ መገመት ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው መረዳት ተችሏል።

4.3.3. ድህረ ንባብ ደረጃ

4.3.3.1. በድህረ ንባብ ደረጃ መምህራን የሚያከናውኗቸው ተግባራት

በድህረ ንባብ ደረጃ መምህራን ከሚያከናውኑት ተግባር አንዱ ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት በማድረግ ማቅረብ ነው። ተጠኝ መምህራኑ ይህን ስለማከናወናቸው ከክፍል ምልከታው የተገኘ መረጃ በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመላክቷል።

ሠንጠረዥ ሃያ ሁለት :- መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በተመለከተ በክፍል ምልከታው የተገኘ መረጃ፡-

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ተከናውኗል		አልተከናወንም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
3.2	ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት አድርገዋል።	5	83%	1	17%

ይህን በተመለከተ በሠንጠረዥ ሃያ ሁለት እንደተገለጸው ፭5 (83%) መምህራን ተከናውኗል፣ ፩1 (17%) መምህር አልተከናወነም። መረጃው እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ተማሪዎች ንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያይዙ በማድረግ ማቅረብ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት የሰጡት መሆኑን ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለመምህራን በቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውን- መረጃ ለማነጻጸር እንደሚከተለው ቀርቧል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሠንጠረዥ ሃያ ሶስት፡- መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በተመለከተ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄ	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር እጠቀማለሁ		አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ		አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ		ፈጽሞ አልጠቀምም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
3.2	ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት ያደርጋሉ	2	33.3%	2	33.3%	2	33.3%	0	0%

በሠንጠረዥ ሃያ ሶስት እንደተገለጸው ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያዙ ስለማድረጋቸው 2 (33.3%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም መረጃ አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ምንባቡን ከተማሪዎች ገጠመኝ ጋር በማያያዝ ማቅረባቸውን ያመለክታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሃያ አራት፡-መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ይዘት	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር ይጠቀማሉ		አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ		አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ		ፈጽሞ አይጠቀሙም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
3.2	ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት ያደርጋሉ።	23	17%	28	21%	50	38%	31	24%

ከሠንጠረዥ ሃያ አራት መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ተጠኝ መምህራኑ ምንባቡን ከተማሪዎች ገጠመኝ ጋር አያይዘው ስለማቅረባቸው 23 (17%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 28 (21%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 50 (38%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 31 (24%) ተማሪዎች ደግሞ ፈጽሞ አይጠቀሙም የሚል ነው። ይህም የሚያሳየው በተለያየ ደረጃ ይሁን እንጂ ተጠኝ መምህራኑ ምንባቡን ሲያቀርቡ ተማሪዎች ከገጠመኛቸው ጋር እንዲያያይዙ እያደረጉ መሆኑን ነው።

ለማጠቃለል ያህል ከክፍል ምልከታው፣ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ምንባቡን ከተማሪዎች ገጠመኝ ጋር በማያያዝ ያቀርባሉ ማለት ይቻላል። በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው መምህራንን ምንባብን ከተማሪዎች ገጠመኝ ጋር በማያያዝ ማቅረባቸው ተማሪዎች ከንባቡ የሚያገኙትን ግንዛቤ ከእውኑ ዓለም ጋር እዲያዛምዱ ያደርጋቸዋል። ይህም የንባብ ትምህርቱን ህይወታዊ ለማድረግ ያስችላቸዋል። ስለዚህ ተጠኝ መምህራኑ ለዚህ ትኩረት መስጠታቸው የንባብ ትምህርቱን ህይወታዊ ለማድረግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

4.3.3.2. በድህረ-ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎችን የተሰጣቸውን ትኩረት በተመለከተ

በድህረ-ንባብ ደረጃ ትኩረት የሚሰጣቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳት፣ የመገምገም ችሎታ እና ንባብን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር መማር ነው።እነዚህን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ተጠኝ መምህራኑ መተግበራቸውንና የሰጡትን የትኩረት ደረጃ ለማወቅ የተደረገው ምልከታ በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሃያ አምስት፡- ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከክፍል ምልከታው የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ተከናውኗል		አልተከናወንም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
3.1	ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን መምህሩ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል።	6	100%	0	0%
3.3	ተማሪዎች ምንባቡ እንዲገመግሙ አድርገዋል።	2	33.3%	4	66.7%
3.4	ከንባብ ጋር ሌሎችን ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አቅርበዋል።	6	100%	0	0%

በሠንጠረዥ ሃያአምስት እንደተመለከተው የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳታቸውን መምህራኑ ጥያቄ በመጠየቅ ስለማረጋገጣቸው በተደረገው ምልከታ በ6ቱም (100%) መምህራን ተግባራዊ መደረጉን መረጃው ያሳያል። በመሆኑም አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳት ንዑስ የንባብ ክሂል በተጠኝ መምህራኑ ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው ያመለክታል።

በድህረ ንባብ ጊዜ ከሚከናወነው ተግባር አንዱ ተማሪዎች የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ ነው። ይህንንም ተግባር ተጠኝ መምህራኑ በሙሉ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለመገንዘብ ተችሏል።

በሠንጠረዥ ሃያ አምስት በተቁ. 3.3 በቀረበው ጥያቄ ከንባብ በኋላ ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ ስለመደረጉ በክፍል ምልከታ እንደታየው በ2 (33%) መምህራን ተከናውኗል፣ በ4 (66.7%) መምህራን አልተከናወነም። ይህም መረጃ የሚያመለክተው የመገምገም ችሎታ ንዑስ የንባብ ክሂል የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ ነው። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ ማድረግ የምንባቡን ሀሳብ የበለጠ እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም የቀረበውን ምንባብ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር በማነጻጸር በሀሳቡ መስማማታቸውን፣ተአማኒነቱን፣ ጥሩ መሆኑን እና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች በመመርመር የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ይሁንና ይህን ንዑስ የንባብ ክሂል በክፍል ውስጥ በበቂ ሁኔታ ተግባራዊ ሲደረግ አልተስተዋለም። መምህራኑ ይህን የተማሪዎችን የመገምገም ችሎታ ለማዳበር የሚያግዝ ክሂል በወጉ እንዳልተገበሩት ያመላክታል።

በተራ ቁጥር 3.4 ለተመለከተው ተጠኝ መምህራኑ የንባብን ክሂል ከሌሎች ጋር በማጣመር ስለማቅረባቸው በቀረበው ጥያቄ በ6ቱም (100%) መምህራን መከናወኑን ከሰንጠረዥ ሃያ አምስት መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጂ በክፍል ምልከታው እንደታየው ንባብን ከክሂሎች ጋር ማቀናጀት በአብዛኛው የተከናወነው ከንግግርና ከማዳመጥ ክሂል ጋር በተያያዘ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ጥያቄዎችን አዳምጠው በቃል እንዲመልሱ መደረጉ የጽሕፈት ክሂል እንዲዘነጋ አድርጎታል። የጽሕፈት ክሂል በመዘንጋቱ ሁሉንም ተማሪ ለማሳተፍ አላስቻለም።

ንባብን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ለማቅረብ የተለያዩ መልመጃዎችን መስጠት ይቻላል። ይሁንና ተጠኝ መምህራኑ በቃል ጥያቄ ላይ ያመዘነ አቀራረብ ነበራቸው። ይህንንም ሀሳብ በተመለከተ ተጠኝ መምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሃያ ስድስት፡- ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር እጠቀማለሁ		አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ		አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ		ፈጽሞ አልጠቀምም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
3.1	ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሃሳብ መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል።	3	50%	2	33.3%	1	16.7%	0	0%
3.3	ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ (ጥሩ መሆኑን መስማማታቸውን፣ አለመስማማታቸውን) ያደርጋሉ።	1	16.7%	3	50%	1	16.7%	0	0%
3.4	የንባብን ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ያቀርባሉ።	3	50%	2	33.3%	1	16.7%	0	0%

ከሠንጠረዥ ሃያ ስድስት መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሃሳብ መረዳታቸውን ስለመጠየቃቸው ተጠኝ መምህራኑ በሰጡት ምላሽ 3 (50%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1 (16.7%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ መምህራን ለዚህ ንዑስ የንባብ ክሂል ትኩረት መስጠታቸውን ነው። ይህም መረጃ ከክፍል ምልከታው ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል።

ሌላው አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ ምንባቡን እንዲገመግሙ ስለማድረጋቸው ተጠኝ መምህራኑ በሰጡት ምላሽ 1(16.7%) መምህር ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 3(50%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1(16.7%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ፤ የሚል ነው። ይህም አብዛኞቹ መምህራን ምንባቡን መገምገም ላይ ትኩረት እንደሚሰጡ ያሳያል። ሆኖም ግን ይህ ሁኔታ በክፍል ምልከታው ከታየው ጋር የተስማማ አይደለም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በድህረ-ንባብ ጊዜ የንባብ ትምህርትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ያቀርቡ እንደሆነ በቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ 3(50%) መምህራን ዘወትር እጠቀማለሁ፤ 2 (33.3%) መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ፤ 1(16.7%) መምህር አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ የሚል ነው። ከዚህ በመነሳት አብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ንባብን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውታል ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የጽሕፈት ክሂል ጨርሶ የተዘነጋ ነበር። በክፍል ምልከታው እንደታየው ከጽህፈት ክሂል ጋር በተያያዘ ተማሪዎች የፈጸሙት ተግባር አልተስተዋለም። የተገለጸውን ሀሳብ በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው እንደሚከተለው በማነጻጸር ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሃያ ሰባት፡-ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጣቸው ትኩረት ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ

ተ.ቁ	ይዘት	ሀ		ለ		ሐ		መ	
		ዘወትር ይጠቀማሉ		አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ		አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ		ፈጽሞ አይጠቀሙም	
		ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ	ብዛት	መቶኛ
3.1	ንባብ በኋላ አጠቃላይ የንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ መምህራችሁ ጥያቄ ያቀርባሉ።	83	63%	22	17%	20	15%	7	5%
3.3	ምንባቡን እንድትገመግሙ (ጥሩ መሆኑን፣ መስማማት አለመስማማታችሁን) ያደርጋሉ።	36	27%	35	27%	37	28%	24	18%
3.4	መምህራችሁ የንባብን ትምህርት ከጽህፈት፣ ከንግግር ከማዳመጥ ጋር በማያያዝ እንድትማሩ ያደርጋሉ።	62	47%	34	26%	23	17%	13	10%

ከሠንጠረዥ ሃያ ሰባት መረዳት እንደሚቻለው የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳታቸውን በመምህራቸው ስለመጠየቃቸው 83(63%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 22(17%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 20 (15%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፣ 7(5%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ በማለት መልሰዋል። ከመረጃው እንደሚታየው አብዛኞቹ መምህራን አጠቃላይ ሀሳቡን መረዳት ንዑስ የንባብ ክሂል ትኩረት የሰጡ መሆኑን ነው። ይህም መረጃ ከክፍል ምልከታው እና ከመምህራን መጠይቅ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል።

በጥያቄ 3.3 ላይ የተመለከተው መጠይቅ ተጠኚ መምህራኑ ምንባቡን እንዲገመግሙ ስለማድረጋቸው ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ 36(27%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፤ 35(27%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 37(29%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤22 (17%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም፤ የሚል ነው ምንም እንኳን ተማሪዎች አብዛኞቹ ተጠኚ መምህራን ምንባቡን ለመገምገም የሰጡት ትኩረት ከፍተኛ መሆኑን ቢገልጹም በምልከታ ከታየው ጋር የሚጣጣም አልሆነም።

በመጨረሻም ተጠኚ መምህራኑ የንባብ ትምህርትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማጣመር ያቀርቡ እንደሆነ ለማወቅ ለተማሪዎች በቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ 62(48%) ተማሪዎች ዘወትር ይጠቀማሉ፣ 33(26%) ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ፣ 22(17%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ፤ 12(9%) ተማሪዎች ፈጽሞ አይጠቀሙም የሚል ነው። ከዚህ በመነሳት ማጠቃለል የሚቻለው ክሂሎችን በማጣመር የማስተማር ንዑስ የንባብ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ነው። ይህም መረጃ ከክፍል ምልከታውም ሆነ ከመምህራን መጠይቅ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ተገኝቷል።

በጥቅሉ ሲታይ በድህረ-ንባብ ደረጃ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የተሰጠው ትኩረት ከጊዜ-ንባብ ደረጃ ከተሰጠው ትኩረት የተሻለ ነው። ይሁንና በቪዲዮ ቀረጻ በታገዘው ምልከታ እንደታየው አንዳንድ ተጠኚ መምህራን በንባብ ትምህርት ጊዜ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ አልነበሩም። ይህም ማለት ቅድመ-ንባብ መቅረብ የነበረባቸውን ጥያቄዎች በድህረ-ንባብ ደረጃ ሲያቀርቡና፤ ጊዜ-ንባብ ደረጃ መተግበር የነበረበትን የአሰሳ ንባብ በድህረ-ንባብ ደረጃ ሲተገብሩ ለማስተዋል ተችሏል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ ተጠኚ መምህር በቃለ መጠይቁ ላይ እንደገለጹት የአሰሳ ንባብን የሚጠቀሙት መልመጃዎችን በሚያሰሩበት ጊዜ መልሱን ከምንባቡ ለይቶ ለማውጣት እንደሆነ ጠቁመዋል። ይህም ሁኔታ መምህራኑ ስለ አሰሳ ንባብ አላማና አተገባበር ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ መሆኑን ያመለክታል። Wallace (1992:6) እንደገለጹት የአሰሳ ንባብ

ከአንድ ጽሑፍ የተወሰኑ መረጃዎችን ለማግኘት የሚከናወን ተግባር ነው። መተግበር ያለበትም በጊዜ-ንባብ ደረጃ ነው።

4.3.4. ተጠኝ መምህራን ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው ከጥናቱ ዓላማ አንዱ መምህራን ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ነው። ይህን በተመለከተ ለተጠኝ መምህራን በተሰጠው የጽሑፍ መጠይቅ ላይ በክፍት ጥያቄ 2.6 የንባብ ትምህርት ሲሰጡ ለየትኞቹ የንባብ ንዑሳን ክሂሎች ትኩረት ይሰጣሉ? ለሚለው ጥያቄ ተጠኝ መምህራኑ የተለያየ መልስ ሰጠተዋል። በዚህም መረጃ 2 (33.3%) መምህራን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማለትም መናገር፣ ማዳመጥ፣ ማንበብና መጻፍ በማለት መልሰዋል። 4 (66.7%) መምህራን ደግሞ ለጥያቄው መልስ ከመስጠታቸው በፊት ክፍት ቦታ በመተው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚባሉት ምንድናቸው? የሚል ጥያቄ አንስተው ማብራሪያ ጠይቀዋል። በማብራሪያውም በንባብ ጊዜ የሚተገብሯቸው ተግባሮች እንደሆኑ ፍንጭ መስጠት የግድ ነበር። ፍንጭ ከተሰጣቸውም በኋላ የጠቀሷቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎችም ቢሆኑ በቁጥር ከ4 አልዘለሉም። ከሰጡትም መልሶች መካከል አንብቦ መረዳት፣ የማስተዋል ጥያቄ የሚሉ ጥቅል ሀሳቦችን የሚገልጹ ነበሩ። ይህም የሚያመለክተው መምህራኑ የንባብን ትምህርት የሚያስተምሩት መማሪያ መጽሐፉን ተከትለው በውስጡ ያሉትን ጥያቄዎች በማሰራት ላይ ባተኮረ መሆኑን ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በቃለ ምልልሱ ላይ እንደገለጹት ቀደም ብሎ ስልጠና የወሰዱ በመሆኑ ስለዘመናዊ (ተማሪ ተኮር)ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ግንዛቤ እንደሌላቸው ገልጸዋል።በመሆኑም የሚያስተምሩት በልምድና ከተማሪዎች ችግር በመነሳት የራሳቸውን መንገድ በመከተል እንደሆነ ገልጸዋል። እንዲሁ አንድ መምህር ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውጭ ንዑሳን ክሂሎች ስለመኖራቸው አላውቅም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ በመነሳት አብዛኞቹ ተጠኝ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑን መገመት ይቻላል። ንዑስ ክሂሎችን ተግባራዊ የሚያደርጓቸው በመጽሐፉ ቅድመ-ንባብ የመወያያ ጥያቄዎችና በድህረ-ንባብ ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎች ላይ ያሉትን ጥያቄዎች በሚያሰሩበት ጊዜ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ9ኛ ክፍል የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ምን ያህል ነው? ለሚለው ጥያቄ በሂደት መልስ ለመስጠት ነው። በተጨማሪም በንባብ ትምህርት ወቅት ለየትኞቹ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የበለጠ ትኩረት ይሰጣል? መምህራንስ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዘቤ ምን ይመስላል? ለሚሉ ዝርዝር አላማዎች መልስ ለመሻት ነው።

በዚህ ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት የዋሉት በዋነኛነት የክፍል ውስጥ ምልከታ (በቪዲዮ ቀረጻ የታገዘ ነው)፣ የመምህራንና የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም ለመምህራንና ለክፍለ ትምህርት ተጠሪዎች ቃለ መጠይቅ ናቸው። እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን በመጠቀም የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው የሚከተሉት የማጠቃለያ ነጥቦች ላይ ተደርሷል።

5.1. ማጠቃለያ

5.1.1. በቅድመ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ተመሳሳይ የትኩረት ደረጃ እንደተሰጣቸው ተረጋግጧል። እነዚህም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የመገመት ችሎታና የቁልፍ ቃላትን ፍቺ ማወቅ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በአብዛኞቹ ተጠኝ መምህራን ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል።

5.1.2. በጊዜ ንባብ ደረጃ መምህሩ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ ጊዜ ወስኖ መስጠት በመምህራኑ ያልተከናወነ ሲሆን የንባብ ትምህርት ይቀርብ የነበረው በተማሪዎች ወይንም በመምህራን በጮክታ (ድምጽን በማውጣት) ንባብ ነበር።

5.1.3. በጊዜ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በተለያየ ደረጃ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ተረጋግጧል። በዚህ መሠረት በጊዜ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መካከል የአሰሳ፣ የገረፍታ፣ የዝምታ ንባብ እንዲሁም ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መመላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሠንጠረዥ መመላት ምንም ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ጥናቱ አሳይቷል። አነስተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ንዑሳን ክሂሎች ከንባብ ዝርዝር መረጃን

ማውጣትና የጽሑፉን አደረጃጀት መረዳት ናቸው። ከፍተኛ ትኩረት ያገኘው ደግሞ የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር መገመት ሆኖ ተገኝቷል።

5.1.4. በድህረ-ንባብ ደረጃ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ ከሚያከናውነው ተግባር አንዱ የቀረበውን ምንባብ ከተማሪዎች ገጠመኝ ጋር በማያያዝ እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። ይህም ሁኔታ በአብዛኞቹ ተጠኚ መምህራን ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በዚህ ደረጃ ንዑሳን ክሂሎችን በተመለከተ የተገኘው ውጤት የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳት ንዑስ ክሂል እና የንባብን ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር ማጣመር ንዑስ የንባብ ክሂል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን የቀረበውን ምንባብ መገምገም ደግሞ አነስተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ ጥናቱ አመላክቷል።

5.1.5. ተጠኝ መምህራኑ ስለንዑሳን የንባብ ክሂሎች ያላቸው ግንዛቤ ለማወቅ በክፍት ጥያቄና በቃለ መጠይቅ በተደረገው ፍተሻ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን መረጃው ያሳያል።

5.2. አስተያየት

በዚህ ጥናት የተገኙትን ውጤቶች መሠረት በማድረግ ማጠቃለያ ተሰጥቷል። ከማጠቃለያው ሀሳብ በመነሳት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

1.2.1. የዘጠነኛ ክፍል ገሚሱ ተጠኝ መምህራን የመማሪያ መጽሐፉን ብቻ በመጠቀም የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ ገሚሱ ደግሞ ከመማሪያ መጽሐፉ ውጭ ሌሎች የጽሑፍ ምንጮችንም ይጠቀማሉ። ይሁን እንጂ ከመማሪያ መጽሐፉ ውጪ የሚያዘጋጇቸው ጽሑፎች ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ለማዳበር ሆነ ተብለው የሚዘጋጁ ቢሆኑ፣

1.2.2. በቅድመ ንባብ ደረጃ ተማሪዎችን ማወያየትና በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩ ማድረግ ትኩረት የተነፈገው በመሆኑ ለዚህ ንዑስ ክሂል አመቺ ሁኔታን በመፈለግ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ቢደረግ ፣

1.2.3. በቅድመ ንባብ ደረጃ መዳበር የሚገባቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ማለትም የመገመት ችሎታና ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት ተገቢ ትኩረት ያገኙ በመሆኑ ሌሎቹም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ተመሳሳይ የሆነ ትኩረት ቢያገኙ፣

1.2.4. በጊዜ ንባብ ደረጃ ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን በመተገበር ላይ ትልቅ ድክመት የታየበት ደረጃ ነው። አብዛኞቹ መምህራን ተግባራዊ ያደረጓቸው ንዑሳን

የንባብ ክሂሎችም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት በቅድመ- ንባብ የመወያያ ጥያቄዎችና ከድህረ-ንባብ በኋላ በሚቀርቡ መልመጃዎች ትኩረት ለተሰጣቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከራሳቸውም ሆነ ከመጽሔት የሚመርጧቸው ጽሑፎች ጥሩ ጎን ቢኖራቸውም በአላማው መሰረት የተመረጡ ቢሆኑ፣

1.2.5. የአሰሳ ንባብ፣ የገረፍታ ንባብ፣ ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መመላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሠንጠረዥ መመላት ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ምንም ትኩረት ያላገኙ በመሆኑ ትኩረት ቢሰጣቸው መልካም ይሆናል። በተለይ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ይዘው የሚመጡት የንባብ ትምህርት ልምድ (የጮክታ ንባብ) ቀስ በቀስ የሚለወጥበትን ዘዴ በመቀየስ የዝምታ ንባብን ተግባራዊ በማድረግ በንባብ ትምህርት የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ለማድረግ መምህራኑ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ተጠኝ መምህራኑ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች በቂ ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የትምህርትና ስልጠና ክፍሎች አጫጭር ስልጠናዎች ተዘጋጅተው የመምህራኑ ግንዛቤ የሚያዳብርበት ሁኔታ ቢመቻች፣

1.2.6. በድህረ-ንባብ ደረጃ ተማሪዎች የመገምገም ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያግዛቸው ንዑስ የንባብ ክሂል ትኩረት አልተሰጠውም። በመሆኑም መምህራን ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ ከተለያዩ የጽሑፍ ምንጮች ምንባብ ሲመርጡ አነስተኛ ትኩረት የተሰጣቸውን ንዑስ የንባብ ክሂሎች ሊያለማምዱ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የታየውን ክፍተት ቢያሟሉ፣

በአጠቃላይ በጥናቱ እንደታየው ተጠኝ መምህራን ባላቸው አቅምና ችሎታ የንባብ ትምህርት ሲተገበሩ ተስተውሏል። ከክፍለ ትምህርት ሐላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለመጠይቅ ላይ እንደተገለጸው መምህራኑ ያለባቸውን ችግር እርስ በርስ በመወያየትና በመረዳዳት ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ። በዚህም ልምድ ያላቸው መምህራን አዲስ ለሚመጡት ልምዳቸውን በማካፈል ያግዛሉ። ይሁን እንጂ መምህራኑ የሚያስተምሩበት መንገድ በልምድ ከማስተማር የተሻለ አይደለም። ስለዚህ የንባብ ክሂል በተገቢው ሁኔታ ለማስተማር እንዲችሉ የማስተማሪያና፣ የተማሪው መጽሐፍ ንዑሳን ክሂሎችን ለማዳበር በሚያስችል መልኩ ታስቦባቸው የሚዘጋጁ መሆኑ መልካም ነው። ለዚህም መነሻ ምክንያት የሆነው በዚህ ጥናት ውጤት እንደታየው ተጠኚ

መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው ተግባራዊ ያደረጓቸው በመማሪያ መጽሐፉ በቅድመ -ንባብ የመወያያ ጥያቄዎችና በድህረ ንባብ መልመጃዎች ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸውን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ብቻ ነው።

በመምህራን ቃለ መጠይቅ ጊዜ አንዳንድ መምህራን በሰጡት አስተያየት አሁን ያለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ቀድሞ ከነበረው የተሻለና የንባብን ትምህርት ለማስተማር ፍንጭ ሰጭ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን ንዑሳን የንባብ ክሂሎችን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ የሆነ የማስተማሪያ መጽሐፍ ሊዘጋጅላቸው እንደሚገባ የሚጠቁም ነው። ለመምህራኑ ስለ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች እንዲሁም በማስተማር ረገድ አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚመለከተው ክፍል ቢያሰብበት ጥሩ ነው።

ዋቢ ጽሑፎች

ሂሩት አምሃ (1996) "የንባብ ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች ትግበራ በአስረኛ ክፍል በተመረጡ ሶስት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች (የግል)::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያ ፅሁፍ (ያልታተመ)::

መሰሉ መንግስቱ (1994) "የአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴ በስራ ላይ ላሉ ሰልጣኞች የተዘጋጀ የርቀት ማስተማሪያ ፅሁፍ::" ደቡብ ዩኒቨርሲቲ የዲላ መምህራን ትምህርት ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የርቀት ትምህርት ክፍል፣(ያልታተመ)::

መዝገበ ስዩም (1993) "የንባብ ክሂል ትምህርት ትግበራ በአስረኛ ክፍል በተመረጡ ሶስት የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቤቶች"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያ ፅሁፍ (ያልታተመ)::

ማርታ ነጋሽ (1992) "የዳግማዊ ምኒልክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና የቅዱስ ዮሴፍ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ1992 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ግምገማ::" ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመጀመሪያ ደረጃ ዲግሪ ማሚያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)::

ማስተዋል ወበቱ (1989) "የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገ ጥናት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሚያ ፅሁፍ (ያልታተመ)::

በድሉ ዋቅጅራ (1996) <u>በስነ-ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር</u>:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

ተክሉ ዕቁር (1996) "የዘጠነኛ ክፍል፣ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ትንተና፡- መንግስታዊ በሆኑና መንግስታዊ ባልሆኑ የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሚያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)::

ተፈራ ጋሻው (1990) "ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ንባብ ትምህርት አቀራረብ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያ ፅሁፍ (ያልታተመ)::

አለም እሸቱ (1995) "በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሣሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር" ከጥቅምት 25-29 ዓ.ም ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት ከሥ/ት/ዝ/ጥ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፣ (ያልታተመ)::

_____ (1992) <u>መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ</u>:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

አማርኛ ትምህርት ክፍል (1996) "10+3 ለሚያስተምሩ ዕጩ ሰልጣኝ መምህራን የተዘጋጀ።" ሳንደር፣ ያልታተመ ጥራዝ (ሞጁዩል)።

እንግዳ ዘውዴ (1992) የ"ቶፕዳውን" (Top-down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት፣ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ) ።

ወንድአጥር ደነቀ (1993) "በማስተማሪያ ቋንቋነት፣ በኦሮሚያ ክልል ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ተገቢነት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

የኔሰው ደሴ (1990) "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋፅኦ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

ጌትነት ታፈረ (1998) "ልብወለድን በመጠቀም በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ በትግራይ ክልል፣ ማዕከላዊ ዞን፣ በተመረጡ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ። (1998)። የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

Addis Abeba Education Bureau. (2005) "Education Statistics Annual Abstract" Addis Ababa: (Unpublished).

Aeberold, J. and Field, M. (1997) Form Reader to Reader Teachers: Issues and Strategies. For Second Language Classrooms. Cambridge: Cambridge University Press.

Alderson, C. and Lukmani, Y. (1989) "Cognition and Reading: Cognitive levels as Embodied in Test Questions' in Reading in a Foreign Language Journal. 5(2); 253-270.

Alderson, J. and Urquhart, A.(Eds.) (1984) Reading in a Foreign Language. London: Longman.

Allwright, D. (1988) Observation in the Language Classroom: Applied Linguistics and Language Study. New York: Longman.

Atkins, J. and et. al. (1996) Skill Development Methodology: Part 2. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

BBC (2007) "British Council Teaching English-Reading Theories of Reading" From: http://www.teaching English.org.uk/think/read/reading Theories. shtm/.

Carrell, D. and Eskey, D. (1988) Interactive Approaches to Second Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Celec-murcia, M. (1991) (Eds.) Teaching English as a Second Language. Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Clarke, M. and Silberstein, S. (1988) "Towards a Realization of Psycholinguistics Principles in the ESL Reading Class" In Language Learning. 27 (1) 135-154.

Cooper, M. and Fox, M. (1978) Junior English Reading. London: Longman.

Davis, F. (1995) Introducing Reading . London: Penguin.

Dubin, F. and Bycin, D.(1991) " Academic reading and the ESL/EFL Teaching" In Celec-murcia, M.(Eds.) Teaching English as a Second Foreign Language. Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Greenall, S. and Swan, M. (1986) Effective Reading: Reading skills for Advanced Students. Cambridge: Cambridge University Press.

Greenwood, J. (1981) "Comprehension and Reading" in Abbott et. al (Eds.) Teaching English as an International Language: A practical guide. London: Rutledge.

Grellet, N.(1981) Developing Reading Skills. New York: Cambridge University Press.

Hamp-Lyons, L. (1985) "Tow Approaches to Teaching Reading:A Classroom-Based Study" In Reading in a Foreign Language Journal. 3(1): 367-374.

Harmer, J. (1991) The Practice of English Language Teaching. London: Longman.

Harrison, C. (1980) Reading in the Classroom. New York: Cambridge University Press.

Haverson, W. (1991) " Adult literacy Training" In Celec-murcia, M. (Eds.) Teaching English as a Second Foreign Language. Boston: Heinle and Heinle.

Heaton, J. (1975) Writing English Language Tests. London: Longman.

Hosenfeld, C. (1979) A Learner in Today's Foreign Language Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Kersima Muzeyene (1994) "An Evaluation of the use of Reading Tasks in Developing Sub-skills in grade 9th" Addis Ababa University: BA Thesis (Unpublished).

Lange, B. (1991) "Making Sense with Schemata" In Journal of Reading. 24 (5): 442-442.

May, F. (1990) Reading as Communication an Interactive Approach. New York: Macmillan Publishing Company.

Nunan, D. (1991) Language Teaching Methodology. Hertfordshire: Prentice Hall International.

Nuttal, C. (1982) Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London: Heinemann Educational and Professional Publishing Limited.

Paran, A. (1996) "Reading in ELT: Facts and Fiction" In ELT Journal. 50 (1): 25-34.

Parrott, M. (1993) Tasks for Language Teachers: A Resource Book for Training and Development. Cambridge: Cambridge University Press.

Pupalia, A. (2000) "Interaction of Reader and text" In Rivers, W. (1987) Interactive Language. Teaching. New York: Cambridge University Press.

Richard, J. (1990) The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J. and Nunan, D. (1990) Second Language Teaching Education. Cambridge: Cambridge University Press.

Reivers, W. (1987) Interactive Language Teaching. New York: Cambridge University Press.

Smith, F. (1985) Reading. Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P. (1996) A Course in Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, C. (1992) Reading. Oxford: Oxford University Press.

Wallace, M. (1991) Training Foreign Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Weaver, C. (Ed.) (1990) Understanding Whole-language: From Principle to Practice. Toronto: Irwin Publishing.

Weir, C. and Robert, J. (1994) Evaluation in ELT. Oxford: Black Well Publishers.

William, E. (1984) Reading in the Language Classroom. London: Macmillan Publisher Ltd.

William, R. (1986) " 'Top-ten' Principles for teaching reading " in ELT Journal. 40(1): 42-45.

ሙዳየ ቃላት

Aloud reading	የጮክታ ንባብ
Approaches	አቀራረቦች
Back ground Knowledge	የቀደመ እውቀት
Bottom-up-reading	ከዝርዝር ወደ ጥቅል የንባብ ሂደት
Context	አውድ
Extensive	ሰፊ ንባብ
Feed –back	ምጋቤ ምላሽ
For Survival	ለህልውና
Inferring	በተዘዋዋሪ የቀረበ ትርጉም
Intensive	ጥልቅ ንባብ
Interactive	መስተጋብራዊ
Linear	መስመራዊ
Mood	አንድምታ
Pronunciation	ንበት
Receptive skill	የመቀበል ክሂል
Scanning	ግርፍ ንባብ
Silent reading	የዝምታ ንባብ
Skill	ክሂል
Skills-based	ክሂል -ተኮር አቀራረብ
Skimming	የአሰሳ ንባብ
Strategy-based	ስልት -ተኮር አቀራረብ
Structure	መዋቅር
Sub-skills	ንዑሳን ክሂሎች
Technique	ስልት
Text	ውህድ አሐድ
Tone	ድምፀት
Top-down-Reading	ከጥልቅ ወደ ዝርዝር የንባብ ሂደት

አባሪዎች

አባሪ 1ሀ.

ኮድ 01

ቀን 19/8/99

ክፍለ ጊዜ 3ኛ

ሰዓት ከ4:00 - 4:42

መ = (የዕለቱን ርዕስ ሰሌዳው ላይ መጻፍ ጀመሩ ከስሩም አንዳንድ ማስታወሻዎችን ጻፉ) በገጣሚያን የተለያዩ የኪነ ጥበብ ሰዎች እንዳሉ አንድ ቢሰውር፣ በሽተኛ ፣ ሰውየው ወይም ገረመው አሮጊቷ በምንባቡ እነዚህ አምስቱ ሰዎች የሉም ?

ተ = (በጋራ)አሉ

መ = እነዚህ የሚወክሉ ናቸው ሰዎች የምናውቃቸው ናቸው እንዴ? ኧ

ተ = አይደሉም (በጋራ)

መ = አሁን የጠራናቸው ግን የምናውቃቸው ናቸው። አዎ በአካል እጆቻቸውን ፣ እግሮቻቸው የነሱ አስራር፣ የነሱ ሁኔታ አቀራረብ የእነሱ አነጋገር መውሰድ የሚቻል ሲሆን እነዚህን ነገሮች ግን በአምሮአችን የዓለም ነጸብራቅ የሆኑ ነገሮችን ገጸ ባህሪ ወክለው የቀረቡ ናቸው። ስለዚህ ልዩነቱ ምንድን ነው? እነዚህ በአካል የምናውቃቸው ናቸው። እነዚህ ግን የተለያዩ ነገር የገሃድን ዓለም ወክለው የሚገቡ በአካል የማናውቃቸው ነገር ግን በኪነ ጥበቡ ግን የስነ ፅሑፍ ሰዎች ወይም ተወካዮች ናቸው ሌላው መግቢያ የሚያነብልን አንድ ሰው፣ መግቢያ የሚያነብልን ማነው? መግቢያ የሚያነብልን? ይድነቃቸው ይሁን አይደል?

ተ = አዎ(በጋራ)

መ = እሺ! ቢሰውርስ?

ተ = ብርሃኔ

መ = እሺ! ቢሰውር ብርሃኔ አሮጊቷስ?

ተ = ትዝታ! ኤደን !

መ = እሺ! ማን ይሁን?

ተ = ኤደን

መ = እሺ. በሽተኛስ

ተ = ትዝታ

መ = እሺ. ሰውየው ወይም ገረመውስ?

ተ = አስፋው

መ = እሺ አስፋው ሰውየው ወይም ገረመው ሁለቱ አንድ ናቸው ገረመው አንድ ብቻ ነው የሚናገረው እሺ መግቢያ ይድነቃቸው ውጣ ሁላችሁ ስታነቡ ግን ተራ ምንባብ ሳይሆን ገጸባህሪያት የሚናገሩትን በሸተኛ እየሳቀ ነው እንዴ? የሚናገረው

ተ = አይደለም

መ = እያቃሰተ ፣ እየደከመ ፣ ድምጹ እየሰለለ ፣ ሁሉም ይሰቃያል ማለት ሳይሆን ነገር ግን ስናነብ በሽታው የሚያሰማው የጭንቀት ድምፅ እሱን ነው ማሰማት ያለብን፡፡ እሺ አሁን መጀመር ትችላላችሁ እናንተ ዝም በሉ ወሬ ይቅር (5 ተማሪዎች ፊት ለፊት ወጡ)

ተ = (በመቀባበል ማንበብ ጀመሩ ምንባቡን ሲያነቡ በተውኔታዊ ሁኔታ ንግግራቸውን እየቀያየሩ ነበር) ምንባቡን አነንብበው እንደጨረሱ ከአንድ ተማሪ በስተቀር ወደቦታቸው ተመለሱ

$ተ_1$ = (በተማሪዎች አንባበብ ስልት ላይ አስተያየት መስጠት ጀመረ)

መ = ለሌላው ዕድል ስጥ

$ተ_2$ = ካሣሁን ሲያነብ ድምጹ ይንቀጠቀጣል ስለዚህ ፍርሃትን ማስወገድ አለበት

$ተ_3$ = ተቀብለሃል

$ተ_1$ = ሌላ

$ተ_4$ = እነሱ ሲናገሩ በሚናገሩበት ሰዓት ሳቅን ማስቀደም የለብንም ሀሳባችንን ከጨርስን በኋላ መሳቅና መንተባተብ ሰው ማንም ተማሪ ነው ተማሪ ለተማሪ መፈራራት የለበትም ሃሳቡን በግልጽ መናገር አለበት

$ተ_1$ = እሺ ሌላ ተጨማሪ ሃሳብ ካለ

$ተ_5$ = ልጆቹን በጥሩ ጎኑ የምደግፈው አብሶ ብርሃኔ... ትንሽ መንተባተብ አለ

$ተ_6$ = ምንባቡን በደንብ እንደተወያየን እንደ ድራማ ብንሰራው ጥሩ ይመጣ ነበር...

መ = ሌላ የሚታያችሁ

$ተ_7$ = እንደ ሰውየው ሆና መስራት የሚገባውን እሷ ሰርታዋለች እና ተራ አለማወቅ አለ እሷ ደሞ ሰውዬ ሆኖ ሰርታለች

$ተ_1$ = የጸታ ለውጥ ተደርጓል

$ተ_8$ = አዎ እና የፈደል መገደፍ

$ተ_9$ = እነዚህ ሰዎች ዝም ብለው እንደስድ ንባብ ነው የሚያነቡት እንጂ ሌላው ጥሩ ነው

$ተ_1$ = እሺ ሌላ ተጨማሪ

$ተ_{10}$ = መድረክ ላይ ቢሆን ተመልካች አይስቅም እንዴ ...

መ = ሌላ

ተ$_1$ = ማለት ነው እኔ ሳነብ እርግጥ እንደሐኪምም ሆነ እንደ ገረመው ሆኜ ግዴታ መናገር የለብኝም አንብቤዋለሁ አሸ ሌላ አስተያየት የሚሰጥ አለ?

መ = ጥሩ ነው? እንዴት ነው? ይጠቅማል ወይ? በርዕሱ ዙሪያ

ተ = በዚህ ርዕስ ዙሪያ በበፊቱ ነበር መቼም በገጠር አካባቢ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች አሉ። አሁን ግን የሉም ተብሎ ይታመናል እንጂ ሙሉ በሙሉ ሊደገፍ አይችልም ምክንያቱም አሁን በሽታዎች በዝተዋል መርፊ በተከታታይ ለአንድ መርፊ ለሁሉም የሚወጋው

መ = በአሁኑ ሰዓት እንዲህ አይነት በየቀበሌው በየምኑ በባሕላዊም በመድሃኒቶች ሰበብ የተለያዩ ለሰማንያ ለመቶ ያክል በሽታ የሚሆኑ በሽታዎች እናድናለን፣ እንፈውሳለን ጐራ በሉ ነ እየተባለ የሚባልበት የለም እንዴ?

ተ= (በጋራ) አለ

መ = ስለዚህ ከአዲስ አበባ ከተማ ሳይቀር የለም ወይ? አለ የሚባል ነገር አለና ከዚህ አንባር ከገጠሩ ከከተማው በሃያአንደኛው ክፍለ ዘመን እንዲህ ነገር ለተለያዩ በሽታዎች የሚያጋልጥ ነው ወይ? ይሄን ነገርስ እንዴት ነው ማስቆም ማስቀረት የሚቻለው? እንዴት ነው መኮነን የምንችለው? እሰቲ ከዚህ አያይዛችሁ ብትመልሱ

ተ$_1$ = እሸ

ተ$_2$ = መንግስት የምትለው ሕዝቡ ራሱ መንግስት ነው መንግስት ማለት ህዝብ ስለሆነ ሕዝቡ ራሱ ለነዚህ ነገሮች ተጠቃሚ ሳይሆን ቢያስቀረው እነዛ ሆስፒታሎች ነገሮች ላልተወሰነ-- ለኪሳራ ስለሚወድቁ ያንን ስራ ሊተውት ይችላሉ። አለበለዚያ አንዳንድ ተቋማት ይሄን በማየት እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል።

ተ$_3$= ጎጂ እንደሆነ ያውቃሉ በመንደር ላይ መጠቀም የለባቸውም የከተማዎቹ ብዙ ማለት ብዙ ነገር ያውቃሉ የገጠሮቹ ደግሞ ስለማያቁ በእንደዚህ አይነት መጠቀም ጎጂ እንደሆነ ብዙ ተጽእኖ እንዳለው

ተ$_4$= እንደተባለው ብዙ ሰዎች አልቀውበታል አሁን በአሁን ዘመን ሃኪም ቤት በየክፍለ ከተማው ስላለ አሁን ትንሽ የተሻለ ነው።

ተ$_5$ = ከተማ ያለው ህዝብ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል አሁን ለምሳሌ ያህል ዛሬን ብወስድ አንድ ሴት ልጅ ብታረግዝ ለውርጃ ብትጠይቅ ሆስፒታል ሄዳ ሆስፒታሉ አልችልም ካላት ግዴታ ወደመንደር መሄዷ ነው ገጠር አካባቢ ማለት ነው እንደዚህ አይነት መርፊ ወጊዎች ጋር ማለት ነው። ግን እንዲህ አይነት ነገሮችን ልናስቀር የምንችለው መጀመሪያ ህብረተሰቡ

ተባብሮ እንዲዚህ አይነት ነገሮች ቢፈጠሩ የሚፈታበት ሁኔታ ቢፈጠር እ ደሞም እነዚህ መርፌ ወጪዎች ቢከለከሉ

ተ1= እሺ ሌላ እርዳታ ብትጠይቅ ገንዘብ ከሌላት በአሁኑ ሰዓት ማንኛውም ነገር የሚንቀሳቀሰው በገንዘብ ነውና ገንዘብ ከሌለው ደግሞ ሰው አንድ ነገር ሊደረግለት አይችልም በጐ አድራጐት ካልሆነ በስተቀር ስለዚህ ያቺ ሴት የት ነው የምትሄደው? ግዴታ መንደር ውስጥ ባለው ሐኪም ውስጥ ነው ... እና በኔ አመለካከት የምሰጠው አስተያየት ምንድን ነውን መንደር ውስጥ ያሉ ሐኪም ቤቶች መሉ በሙሉ መቅረት አለባቸው በመንግሥት ያልታወቀት ለምሳሌ አሁን እኛ ሰፈር ውስጥ አንድ በዶክትሬት ተመርቀዋል። እንደገና ደሞ የዶክተርነት ህግ ፈቃድ አላቸው እና እንደዚህ አይነቱንስ የመንደሩ መርፌ ወጪ ነው ልንል የምንችለው ወይስ? ከመንግሥት ሆነ ከግል

ተ6= እውቅና ሳይኖረው ዶክትሬት ሳይኖረው እውቀት ሳይኖረው ማለት ነው እኔ ዶክተር ነኝ ብሎ የሚያምን ለሱ ነው የመንደሩ መርፌ ወጪ የሚባለው።

መ = ብዙ አንስተን ልንገልጸው ልናብራራው የምንችለው በመሆኑ ብዙ ሊያወያየን ይችላል ወይ? ምንባቡ ወደ ምንባቡ ስንመጣ ስንመለስ ምንድነው ስናስብ ግማሹ እንደዚህ ብለን ማንበብ የለብንም (በድርጊት በማሳየት) ያው አቋቋም ያስፈልጋል። ይሄንን ነገር ባለንበት በዚያኑ ሰዓት በዚህ ጊዜ እንደዚህ አይነት ነገሮች መስፋፋት አለባቸው እንዴ?

ተ = አይ

መ = ማቆም ነው ያለባቸው አይደል እህቴ የተወጋችበት ነው እያልን በአሁኑ ሰዓት በአሁኑ ጊዜ በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መርፌ የሚወጉ አሉ? አሁን ለምሳሌ ንፋስ ስልክ ያሉት አቶ ማሞ የሚባሉ አሉ መድሃኒት አለበት እንጂ በየስርቻው በየጓዳው በየጎድጓዳው እየሄዱ መታከም አደጋ አለው። (ትምህርቱን አጠቃለሉ)።

አባሪ 1ለ.

ክድ 02

ክፍለ ጊዜ 4ኛ

ቀን 28/8/99

ሰዓት 5:00-5:42

መ= (ሰላምታ ከሰጡ በኋላ) አገኛችሁት ገጽ 132 መጽሐፍ ካለው ጋር ሁኑ ምንባብን የምታነቡት በቅብብል ነው የሴቱን ሴት የወንዱን ወንድ ሆናችሁ ነው የምታነቡልኝ። መጽሐፍህስ? ከፊት አንብብልኝ ምነው ቆየኝ እሺ ጮክ በልና

ተ= (ማንበብ ጀመረ)

መ= ይሄ ምን አይነት ድርሰት ነው የምንለው (ንባቡን አቋርጠው) በምን መልኩ ነው የምናየው;

ተ= ስዕላዊ

መ= ስዕላዊ፡ ቀጥል ቀጥል! አሁን በስዕላዊ ድርሰት

ተ= (ማንበብ ቀጠለ)

መ= እሺ! ድርሰትም... ራቅ ብሎ ቆሟል በጠረጴዛው ላይ የመድሐኒት ብልቃጦች ተቀምጠውበታል---- (ማንበብ ጀመሩ) ይሄ በስዕላዊ ድርሰት የቀረበ ነው። ከታች ያለውን እዩ ገረመው! እስኪ የገረመውን "አክት" የሚያነብልን ልክ ገረመው እንደሚያደርገው! እሺ። (ለአንድ ተማሪ ዕድል ሰጡ) ያፌል ቆይ ተነሽ አንቺ

ተ= በሽተኞችን ዝም ለማሰኘት (ማንበብ ቀጠለች)

መ= ትጠየቃላችሁ ዝም (በድርጊት እያሳዩ)

ተ= አነበበች

መ = የጀመሪያው ሰልፍ እዚህ ጋር ነው (በድርጊት እያሳዩ) (2)

ተ= (አነበበች)

መ= እስኪ ሌላ እንደገረመው ሆኖ የሚያነብ ወንድ (2) የሴት አለ የራሱ እስቲ ሌላ ሌላ (የሚያነብ ባለመገኘቱ) ቁጥር ልጠራ... ወንዶቹን ነዋ የምፈልገው (እሷ አንድ ተማሪ እንዲያነብ ጠየቁት ፈቃደኛ አልሆነም) በል! በል እንጂ

ተ= ማንበብ ጀመረ

መ= ጮክ በልና አንብብ (አንድ ተማሪን አስጠነቀቁ)

ተ= ንባብ ጀመረ

መ= ዝም ብትሉ ምናለበት (ተማሪዎችን አስጠነቀቁ) እሺ ቀጥል

አሁን አንተ ገረመውን ሆነህ ነው የምትሠራልን

ተ= ማንበብ ቀጠለ

መ= ወንድም ባለኮፍያ አንተ

ተ = (አነበበ)

መ= ወንድም! ስንታየሁ (ሌላ ተማሪ እንዲያነብ ነው)

ተ=ማንበብ ቀጠለ

መ= እርማት ሰጡት (ተማሪዎች ተንጫጩ)

ተ= ማነህ? ቀጥል

መ= እሺ. ቢሰውርን ቀጥል አንተው ራስህ

ተ= (አነበበ) (ተንተባተበ)

መ= ሌሎቻችሁ አዳምጡት እስቲ ሱሪህን አታወልቅም! (በደንብ ብታነበው ምን አለበት)

ምን አይን አይኑን ታያለህ ቀበቶህን ፈተህ ሱሪህን አታወልቅም (የአነባበብ ስልቱን አሳዩት);

ተ= (ማንበብ ቀጠለ)

መ= እሺ. ሱሪውን ቀጥልልን አንተው ራስህ

ተ= ወንድም (አነበበ) ምንህ ላይ የምትወጋ ይመስልሃል?

ቢሰውር እ...

መ = እሺ.

ተ= አነበበ

መ= እሺ. አሁን እድሜው ገፋ ያለ በሽተኛ አንክስ እያለ ይገባል

ተ= አነበበ

መ=መርፌውን ይወጋሃል ብለህ አንተ ምን ትመልሳለህ

ተ= አነበበ

መ= እሺ. ሰውየውን ሆነህ ስራልና

ተ= (አነበበ)

መ= እሺ. የስር መሸማቀቅ ደርሶብኝ

ተ= (አነበበ) (ተማሪዎች ሳቁ)

መ=ቀጥል

አሮጊት ሆኖ የሚሰራ እኔ ልምራሽ እኔ ላል እያጣደፋቸው ስልሽ

ተ= (አነበበች)

መ= ቢሰውር

ተ= አነበበች

መ= ልብስዎን

ተ= አነበበች

መ= እሺ አሁን ያንቺ ተራ ነው

ተ=አነበበች

መ= እሺ ቀሚስዎን ክፍ ያድርጉ አሮጊቷን ይወጋና በዛ እሽት እሺ አሁን ያንቺ ነው

ተ= አነበበች

መ= የሆድ ቁርጠት ይገላግለኛል

ተ= አነበበች

ተ= አነበበ

መ= ቀሚሳቸውን እንደገለቡ በሌላ ታፋቸው ይወጋቸዋል (አሁን ያንቺ ነው)

ተ= አነበበ

መ= አዎ በጣም፡ አሁን

ተ= አነበበች

መ= ካሁን ጀምሮ

ተ=አነበበች

መ=አይዘጋ ደጃችሁ

ተ= አነበበ

መ= ገረመው ድምፁን ያጠፋና ወዲያው

ተ= አነበበ

መ= አቁረጡት (አንተ አይደለህም) እስቲ!

ተ.=አነበበ

መ= በሚጥም ሁኔታ አልተነበበም አነባበቡ

ተ= በጋራ (አልጣመንም)

መ.=ተቀባብሎ ሊያነብል የሚችል የሴቱን ሴት የወንዱን ወንድ አክት እኮ በነገው ላይ በትያትሩ ላይ እንገመግመዋለን እስኪ ዛሬ በመወያያ ጥያቄዎች ላይ እናየዋለን።

ርዕሱን በማንበብ ምንድነው የመንደሩ መርፊ ወጊ የሚለውን አይተን ምን እንረዳለን።
እንደገና ጊዜ ስነፅሑፍ ስናነብ ርዕሱን አይተን ምን እንደሆነ መገመት እንችላለን። ከውስጥ
የምንገምተው ነገር ምንድነው ?እጃችሁን እያወጣችሁ መልሱ

ርዕሱን አየን! ከውስጥ ይዘቱን አንብበናል አሁን ከርዕሱ የምንረዳው

ተ= ከመንደሩ መርፊ ወጊ ርዕስ አይተን የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ፍላጎት ለማርካት
ያላቸው ብቃት አነስተኛ መሆኑን የሥራ ልምድ አለመኖር

መ= ብቃት ያላቸውን እጃችሁን እያወጣችሁ እስኪ ሌላ!

ተ=ሰውየውን አልሰማሁትም

ተ= ያንዱን በሽታ ወደሌላ ያስተላልፋሉ።

መ= በሽታን ወደ ሌላ ሲያስተላልፉ አይተንበታል ሌላስ! እሺ አሁን ማለት እንድትሉ የምፈልገው
የመንደሩ መርፊ ወጊ የሚለው ርዕስ ከይዘቱ ጋር ምንድነው ግንኙነቱ! ግንኙነት አለው? የለውም?

ተ= (በጋራ)አለው

መ= እስኪ ሌላ አሁን ያላችሁትን በሌላ እናነሳዋለን

ተ= ሕጋዊ አይደለም

መ= ሕጋዊ ያልሆኑ ሐኪሞችን እናይበታለን ከገረመው አለባበስና ሲጋራ ማጨስ የምንረዳው
ምንድነው? የሚያመለክተው ምን እንረዳበታለን? እጃችሁን እያወጣችሁ ምንድነው የምንረዳው?
ሲጋራ እያጨሰ የሚገባ ዶክተር

ተ1 = ስነስርዓት የሌለው መሆኑን

ተ2 = የሚታየው ስነምግባር አለማሟላቱን

ተ3 = ዶክተሩ ያልተማረ መሆኑን ከህብረተሰቡ ጋር ያለውን ሪሌሽን ያሳያል

መ= እሺ

ተ=ሙያ የሌላቸው መሆኑን ከሙያው ጋር ተያይዞ የሚወጣ ስነምግባርን አለማሟላታቸው ምንም
የተማረ ቢሆን ኖሮ መጀመሪያ ለራሱ ያውቅበት ነበር።

መ= እሱ ሲጋራ አታጭሱ ይል ይሆናል! አይደል እሺ ያጨሳል ንፅህና የጎደለው ነው ሲጋራ
እያጨሰ የሚገባ ዶክተር ምንድነው? ሱስ ሊኖርበት ይችላል። ከውጭ ሊያጨስ ይችላል
የሚያጨስ አስተማሪ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን እዚህ ክፍል ውስጥ አያጨስም ከስነምግባር
አንጻር ስናየው ዶክተር አይደለም ከልምድ ነው የሆነው ሌላ የተቀመጣችሁ ሁሉ ተነሱ ይላል
ለምንድነው፣ (በድጋሚ ጠይቁ) ምንድነው የምንገነዘበው ከዚህ አባባል ሐኪም ቢሰውር
መጥተዋልና የተቀመጣችሁ ሁሉ ተነሱ ነው የሚለው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ተ= ግዴለሽነት

መ =እጅህን አውጥተህ ብትመልስልኝ ጥሩ ነው። ሐኪም ቢሰውርና መጥተዋልና የተቀመጣችሁ ሁሉ ተነሱ ነው የሚለው ከዚህ የምንረዳው ምንድነው ?

ተ=ክብር ለመስጠት

መ= ለዶክተሩ ክብር ለመሰጠት ነው።

መ =እንደውም አጨብጭቡ እልል በሉላቸው ነው የሚለው መተዋል ነው የሚለው ቅድም እንዳልከው መቼም የታመመ ሰው እንኳን እና አጨብጭብ ተነስ እግር ሳምም ብትለው ይስማል ህብረተሰቡ ለመዳን ነው ፈልጎ እስኪሄድ ድረስ የተባለውን ያደርጋል የንቃተ ህሊና ማነስ ያለመማር ውጤት ነው። ምንድው የሚለው አንብባችሁታል? አይደል አብረን ነው ያነበብነው። እኛችሁን ከንዱ ይላል እንዴ! ታመው ነው የሚሄዱት በደጋፊ ነው። የመጀመሪያው በሽተኛ እንደገባ አይን ዓይኑን ይመለከተው ነበር ለምንድነው? አትዩ መጽሐፋችሁን አንብበነዋል። እሰቲ ማስታወሳችሁንም እንወቀው ! መርፊ ሊወጋ የገባው ሰውየ ስሪንጅ ይዞ ይመለከተው ነበር ቆሞ ያየው ነበር ለምንድነው ?ፈርቶ ነው ?ለምንድው ? መድሐኒቱ (እንዲህ እንዲህ ሲያደርግ) ቆሞ ያየው ነበር ለምንድነው?

ተ = ከፍርሐት አንባር ነው

መ = ከፍርሐት አንባር (ጮክ) ይላል

ተ = በሽታውን ሳይጠይቀው ቀጥታ ሊወጋው ስለሆነ ነው

መ = ትክክል ናት ምንህን ያምሐል ምናምን ብሎ ሳይጠይቀው ምን ይገትርሐል ከፊቱ ነው ያለው አይደል ? አሁን እሱ የመሰለው በሽታውን ጠይቆ የሚታዘዘውን መርፊ ሊሆን ይችላል ያ ሰውዬ ግን ዝም ብሎ ነው ሊወጋው የነበረው ሰውዬው ዝም ብሎ ቆሞ ያየው በፍርሐት ነው

መ = ሚስት አለህ ብሎ ሲጠይቀው ምንድነው ያለው ?

ተ = እንዴታ

መ = በጣም ሸማግሌ ነው ለምንድን ነው እንደዚህ ያለው እንዴታ ያውም የልጆቼ እናት ነው ያለው? ከዕድሜ አንባር እንኴን እንዴት ነው አላገባም ያለኝ ሌላ ሳይሆን ከዕድሜ አንባር እንዴት አላገባም ይለኛል ነው ታዲያ ብዙ ሰዎች ወደመንደሩ መርፊ ወጊ ብዙ ሰዎች ሂደዋል (መጽሐፋችሁን አትዩ) ግን ይሄ ታዲያ አግባብ ነው ትላላችሁ ? እኛችሁን አውጥታችሁ መልሱ አግባብ ነው እንበል

ተ= ሰው ከኢኮኖሚው አንፃር ሰውየው ከዝቅተኛ ስለሚያክሙ የድሮ ሰዎች በብዛት ስላልተማሩ ዝቅተኛው ጋር መሄድ ነው

መ = ከኢኮኖሚ ሌላስ ?

ተ$_1$ = ህብረተሰቡ በመቸገር ነው እዛ አካባቢ ሆስፒታል ላይኖር ይችላል

ተ$_2$ = ርካሽ ስለሆነ ነው

መ = ሌላስ ? ግን እኮ በተዘዋዋሪ በመርፌ እየወሰደው ነው ለምሳሌ ሌላ አካባቢ ብናይ ለምን ለምን እያልን ከዚያ በላይ እናወጣለን። ምርመራ 10 ብር ነው ይላል ሐኪም ቢሰውር ለምርመራ አያስከፍል እንጂ በተዘዋዋሪ ለመርፌ እያለ እያስከፈለ ነው እስኪ ሌላስ?

ተ = አንዳንድ ጊዜ አግባብ ነው አንዳንድ ጊዜም በሽተኞች እጃቸውን አጣጥፈው እቤት ከሚቀመጡ ትንሽ እንኳን በዕውቀት ይሻላሉ አንዳንዴ ከማያውቁት ነገር የሚያውቁት ነገር ይሻላል

መ = ያውቃል ማለት እንችላለን ሐኪም ቢሰውርን ? የምንባቡን ይዘት ነው አሁን የምንገመግመው እስኪ ሌላ ህብረተሰቡ በብዛት እዛ እየሄደ ነው መሄዱ አግባብ ነው ወይ?

ተ = ምክንያቱን ለመናገር

ተ$_1$ = ለራሱ ብቻ ስለሚያስብ

ተ$_2$ = ወደ ምርመራ እንኳን አይገባም

መ = መርፌው አንድ ዓይነት ነው አይደለም? እንደውም መድሐኒቱም አንድ ዓይነት ነው ምንም እንደውም በሽታ ሸምቶ መሄድ ነው ተግባሩ ኤች አይ ቪ ከማሰፋፋት አንፃር እንዴት ይታያል? ብሂላቸው ተገቢ ነው ብለናል አይደለም ብለናል።

ተ = በአንድ መርፌ ብዙ ሰው ስለሚወጋ በሽታ ያስፋፋል

መ = ህብረተሰቡን ምን እያደረገ ነው? እየበከለ ነው የመንደሩ መርፌ ወጊ ከጥቅሙ ይልቅ ምኑ ነው የሚያመዝነው ?

ተ = ጉዳቱ

መ = ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው ከኢኮኖሚ አንፃር ኢኮኖሚ ስንል ግን ከገንዘቡ አንፃር ነበር መዳን አይደለም ሞት ነው ይዘን የምንመጣው (የሌሎች ክፍሎችን የድራማውን አሰራር ምሳሌ ስጡ) (የአንድ ተማሪ ገጠመኝን ተረኩላቸው በመንደር መርፌ ወጊ ምክንያት የመጣ ችግር ነበር) (በድራማው አሰራር ላይ ክርክር ገጠሙ ተማሪዎች ይህን ምንባብ በድራማ መልክ ለማቅረብ ተነጋገሩ) በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ የሚሰሩትን የቤት ሥራ ሰጡ ክፍል አንድ 3ኛውን ስሩ።

አባሪ 1ሐ.

ክድ 03

ክፍለ ጊዜ 3ኛ

ሰዓት 3:25 -4:07

ቀን 24/8/99

መ= (ርዕሱን በሰሌዳው ላይ ፃፉ) ማንኛውም ቋንቋ አራት ክሂሎች እንዳሉት ነው እነዚህ አራት ክሂሎች የራሳቸው የሆነ ክፍፍል አላቸው የመጀመሪያው ክሂላችን ከመጀመሪያው ልምዳችን ስንነሳ ማዳመጥ ነው ሌላኛው ደግሞ እያደጉ ሲመጣ መናገር፣ ሌላኛው ማንበብ ነው።

ሌላኛው ደግሞ መፃፍ ነው። እነዚህ እንዲህ አራቱ ክሂሎች የሚባሉ ናቸው። እነዚህን እንግዲህ አራቱን ክሂሎች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንከፍላቸዋለን። ማዳመጥና መናገርን ብዙውን ጊዜ ከአካባቢው ከቤተሰቦቻችን ተምረን የምናመጣቸው ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ የሚያስፈልጉን የክሂል አይነቶች ማንበብና መፃፍ ናቸው። በእርግጥ እነዚህም አሉ። ማዳመጥ አለ መናገር አለ። እነዚህ ብዙ ጊዜ ማንበብና መፃፍን የምናገኛቸው ትምህርት ቤት ውስጥ ነው። እና እነዚህን ነው ትምህርት ቤት ስንመጣ /ጽህፈትና ንባብን/ የማድ ት/ቤት መግባት ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር ስንመጣ «ለምን እንፅፋለን» የሚለውን በመጽሐፋችን እንመልከት። እስቲ ወደዚህ ? ሀሳብ ወደ ምንባብ ከመግባታችን በፊት ለነዚህ መንደርደሪያ የሚሆኑ ጥያቄዎች አሉ።እያንዳንዱ የራሱ የሆነ አላማ አለው እያንዳንዱ የራሱ የሆነ አላማ አለው የመጀመሪያ ፅሁፍ ምንድነው ነው?

መ= የጽህፈት ጥቅም ምንድን ነው? /ተማሪዎች እጃቸውን አወጡ/

እሺ ጮክ በይ

ተ1= አንድ ነገር ለመጻፍ እንዳንረሳ

መ= አዎ! የጽሕፈት አገልግሎት ነገሮች እንዳይረሱ ለማድረግ ነው

ተ2= ለምሳሌ ጥንት የተጻፉ ጽሁፎች አሁን እኛ እናነባቸዋለን፤ ያኔ ስለተጻፉ ማለት ነው እኛ የምንጽፋቸው ጽሑፎች ደግሞ ወደፊት ለሚመጡ ይጠቅማሉ።

መ= ወደፊት ለሚመጡት እንዲያገለግል ያደርጋል እሺ ጥሩ ነው!

ተ3= በማስታወሻ ጽፎ ለማቆየት

መ= የምናከናውነው ነገር በማስታወሻ ለማስቀመጥ ነው።

እንደውም ተረትና ምሳሌ ምን ይላል?

«እብድና ወረቀት የያዘውን አይለቅም » ብዙውን ጊዜ የሚባል አባባል አሉ እና በጥቅል እንዳላችሁት ነው።።

ወደ ሁለተኛው እንምጣ ሀሳባችን እንትን እያላችሁ እንድንሄድ ነው።። / ጥያቄውን አነበቡ/ ፅሀፈት ከንግግር በምን ይለያል? እንግዲህ ቅድም እንዳያችሁት /በድጋሚ ጥያቄውን አቀረቡ/ ቅድም ያልናቸው ክሂሎች አሉ።። አንዱ ንግግር ነው ሌላኛው ፅሀፈት ነው።። ይሄ ፅህፈት ከንግግር በምን ይለያል? ሌላስ ሌላው ንግግር በምን ይደገፋል /2/ በአካል እንቅስቃሴ ይደገፋል አይደለም እንዴ ? አሁን ሰው ለማስረዳት ስትፈልጉ ይሄ እኮ እንደዚህ ነው / እጃቸውን በማወዛወዝ ያሳያ ሉ/ እያላችሁ ማለት ትችላላችሁ ፅህፈት ላይ ግን የአካል እንቅስቃሴ ሊኖር ስለማይችል ጥንቃቄ ያስፈልጋል።። ማለት ነው ።። የአካል እንቅስቃሴ በንግግር ሲገለጽ ወይም ሲታይ በጽህፈት ላይ ግን የአካል እንቅስቃሴ መታየት አይችልም ማለት ነው።። የአካል እንቅስቃሴ ሊተኩ የሚችሉት ምንድን ናቸው?

ተ= /በጋራ/ ቃላት

መ= በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙት ቃላት ሐረጎች ናቸው እንዲሁም ደግሞ ዐረፍተ ነገሮች ናቸው።። እነሱን ይወክሉልናል።። የመጨረሻው ጥያቄያችን አንድ ፀሐፊ ጥሩ ፀሐፊ የሚያሰኘው ምንድን ነው? /ተማሪዎች ዝም ስላሉ በድጋሚ ጥያቄውን አብራሩ /ስለአንድ ነገር በውስጣችን የሚያድር ነገር አለ ያን ነው እንግዲህ ተማርን የምንለው።። የተፃፈ ነገር ለማንበብ አስቀድመን ወይም ከልምዳቸን አንባር ወይም ካየነው፣ ካካባቢያችን አንባር እንዴት መረዳት እንችላለን ብለን ስለዚህ አንድ ፀሐፊ ለመጻፍ የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ተ= ጥሩ ቃላት የሚጠቀም

መ= አዎ ጥሩ ቃላትን የሚጠቀም።። ጥሩ ቃላትን መጠቀም ሲችል /በሰሌዳው ላይ እየፃፉ/ የቃላት አመራረጠ።። ሌላስ? እሺ !

ተ= ፅሁፉ አንባቢን የሚስብ ሆኖ ሲገኝ

መ= /የተማሪውን መልስ ደገሙና/ ሌላስ እሺ ሌላስ እነዚህ እንግዲህ ከቃላት ጋር የተያያዙ ናቸው።። ሌላስ አንድ ፀሐፊ ጥሩ ነው የሚባለው።።

ተ= ብዙውን ጊዜ ግልፅና የሚገባ ሲሆን

መ= /የተማሪውን ሀሳብ ደግሞ/ የቃላት አመራረጥ ሌላስ? /ጠየቁ/ ምን አይነት ነገር ሊኖረው ይገባል አንድ ፀሐፊ ለመሆን ወይም ደራሲ ለመሆን ምን ምን ነገሮች ሊጠበቁበት ይችላሉ? ዋናው ትልቁ ነገር እናንተ እንዳላችሁት የቃላት አመራረጡ የአፃፃፉ ስልት አንባቢን የሚስብ መሆን መቻል አለበት እርግጥ እነዚህ በቃላት ይገለጻሉ ነው።። ሌላስ ምን ማድረግ ይገባዋል? አንድ ደራሲ ማድረግ የሚገባው የሚፅፍበትን ቋንቋ ምን አድርጎ ማወቅ አለበት?

ተ= ጠንቅቆ

መ= ጠንቅቆ ማወቅ አለበት /በሰሌዳው ላይ ጻፉ /ለምሳሌ እኔ ትግርኛ ትንሽ ትንሽ እየቻልኩ፣ ግን በጣም አማርኛ እየቻልኩ በትግርኛ መፃፍ ግን በጣም ይቸግራል ምክንያቱም ቋንቋ በውስጣቸው ምንን ይገልጻሉ ባህሪን ይገልፃሉ። አካባቢን ይገልፃል ስለዚህ በዛ አካባቢ የሚባለውን የምፅፍ ከሆነ ያንን ቋንቋ ጠንቅቄ ማወቅ አለብኝ።

አንዳንዱ ቃል ፍቺውን ያለውን ማወቅ መቻል አለብኝ ያለበለዝያ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ቋንቋዎች ይወራረሳሉ። ተወራርሰው ሲሄዱ በሌላ አካባቢ የሚባለውን ነገር በዛ ቦታ ለምሳሌ በጎንደር የሚፃፈውን በአዲስ አበባ መጥቼ ልፃፍ ብል አይሆንም ስለዚህ አካባቢያችንን ጠንቅቆ ማወቅ ሌላስ /2/ አንድ ደራሲ የሚጠበቀው ቋንቋውን ጠንቅቆ ማወቅ ነው፤ /አስታውሱ/ ሌላው የቃላቶች አመራረጥ ነው፤ ሌላው ከደራስያን ጋር ከታላላቅ ደራስያን ጋር ምን ማድረግ ነው? . . . መገናኘ ት /2/ ሌላስ? አንድ ዋና ነገር አለ ራሳችሁ እየፃፋችሁ ምንድነው የምታደርጉት? ዝም ብላችሁ ነው የምትጽፉት? ፍላጎት መኖር አለበት። ሌላስ? ፍላጎት በምን ይታገዛል? የተለያዩ ምኖችን? መጽሐፎችን ማንበብ የግድ ይላል። አንድ ነገር ለመጻፍ ሰዎች የጻፉትን ነገር ማንበብ አለብን። ፅሁፍ ሰዎች የፃፉትን ነገር ስናይ የቃላት አመራረጦችን የተዋበ ሊሆን ይችላል፣ የአፃፃፍ ስልት የተዋበ ሊሆን ይችላል። ብዙ ነገር ሊጻበር ይችላል ስለዚህ አንድ ደራሲ የቃላት አመራረጥ፣ እንደገና የሚናገረው ቋንቋ ወይም የሚፅፈውን ቋንቋ ጠንቅቆ ማወቅና ማወቅና ከሌሎች ደራሲያን ጋር መገናኘት፣ ሌላው ደግሞ ፍላጎት መኖር፣ ውስጣዊ ፍላጎት ከሌላው ደራሲ መሆን አይችልም ስለተማሪው ብቻ ፀሐፊ መሆን የለበትም የስፖርት ፕሮግራም ላይ መሐንዲስ የ ነበረው የስፖርት ምን ሆኖአል? የስፖርት ጋዜጠኛ ሆኗል። ሌላውስ ፍላጎት ሌላው የተፃፉ ነገሮችን ማንበብ ያጻጻፍ ቴክኒኮችን መንገድ ሊሰጡን ይችላሉ እንግዲህ እንፅፋለን ብለን ስንነሳ እነዚህን ነገሮች እናያለን። ፅሁፍስ የሚለውን ነገር ደግሞ በማንበብ እናየዋለን። እሺ እስቲ የሚያነብልኝ ከናንተ መጀመሪያ እሺ

ተ1= /አንዲት ሴት ተማሪ አነበበች/

ተ2= /ሌላ ተማሪ አነበበች/

ተ3= /ሌላ ተማሪ አነበበች/

ተ4= /ሌላ ተማሪ አነበበ/

መ= /ተማሪዎች በመቀባበል አንብበው እንደጨረሱ/ ንባብ ብዙ አይነቶች አሉት ግልጽ ንባብ አለ፣ ጥልቅ ንባብ አለ ሌላም የምንባብ አይነቶች አሉ አንድ ምንባብ በምናነብበት ሰዓት እያንዳንዱ ጥያቄዎች አሉት ዝም ብለን በፍጥነት በማንበብ ሳይሆን ምንባቡ ጠለቅ አድርገን ማንበብ አለብን በተቻለ መጠን ምክንያቱም በጥያቄ ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች እነዚያን ጥያቄዎች ለመስራት ምንባቡን ጠንቅቀን ማወቅ ይጠበቅብናል በመጀመሪያው ምንባባችን ስለምንባብ ያለንን አመለካከት ማስተዋል ነው። አመለካከታችን ትክክል ሊሆን ላይሆን ይችላል ነገር ግን ያለንን

ስሜት ማወቅና ከዛ በኋላ ምንባቡ ከኛ ስሜት ጋር ያለውን ካሰብነው አንጻር ምን አይነት ግንኙነት አለው? ወይስ ደግሞ ሌላ የሚለውን ልዩነት ያሳያናል ማለት ነው። እሺ ለመጨረሻ ጊዜ እኔ እያንዳንዱን አንቀጽ በማንበብ. /ያ የአጻጻፉን መልክ እንዲህ የያንዳንዳችን የራሳችን የሆነ ሁኔታዎች ይኖሩናል።/

/አንቀጽ በአንቀጽ እያነበቡ ገለጻ ማድረግ ጀመሩ/

/የምንባቡ ዋና ሀሳብ በሰሌዳው ላይ በማውጣት ፃፉ/

ገለፃውን ከጨረሱ በኋላ ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንደሚሰሩ ተናገሩ።ምንባቡን ምን ያህል ተገንዝባችሁታል የሚለውን ለማወቅ ነው የሚጠይቁት ጥያቄዎችን በንባብ አቀረቡ /ከመጽሐፉ ላይ/

ጥያቄ፡-ለጥሩ ዕሁፍ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ባህሪያት ምንድን ናቸው? ምርጫዎች አሉ። አንዱ ክሂላችን ምንድነው ብለናል? ማዳመጥ ነው ያዳመጥነውን ነገር ደግሞ በጥያቄ መልክ ሲመጣ ምን ማድረግ ነው?

ተ= «ሐ» በማለት መለሱ

መ= መልሱን አብራሩ

መ= ክፍለ ጊዜውን በማለቁ የቤት ስራ 102 ላይ ያለውን ስሩ በማለት አዘዙ ስለዕሕፈት የተወሰነ ነገር መጻፍ አለባቸው በማለት በተለያዩ ርዕሶች አንድ ዕሁፍ እንዲዕፉ አዘዙ። /በሚዕፉበት ጊዜ የተማሩትን እንዲያስተውሱ በማሳሰብ ትዕዛዝ ሰጡ/ የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ።

አባሪ 1መ.

ኮድ 04

ክፍለ ጊዜ 5ኛ

ሰዓት 5:00 -5:42

ቀን 24/8/99

መ= ዛሬ ቀን ስንት ነው

ተ= /በጋራ / 24

መ= 24/8/ 99 /በሰሌዳው ላይ ፃፉ/

እሺ ዕርሳችን የሚሆነው «የጐበጠ ቤት» የሚለው ነው / በሰሌዳው ላይ ፃፉ/ ርዕሱ የጐበጠ ቤት ነው /2/

እሺ የምንባብ ስራችን እንትን የምንለው አንድ የምንባብ የምንባብ ሥራ በምንሰራበት ጊዜ በመጀመሪያ እኔ አነብላችኋለሁ፤ከዛ በኋላ እኔን መስላችሁ ለማንበብ ትሞክራላችሁ፤ ወይም ጥሩ አንባቢ ነው ብላችሁ የምትገምቱትን ሰው ኮፒ አድርጋችሁ ሳይሆን እሱን በጭንቅላታችሁ በማሰብ ራሳችሁን መስላችሁ ለማንበብ ትሞክራላችሁ። ስለተነጋገርን ይሄን ያህል ብዙዎቻችሁ ጥሩ አንባቢዎች ብትሆኑም አንዳንዶቻችሁ ጥሩ አንባቢዎች እንዳልሆናችሁ ተወያይተን እንለፍ እሺ ኧ. . . ምንባቡ በዚህ መልክ እንትን እንላለን አንዳንድ ጥያቄዎችን አብረን እየሰራን ለመጓዝ እንሞክራለን። አሁን «የጐበጠ ቤት» የሚለውን አነብላችኋለሁ። መጽሐፋችሁን ትከታተላላችሁ።

እሺ አዬ ቴዎድሮስ . . . / ማንበብ ጀመሩ/ የመጽሐፋችሁን ገጽ ተናገሩ።

እሺ ኧ. . . አዬ ቴዎድሮስ የምን ስማቸው ነው?

የንግስና ስማቸው ነው ወይስ ከመንገሳቸው በፊት ነው?

ተ= /በጋራ/ የ ንግስና ስማቸው

መ= እሺ ቴዎድሮስ ወይም አዬ ቴዎድሮስ የንግስና ስማቸው ነው። ከመንገሳቸው በፊት ስማቸው ማን ይባል ነበር?

ተ= ካሣ . . . ካሣ / በጋራ መለሱ/

መ= አዎ የቋራው ካሣ ይባል እንደነበር ነው።

/ምንባቡን ማንበብ ቀጠሉ ወዲያና ወዲህ እያሉ/ . . .ጨካኝ ሊያሰኘው ይችላልን /ማንበባቸውን አቁረጠና/ እንዴት ይሄንን እስኪ መልሱልኝ አንድ ወላጅ ማለት አስገድዶ መድሐኒት እንዲወስድ ቢያደርገው ልጁን ... ወላጁን ጨካኝ ያሰኘዋል?

ተ= /በጋራ/ አያሰኘውም . . . አያሰኘውም !

መ= አያሰኘውም ? ለምን?

ተ= /እጅ በማውጣት / ለደህንነቱ አስቦ ነው።

መ= አዎ ! ለደህንነቱ አስቦ ስለሆነ ጨካኝ አያሰኘውም ማለት ነው እርግጥ ነው ሲገርፈው . .

/ማንበብ ቀጠለ/

/ተማሪዎች እንዲያነቡ እድል ሰጠ/

እሺ አንቺ

ተ= /ማንበብ ጀመረች/ /አንብባ እንደጨረሰች ስለአነባበቧ ጠየቁ/ ጥሩ ታነባለች

መ= ለምን ጥሩ አላችሁት?

ተ= አትንተባተብም

መ= እሺ አንደኛ አትንተባተብም፤ ሁለተኛ ድምጿ ይሰማል።

እሺ አይመስልህም ሙሴ !

እሺ የሚቀጥለውን አንድ ልጅ ማን ያነብልኛል?

በዚህ መደዳ እድል አልሰጠሁም፡ እሺ አንቺ

ተ= ማንበብ ጀመረች

መ= እሺ እና ስታነቡ ቃላት ሲኖሩ ይችላሉ። አሁን ቴዎድሮስን ምን ያላቸዋል? ኢትዮጵያን እንደጥንቱ አንድ አድርገው ይላል።

/ተማሪዎች እጅ አወጡ / እሺ /ተራ በተራ መክራ አድርጉ/ /ለመልሱ ምንም አስተያየት አልሰጠም/ እሺ ሃይማኖት

ተ= ግዛታቸውን ሳይከፋፍሉ በአንድ ላይ አድርገው መግዛት

መ= አዎ የተሻለና ጥሩ መልስ ነው።

እሺ አዲስ ምን ትላለህ?

ተ= ኢትዮጵያን ለማስተዳደር በየግዛቱና በየመሳፍንቱ በአንድነት አድርገው መንግስትና ሕዝባቸውን ለማስተዳደር።

መ= በጣም ድንቅ ነው።

ጌድዮን!

ተ= በአንድ ሀይማኖት በአንድ ቋንቋና በአንድ ባሕል

መ= እሺ ! የሀይማኖትና የአዲሱ በጣም ጠንከር ያለ መልስ ነው።

እና ጥሩ መልስ ነው። አገራቱን

ተ= እና ስለዚህ ተግባራዊ አይሆንም

መ= እሺ በጣም ጥሩ ሀሳብ ነው። /ለሌላ ተማሪ ዕድል ሰጠና የመጨረሻው የአንቺ ይሆናል/

አባሪ 1ሠ.

ክድ 05

ክፍለ ጊዜ 5ኛ

ሰዓት 5:00 -5:42

ቀን 6/9/99

መ= መጽሐፋችሁን አውጡ:: ምንባቡን ከማንበባችን በፊት የቅድመ መወያያ ጥያቄዎች አሉ:: በነኛ ጉዳዮች ላይ እንነጋገራለን::

(ተማሪዎች ተንጫጩ) ወደዚህ በማለት ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲሰበስቡ አሳሰቡ ጥያቄዎቹ የመጀመሪያው በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመዘርዘር ግልጽ የሚል ነው::

እስቲ አንተ (እጁን ያወጣውን ልጅ ጠየቁ)

ተ= ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ስንል ጥቅም የሌላቸው ድርጊቶች ናቸው:: ከነዚህም ለምሳሌ ጫት መቃም ልማድ ምናምን ግን ጎጂ ልማድ ነው::

መ= እሺ ! በአብዱ ላይ የሚጨምር ? ከሴቶች እሺ!

ተ= ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ስንል. . .

መ= አይሰማም

ተ= ጠቃሚነት የሌላቸው

መ= እሱ ትክክል ነው ለምሳሌ

ተ= የሴት ልጅ ግርዛት

መ= የሴት ልጅ ግርዛት አሁን ባለው ሁኔታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከሚባሉት በመጀመሪያ ደረጃ የምናነሳው የሴት ልጅ ግርዛትን ነው:: አንድም የችግሩ ከባድነት አንድም ደሞ ሕብረተሰቡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው ግንዛቤ ትልቅ መሆኑን ተረድተናል አይደለም? ሴት ልጅ ግርዛት አሁን መሉ በመሉ ማለት ይቻላል እየተወገዘ ነው:: ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ሲባል እሺ ቶፊክ!

ተ= ሌላው አሁን ካለው ሁነታ ስንነሳ በሶሳይቲ ውስጥ ያለው ሁኔታ ነው ሌላው ደሞ ሴትን ዝቅ አድርጎ መገመት ነው::

መ= ስለዚህ ሴትን ልጅ ዝቅ አድርጎ መገመት በራሱ ጎጂ ልማድ ነው በሕብረተሰቡ በተዘዋዋሪ እነዚህ ጎጂ ልማዶች በሕብረተሰቡ ላይ ነው ጎጂ የሆኑት ስለዚህ ጎጂ ልማዶች ሌላ ሀሳብ ያለው::

ወደ ሁለተኛው እንሂድ? እሺ ጋብቻ ወደ አንቻቦ ከመሄዳችን በፊት ጋብቻ በተጋቢዎች ፈቃደኝነት ላይ ካልተመሰረተ ምን ችግር ይፈጥራል?

ተ= አሁን ባለው እድሜያችን ይችን ጥያቄ መመለስ አያቅተንም /ተነቃቁ ተማሪዎች / አዲስ ሀሳብ ይኖረናል ካያችሁት ከሰማችሁት በዚህ ጉዳይ ላይ ምንድ ነው የምትሉት? እሺ መስፍን!

ተ= አንድ ሴትየዋ ልታገባውና ሲጋቡ ሲያስቡ የነበረች ልጅ አንዱ የአንዱን ሀሳብ ሊረዳ ካልቻለ ከሱ ቀረቤታ ከሌላት ሀሳባቸውን የመለዋወጥና ዕድገት የማምጣት ሁኔታ ለማምጣት አይመችም::

መ= ስለዚህ ትዳሩ የተሳካ ላይሆን ይችላል

እሺ እዛጋ

ተ= አይስማሙም

መ= ለምን? አይሰማመም ብቻ መልስ አይሆንም:: ማስረጃ ያስፈልግሻል::

/ተማሪዎች ተንጫጩ/ እሽ! እሷናት ሀሳቡን ያቀረበችው እሷ ናት ሀሳቡን ማጠናከር ያለባት ሁለቱ ተጋቢዎች በፈቃደኝነት ካልተመሰረተ ሁለቱ ሰዎች አይስማሙም ለምን? በስርዓት መልሺልኝ ተነሽና

ተ= ፍቅር አይኖራቸውም

መ= ለምን አይኖራቸውም

ተ= ማለት ፍቃደኛ አልሆኑም

መ= ለምን? የፈለኩት አይስማሙምማ አንድ ልጅ ትንሽ ልጅ ይመልስልኛል::

የማይተዋወቁ ሰዎች ሰለሆኑ አይሰማሙም ይላል:: አንቺ በዚህ ደረጃ አይሰማሙም ሳይሆን ለምን እንደማይሰማሙ ምክንያቱን በግልፅ መናገር መቻል አለብሽ:: እሺ /ለአንድ ተማሪ እድል ሰጠ/

ተ= የማይስማሙበት ምክንያት በዚህ ቀደም ስለትዳር ሁኔታ ስለማያቁ የዛሬው ሁኔታ ምን ምን መሆን እንዳለበት ያው ምን ማድረግ እንዳለባቸው የዚህ ግንዛቤ ላይኖራቸው ስለሚችል በዚህ የተነሳ ነው::

መ= እሺ ምንድን ነው ማድረግ ያለባቸው?

ተ= ማለት ከአገር ደረጃ ቤተሰብ የአገር ምንጭ ነው ቤተሰብ ማለት አንድ መልካም አመለካከት ያለው እና የማይጣጣም ቤተሰብ በፈጠርን ቁጥር የማህበረሰቡ እዛ ቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠረው ማህበረሰብ ቤተሰብም የተበከለ አስተዳደግ ነው የሚኖረው ለምሳሌ ወንድ ልጅ ቢያድግ አባቱ በእናቱ ተናዶ ጠጪ ከሆነ ያ ልጅ ምን ሊሆን ይችላል? ሴት ልጅ ከሆነች እናት በዚህ በባል የምትደበደብ ከሆነ የሚደርስባት ጭቆና የምታደርግ ከሆነ ነገ የሚደርስባት ነገር ማሰብ ይከብዳል:: ማለት ሶሳይቲውን ምን ብለን የምንቀርጸው ቤተሰብ ነው የምንቀርጸው ስለዚህ::

መ= ስለዚህ ቤተሰብ ሲመሰረት በጥንቃቄ መሆን አለበት ጋብቻ የሚመሠርቱ ሰዎች ተግባብተው ተፈቃቅደው መሆን አለበት እንኳን ሳይግባቡ ሳይሰማሙ ቀርቶ ተግባብተውና ተዋደው

ከተጋቡ በኋላ ስንት መከራ ነገር አለ? አይደል እንዴ? ተዋደው የተጋቡ ባልና ሚስቶች በየጋብቻቸው መሀል በሚገጥማቸው ነገር አይጣሉም? ይጣላሉ:: ጭራሽ ምንም የማይተዋወቁት፣ የማይግባቡ ያልተፈቃቀዱ ሰዎች ትዳር ሲመሰርቱ ብዙ ችግሮች አሉ:: ቤተሰቡ ሊበተን ይችላል፤ በልጆች ላይ ራሱ ችግሮች አሉ ቤተሰብ ሊበተን ይችላል በልጆች ላይ ራሱ ችግር እየመጣ ነው ያለው::

ስለዚህ እዚህ ላይ እናውቃለንና ወደ ሶስተኛው እንምጣ ኧ. . . በስንኝ መልክ ነው የተቀመጠው

«የአያት የቅደመ አያት ኧ. . . በስንኝ መልክ ነው የተቀመጠው ጋብቻ ትመስርት አካሏ ሳይጠና» የሚለው ግጥም

ተቀባይነት ያለው ይመሰላችኋል ወይ? ለምን?

እስኪ አዲስ እጅ . . . አንተ እሺ እዛጋ

ተ= በኔ በኩል ሀሳብ ተቀባይነት የለውም ምክንያቱም አካሏ ሳይጠና ማለት ሳትደርስ ማለት ነው ስለዚህ

የራሷ ወጋቸውን ለማየት በፈለጉት ደረጃ ሊሆን ይችላል::

እሷ አላማዋ ደርሶ መጋባት እስከምትፈልግ ድረስ መቆየት አለባት ስለዚህ

መ= ስለዚህ ተቀባይነት የለውም! በጣም ነው የተከራከረችው በኃይለኛው! እንዲህ መከራከር መቻል አለባችሁ:: አካሏ ሳይጠና ሲል እኮ ራሱ መጀመሪያ ልጅቱ በአእምሮዋ እንኳ ይቀርና እንደዚህ አይነት ነገር ማድረግ. . . ከዚያ በኋላ የሚመጡትን ችግር ታቃላችሁ አይደል ! በተለያዩ ሚዲያዎች ይነገራል ሴት ልጅ አካሉ ሳይጠና ትዳር ስትመሰርት እሚደርስባት በጣም ብዙ አካላዊ ጉዳት አለ ስትወልድ እድል? የመሳሰሉት ችግሮች አሉ:: ለአንድ ሰው እድል ልስጥና ወደንባቡ እንሄዳለን::

ተ= የአያት የቅደመ አያት ወጋችን ነውና እና አንድ ግዴታ አሁን ልጅቱ ወግ ስለሆነ ብቻ ልታገባ ነው ማለት ነው ወግ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን እነሱ ለሚኖሩበት ሕብረተሰብ ታዛዥ ለመሆን ነው

መ= ትስማማላችሁ በዚህ ሀሳብ

ተ= አዎ / በጋራ /

መ= እኔም እስማማለሁ! እሺ አሁን ወደ ንባብ

እሺ

ተ= አልተስማማሁም / በጋራ/

መ= አልተስማማሁም? እኛ ሰምተናል:: ወይም ድምፅሽን ከፍ አድርጊ ማለት ነበረብህ:: እሺ እኔ ያለችውን ባጭር ልንገርህ የመጀመሪያው ያያት የቅድመ አያት ወጋችን ነውና ይላል:: የመጀመሪያው ስንኝ ወግ ስለሆነ ብቻ ወይም አያቶቻችን ሲያደርጉ ስለነበር ብቻ ዛሬ ይሄን ነገር ማድረግ የለብንም ዛሬ ወግ የሚለውን ለመልካም ነገር አስቀርተን ጋብቻ መመስረት

ያለባት በሰዎቹ በተጋቢዎቹ መፈቃቀድ ስለሆነ ያንን መሰረት አድርገን ነው ጋብቻ መመስረት ያለብን ወግ ስለሆነ ብቻ አይደለም ነው እሷ የገለጸችው።።

እሺ ወደ ምንባቡ እንሂድ

ርዕሱ አንቻቦ ነው የሚለው ወደ ርዕሱ ሲገባ ታሪኩን አስቀድማችሁ አንብባችሁት እንደሆነ ነው ስለዚህ እኔ ምንባቡን አነብላችኋለሁ።። ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች አሉ።። በነዛ ጥያቄዎች ላይ እየተወያየን የምንባቡን መልዕክት እናዳብራለን።።

አዳዲስ ቃላት ስታገኙ ማስታወሻ እየያዛችሁ ትሄዳላችሁ።።

እሺ እንጀምር?

ተ= አዎ /በጋራ/

መ= /ምንባብን ማንበብ ጀመረ፣ አነበቡ/

ተ= /ምንባቡን ከመምህር ጋር በመከታተል አዳመጡ/

መ= እናንተ ሰምታችሁታል! ምን አይነት ታሪክ ነው?

ተ= ትዝታ ነው

መ= እናንተ ስትሰሙት

ተ= በትረካ መልክ የቀረበ ነው

መ= በትረካ መልክ የቀረበ ታሪክ ነው

ይዘቱስ? እሺ አብዱ

ተ= የጋዘር ማህበረሰብ የአንድ ማህበረሰብ የጋብቻ ምን እንደሚመስል

መ= የአንድ ማህበረሰብ የጋብቻ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ምን እንደሆነ ለማሳየት የቀረበ ነው ቅድመ መጀመሪያ በመግቢያችን ላይ ስንነጋገር ስለ ጎጂ ልማዶች ስንነጋገር አንስተን ነበር! አይደል እንዴ? ከዚህ ጋር በተያያዘ ምን አንስታችሁ? ምንባብ ሳንጀምር ምን ተረዳችሁ? ሌሎቻችሁስ? እያነበባችሁ ነበር ሌላ ሌላ እሺ

ተ= አንድ ማህበረሰብ

መ= ድምፅህ አይሰማም

ተ. በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ስለሚካሄድ... የጋብቻ ሁኔታ ነው የአንቻቦ ታሪክ ነው

መ= አለቀ? እንዴ አላለቀም! ታሪኩ የአንቻቦ ታሪክ ነው አደል! ከዛ በኋላ እንዲህ ሆነ ታሪኩን ባጭሩ የሰማኸውን ንገረኝ

ተ= /ታሪኩን በአጭሩ ተናገር/

መ= እሺ በማጠናከር የሚናገር ታሪኩን ባጭሩ ቶፊክ ጀምሮታል ሊያገባ ነበር. . . የሚያገባት ልጅ በባሕሉ መሰረት ከንፈሯን መተልተል ነበረባት ከንፈሯን ተተለተለች ከዛ በኋላ ነው ታሪኩ አሁን የሰማነው ምንድን ነው? እኔ አብዱ ከፊት ስለሆኑ እነሱ ብቻ ናቸው እንዴ የሰሙት? ኋላ ያላችሁትስ እስኪ ንገሩኝ ምን ሆነ? ወይም በአንቻቦ ምን ተፈጠረ? ትህትና! አይሰማም?

ተ= አላገባም አለ

መ= አላገባም በማለቱ ከአባቱ ጋር ተጣላ። ከዛስ?

ተ= እዚህ ጋር አንድ ባሕል ጎጂ ልማድ ነው ጎጂ ልማድ ስንል የሴቱ ከንፈሯን ማስቆረጥ

መ= ከንፈሯን መተልተል

ተ= እና ጠቃሚነቱ ለዛ ሰዎች መጥፎ ጎኑን አስትምረን አስቀርተን

መ= እሺ ከምንባቡስ ምን ተማራችሁ? ወይም መልእክቱ ምን ይመስላችኋል ? ምን ለማድረግ አስባችሁኋላል ከዚህ በኋላ እሺ

ተ= ማለት አንቻቦ እንደሚገባኝ ከሆነ የሚጣለው ከአባቱ ጋር አይደለም ወግ ስርአት ከሚባለው ነገር ጋር እየተጣላ ነው ግን የአንቻቦ አባትና አጠቃላይ ጎሳው እየተጣሉ ያሉት ከአንቻቦ አመለካከት ጋር ነው እና የነሱን ግጭት ነው እንጂ የምናየው የሰዎችን ግጭት አይደለም የምናየው።

መ= ምንባቡ የቀረበው ቀድሞ የነበረውን ባህልና አሁን ያለውን ትውልድ የነበራቸውን ግጭት ነው እንጂ በትክክል ሁለት ሰዎች መጋጨታቸውን ለማሳየት አይደለም ስለዚህ ጎጂ ነው ብሎ . . . ልማድ ጎጂ ነው ብለን በአንድ ቀን አናጠፋውም አይደል? ጊዜ ይፈልጋል እና አንቻቦ በግሉ ምንድነው ያደረገው? ጋዘርን ከንፈሯን ሳትተለትል በፊት ይወዳት ነበር ወይም እንደዛ ነበር ውበቷን የሚያየው ከንፈሯን ስትተለተል አበላሻችኋት ለነገሩ በጎሳው አባላት ውበት ደግሞ ከንፈር መተልተል ነበር በዛ ባህል በከንፈሯ ሸክላ የምታደርግ ሴት ናት ውብ የምትባለው እስቲ አንድ ራሱ የሚደንቅ ነገር ነው ከንፈርን ያህል ነገር ተተርትሮ ሸክላ ተሸክሞ መንቀሳቀስ አስቡ ስለዚህ ጋዘር ያለው ይሄ አይስማማኝም አለ። በዚህ ጊዜ የገጠመው አደጋ በጣም ከባድ ነው? አይደል? ህይወቱን እስከማጣት! እዛ ጋር ያለውን የጎሳውን እምነት ተቀብሎ በጣም ጠንካራ እምነት ነው አባቱ ጥይት ተኩሶ ነው የሳተው ምን ለማስጠበቅ ነው? ወጋቸውን ባህላቸውን !

ተ= ባህላቸውን / በጋራ/

መ= ወጋቸውን ባህላቸውን ሰርዓት ለመጠበቅ ነው እና እሱ እንዳለወ በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለውን አንዱ ኃላቀር ነው የሚለውን ለማሳየት የቀረቡ ታሪክ ነው። እሺ ሌላ ተጨማሪ አለ?

ተ. አይሰማም /ጥያቄ ጠየቀ/

መ. እሺ ስንተኛውን ከንፈሯን ተተለተለች፣ ሸክላ በከንፈሯ ወጠረች፣ ቀለበትን ከንፈሯን በጭንቅላቱ አጠለቀች. . . እንዲዚህ ነው የሚሰነጠቀው /በምልክት አሳየ/ መቼም ሲሰነጠቅ ሰዎች ከሆኑ በኋላ ስናይ በኋላ ከተሰነጠቀ በኋላ ሸክላ ገብቶ ከፍ እያለ ከፍ እያለ ይሄድና ስጋውን ይወጥረዋል አፈጣጠራችን ራሱ አንዳንዴ አይገርማችሁም ይህን የሚያህል ሥጋ ብዙ ትይዛለች ማለት ነው? ስታስቡት ከዛ በኋላ ደግሞ ያ የተተለተለው ምን ይደረጋል፣ ያ ደግሞ

ትልቁ የውበት መግለጫ ነው። ያን ለማሳየት ነው ይሄ መግለጫው ይሄን የምነግራችሁ ከተለያዬ ሚዲያ ያየሁትን ነው እንደ ዋልታ ያሉ ባህላዊ ነገሮችን ያሳያሉ። እሺ!

ተ= /ተናገሩ/

መ= ዛሬ ደክሞአችኋል?

ተ= የጋዘር እናት ትንታግ ምላሷን

መ= ሌላ ጥያቄ ነው? ሀሳብ ጨረስን እሺ የጋዘር እናት ትንታግ ምላስ እንዴት እንደገረፈው እስቲ የሴትየዋን ስሜት ንገሩኝ እናንተ እስቲ ይሄን ምንባብ የጋዘርን እናት እንዴት ትስላችኋላችሁ? ጋዘርን ከንፈሯን ሊተለትሉ ሲዘጋጁ እሺ ደግሞ እንዴት ነው እስቲ ሴትየዋን ከዚህ ሀሳብ ጋር አያይዛችሁ ግለጿቸው።

ተ= የተናደዱ በጣም የተናደደች ሴት

መ= በጣም ኃይለኛ ከንዴትም ያለፈ ትንታግ ሲል እንደ ሰውየው ጥይት ከመተኮስ አይተናነስም በጣም ተናደዋል ሴትየዋ የአያት የቅድመ አያት ወጋችን ነውና! ሌላ ሀሳብ አለ?

ተ= እንዴት «እንደገረመመው»

መ= የጋዘር እናት ትንታግምላስ እንዴት እንደገረፈው እንዴት እንደረገመው ታወሰው

ተ= ትንታግ ምላሳቸው ሲል በጣም ተናዳና በቂጡ በአይናቸው ሲታዩ እንዴት እንደነበረ የብቀላ ስሜት ነው።

መ= የብቀላ ስሜት ነው ! እሺ

ተ= ትንታግ ሲል ተናጋሪ ናቸው በቃ በጣም ይናገራሉ

መ= ይናገራሉ! አስደንግጠውታል! ቀልቡን ገፈውታል! በኃይለኛ እንደዛ የሚናገሩ አሉ ንዴትም ቢሆን ሰዎች ከሚናደዱት ለየት ባለ ሁኔታ በኃይለኛ። ንግግራቸውን የሚያስደነግጥ ስዎች አሉ ሴትየዋ ደግሞ ተጨማሪ ባህላቸውን ወጋቸውን የሚነካ ነገር ስለተናገራቸው ተደናደው ነው እሺ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች አሉ?

ተ= ጮጮ ምንድነው?

መ = ጮጮ ምንድነው ? (ለሌሎች ተማሪዎች ጥያቄውን አቀረቡ)

ተ = የወተት ማስቀመጫ

መ = የወተት ማስቀመጫ ከምንድነው የሚሰራው?

ተ = ከቅል

መ = ከምንድው የሚሰራው እናንተ የከተማ ልጆች ናችሁ ጮጮ ከምንድነው የሚሰራው ብላችሁ ጠየቃችሁ እሷ ትነግራችኋለች

ተ = ወተት ነው የሚቀመጥበት ከሸክላ ነው የሚሰራ

መ = ያሳምሩታል ወተት ነው የሚቀመጥበት የወተት ዕቃ ነው ጮጮ

ተ = እንደቦታው ይለያያል አንዳንድ ቦታ ቅል ያደርጉታል ፣ አንዳንድ ቦታ ሽክላ ያደርጉታል ፣

መ = አዎ ቅል ያደርጉታል ፣ ሽክላ ያደርጉታል ራሱ ላይ በጌጥ ያስውቡታል እዚህ ጋር ምንድነው የሚለው ላምም ሆነ ፍየል አልበው ወተት ያስቀምጡበታል ሲል ከምንባቡ ከራሱ ሃሳብ እንረዳለን የወተት ዕቃ መሆኑን

ተ = እመር ብለው የሚለው

መ = እሺ እመር ይሄ የምንባቡ ወደ መጨረሻ ላይ ያለ ነው አባቱ ይሄን ሲሰሙ እመር ብለው በመነሳት በሁለቱ ሰዎች ጋብቻ ላይ ለመገኘት ሰዎች ተቀምጠዋል እንደምንባቡ እመር ብለው ሲል እንዴት ከእልህ ተስፈንጥረው በኃይል ትሰሏችኋላችሁ አትስሏቸውም? ለምሳሌ እናንተ እንደዚህ ቁጭ ብላችሁ አንዱ ከአንዱ ጋር ቃላት ትለዋወጣላችሁ ከዛ በኋላ አንዱ ቦግ ሲልበት ብድግ ይላል እመር ብሎ ተነሳ በኃይል ማለት ነው። ሌላ?

ተ = የገሪጥ

መ = የገሪጥ እስቲ አይኑን እንደሱ አድርጎ የሚያሳየኝ አንድ ሰው የገሪጥ እሚያያችሁ እንዴት ሲያያችሁ ነው።

ተ = መገላመጥ

መ = መገላመጥማ ሌላ ነው እስቲ በድርጊት የሚያሳየኝ

ተ = በድርጊት ለማሳየት ሞከረ

መ = እስቲ የገሪጥ አሳየኝ

ተ = (በድርጊት አሳየ)

መ = እሺ በጣም ተራ ሳይሆን የግልምጫ አይነት ውስጡ አይን አይን ብዙ ነገር ይናገራል ስንናደድም፣ ደስ ሲለንም፣ ሲከፋንም፣ የሆነ ነገር ስንፈልግም፣ አይናችን ላይ ያስታውቃል ሴትየዋ በንዴት በቁጣ ተራ ከሆነ አስተያየት ሌላ ኃይል ያለው አስተያየት በግልምጫ አይነት አይን በግልምጫ ሰው ያባርራል አይደል?

ተ = አዎ(በጋራ)

መ = የሰው አይን ተመልክታችሁ ልትበሉት የዘረጋችሁትን እጅ እንኳን አትሰበስቡም?

ተ = አዎ እንሰበስባለን(በጋራ)

መ = አይን መልዕክት አለው እንደዛ ማለት ነው። እሺ እነዚህ ጥያቄዎች የምንባቡን ሃሳብ መልሰን ለማዳበር ይጠቅሙናል። በቃል ነው የምንሰራው ጥያቄውን በቃል ነው የመጀመሪያው ጥያቄ የአንቻቦ ዕድሜ ስንት ነው?

ተ = 16 ነው(ተንጫጩ)

መ = እሺ

ተ = 26 ነው(ተንጫጩ)

መ = እሷ ያኔ 16 ዓመት ናት እሱ ደግሞ በ10 ዓመት ይበልጣታል 10 ዓመት ጨምረን 26 እንላለን በዛ ነው የምናኘው እሺ ጋዘር ከንፈሯን የተተለተለችው በስንት ዓመቷ ነው?

ተ = በ14 (በጋራ) 18 ፣ 16 (ተንጫጩ)

መ = በ14 ምንባቡን እኩል ነው ያነበብነው የተነበበው ምንባብ መሠረት አድርጋችሁ ታሪኩ ይሄ የሆነው በዚህ ጊዜ ነው

ተ = 16 ዓመቷ ነው ብሎ ግን የተተለተለችው ከሁለት ዓመት በፊት ነው

መ = ምክንያቱም አንቻቦ ያለፈ ታሪክ ነው እየነገረን ያለው አይደል አሁን ያነበባችሁትን ከነገሮች ጋር ማያያዝ ነው የደገምኩትም ይሄን ነው።ለሶስት ጉልቻ ልንበቃ ነው የሚለው ዐረፍተ ነገር ምንን ይገልጻል

ተ = (ተንጫጩ በጋራ)

መ = ለትዳር ልንበቃ ነው ትዳርን

ተ = ለሶስት ጉልቻ ልትበቃ ነው የሚለውን ጉልቻ ለምን ተመረጠ?

መ = ብዙ ፈሊጣዊ አባባሎች አሉ ብዙ ለምን እንዲህ ሆነ ብለን የማንጠይቃቸው ሶስት ጉልቻ የትዳር መግለጫ ነው። ጉልቻ ምንድነው?

ተ =የትዳር ምልክት ነው

መ =ጎጆ ብለን ስናስብ ጉልቻ ምናምን አብረው አሉ የሴት እቃዎች በአብዛኛው በዛ በኩል ነው ሀሳባችን ሴትየዋ ሶስት ጉልቻ ቤትዋን እሳት ታነዳለች ታማመቃለች ትዳር ይመሰረታል አይደል እንዴ ጉልቻ ለምን ተመረጠ ሌላ ነገር ነው ጉልቻ የትዳር ምልክት ነው። ለምሳሌ ሌላ አይነት አባባልም አለ የእርጉ ዝንብ ይባላል። የእርጉ ዝንብ ምንድን ነው?

እኮ አንድ ሳንፈልግ በንግግራችን መሃል ጥልቅ ሲል የርጉ ዝንብ ነው ለምን የውሃ ዝንብ አልተባለም። ለምን የወተት ዝንብ አልተባለም ብለን እንደመጠየቅ ነው። ግን ጉልቻ ዞሮ ዞሮ የትዳርን መመስረት የሚገልጽ ፈሊጣዊ አባባል ነው። ስለዚህ ምን ይባላል ትዳር ለመግለጽ እሺ ውሃ አጣጩ

ተ= የትዳር አቻዬ

መ= የትዳር አቻዬ ማለት ነው ልክ እንደነዚህ አባባሎች ናቸው። የአንቻንቦን አባት በፈንጠዝያ ያስፈነደቀው ነገር ምንድን ነው? ምንባቡን ማስታወስ ነው የሚጠበቅባችሁ። በጣም ተደስተው ነበር

ተ= ልጃቸውን ሊድሩ ስለሆነ

መ= ምክንያቱም የልጃቸው ሚስት ባህሏን የተከተለች ባህሉን የምታከብር ስለሆነ ልጃቸው ባህሉን የተከተለ ልጅ ስላገኘች ነው በጣም የተደሰቱበት እንደውም የአንቻቦ ትዳር መያዝ እኮ ልጃቸውን የበለጠ ደስታቸው የልጅታ ከንፈር መተልተል ነው። አይደል እንዴ ምክንያቱም ጥሎሹን በደስታ የሚከፍሉት ነው የናት ወግና የአባት ወግ የተባሉት ምንድን ናቸው? ለማስታወስ ሞክሩ መጀመሪያ የእናት ወግና የአባት ወግ የተባሉት ነገሮች እሺ (ለአንድ ተማሪ እድል ሰጡ) እሺ ምንባቡን እንደገና ተመልከቱት እስቲ መጽሐፉን ተመልከቱት ምንባቡ ላይ እዩት የእናት ወግ ናቸው የተባሉት የአባት ወግ ናቸው የተባሉት ምንድን ናቸው?

ተ= በፈርስ መታጠብ

መ= በፈርስ የሚታጠቡት ወንዱ ነው ሴቷ

ተ= ወንዱ (በጋራ) እጁን በፈርስ እንዲታጠብ ማገዝና

መ= ያባት ወግ ነው የተባለው አባት ወንድ ልጁ ትዳር ሲይዝ ነው ይህን ማድረግ እንደሚገባው

ተ= ባለማክበርና ባለመቀበል

መ= እሺ በቃን (ትምህርቱ ተጠናቀቀ)

አባሪ 1ፈ.

ክድ 06

ክፍለ ጊዜ 6ኛ

ለዓት 7:00-7:42

ቀን 7/9/99

መ= እሺ ይህንን ርዕስ አይታችሁታል መጽሓፋችሁን አውጡ! ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች ናቸው። የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት አብራሩ ይላል ማለት ምን ማለት ነው? ተዋናይ

ተ= አንድን ድርሰት ገጸባሕርይን ተላብሶ የሚሰራ

መ= አንድን ድርሰት ገጸ ባሕሪውን ተላብሶ የሚሰራ አንድን ድርሰት ገጸባህሪያትን ተላብሶ የሚሰራ ምን ይባላል ነው ያለው ?

ተ= ተዋናይ (በጋራ)

መ=ተዋናይ ያንድን ድርሰት ባህሪ ተላብሶ የሚሰራ ምን ይባላል ነው ያለው?

ተ= መድረክ

መ= በመድረክ ላይ (2) መድረክ ራሱ ምንድነው? ተላብሶ የሚሰራበት ቦታ ምን ይባላል

ተ= መድረክ

መ= በመድረክ ላይ (2) መድረክ ራሱ ምንድን ነው? እ! መድረክ!

ተ= የሚተወንበት ቦታው

መ= የሚተወንበት ቦታ (2) የሚተወንበት ቦታ ወይም አካባቢውን እና ተዋናዮች ካሉ ምን መኖር አለበት (2) ተመልካቾች መኖር አለባቸው። የሚተውኑበት ቦታ መድረክ ይባላል። ተውኔት? (2) ተውኔት ምን ማለት ነው?

ተ= ስራ

መ= ስራን ከንውንን የሚተውነው ድርሰቱ በአጠቃላይ ተውኔት ብለን እንጠራዋለን። የምታደንቋቸው ኮሜዲያን ተዋናዮች እነ ማን ናቸው?

ተ= ክበበው ገዳ

መ= ለምን ታደንቀዋለህ?

ተ= አነጋገሩና ካፉ የሚወጡ ቃላቶች የሚያስቁና የሚታዘንለት ልጅ ስለሆነ ደስ ይለኛል።

መ= የሚያስቅና የሚታዘንለት ልጅ ስለሆነ አደንቀዋለሁ ነው ያለው ሌላ!

ተ= ቻርሊ ቻፕሊን (ተማሪዎቹ ሳቁበት)

መ= በሀገራችን! ጥሩ ነው በሀገራችን! ተስፋዬ ጥሩ ነው

ተ= ተስፋዬ ካሣ

መ= እሺ ተስፋዬ ለምን አደነቅከው

ተ= በስራው

መ= ብዙ ስራዎችን ስለሰራ ታታሪ ስለሆነ አዝናኝና ትምህርት ሰጪ ስለሆነ ይበቃል ርዕሱን በማየት ስለምንባቡ ምን ትገምታላችሁ?

ይህንን ርዕስ በማየት ስለምንባቡ ምን ትገምታላችሁ (ሰሌዳው ላይ የተጻፈውን በማሳየት) (ተማሪዎችን ገሰጹ ጫጫታ ስለበዛቸው) ምንድ ነው የምትገምቱት?

ተ= ባህላዊ

መ= ባህላዊ የህክምና ዘዴ ይገምታል

ተ= በልማድ የሚሰራ

መ= በልማድ የሚሰራ የመርፌ አወጋግ ይገምታል

ተ= እውቅና የሌለው

መ= እውቀት የሌላው፣ ትምህርት የሌለው ክልምድ እንዲሁ መርፌን መወጋት ተምሮ የመጣ ወይም ተምሮ ማለት በልምድ መርፌ እንዴት እንደሚወጋ የሚያቅ ይህንን እንገምታለን።

ኧ ምንባቡን የሚያነብልኝ! ምንባብን ስታነቡ ግን ሁለት ገረመው አንድ ሰው ይሆናል!

ተ= ምንባቡ ለማንበብ እጃቸውን በማውጣት ተንጫጩ

መ= ገረመው በመሆን አንተ ታነባለህ (አንዱ) ተማሪ በመጠቆም) ገረመው ደረጃ እስከሚደርስ ድረስ ያለውን እስቲ!

ተ1= የመንደሩ መርፌ ወጊ.. .. (ማንበብ ጀመረ)

መ= ገረመው

ተ2= በሸተኞችን ዝም ካሰኘ በኋላ... (አነበበ)

መ= አይሰማም

ተ2= ማንበቡን ቀጠለ

መ= ቆይ ቀጥል

ተ3= ማንበብ ጀመረች

ተ4= በተከታታይ ... ማንበብ ጀመረ

መ= ድምፅ ትንሽ ጨምሪ. (የማንበብ ዕድሉን ለሌላ ተማሪ ሰጡ)

ተ= (እንደገና ማንበብ ጀመረ)

መ= ቢሰውር! ቢሰውር ሆኖ የሚያነብልን እሺ ቀጥል

ተ= (ማንበብ ቀጠለ) አንበብ እንደጨረሰ

መ= እሺ ፋንታሁን እንግዳ ከሚለው ተውኔት ነው የተወሰደው ከዚህ ምንባብ ውስጥ በቃል የሚመለሱ በቃል የሚመለሱ የማዛመድ ጥያቄዎች አሉ! እስቲ በምንባቡ መሠረት ተገቢ ፍቻቸውን ከለረድፍ እየመረጣችሁ መልሱ በቃል የሚመለስ ነው አንደኛው! ከለለ

ተ= ጋረደ ወይም ሸፈነ

መ= ጋረደ ወይም ሸፈነ እሺ ሁለተኛውስ ምን ይላል? ተስገበገበ

ተ= ተሻማ

መ= ተሻማ 3 ቁጥር አደብ ገዛ

ተ= ስርዓት ያዘ

መ= ስርዓት ያዘ መ. ቢጤ

ተ= መሰል

መ= ሸመተ (2)

ተ= ገዛ

መ= ገዛ ምንባቡን በሚመለከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ አሁን ያነበብነው በቂ ነው በቃል እንመልሰዋለን የገረመው አሮጌ ካፖርትና ቱታ መልበስ የቢሰውር ሲጋራ ማጨስ ምን ያስገነዝባችኋል? ምንድነው የሚያሳየን? እንድንገነዘብ የሚያደርገን? እ!

ተ= ኮንዲሽናቸውን ኸሮፌሽናል

መ= ያልሸውን ወደ አማርኛ ለውጪና ንገሪኝ

ተ= ታዋቂ

መ= ትክክለኛና ታዋቂ አለመሆናቸውን

ተ= ሲጋራ ማጨሱ ደግሞ የበለጠ ሌላ

መ= በሽተኞችን እያከመ በሽተኞችን እየረዳ ሲጋራ ማጨሱ ደግሞ የበለጠ ምን አይነት ለህክምና ትኩረት ያልሰጠ መሆኑን ያስገነዝበናል ማለት ነው። ሌላ የሚመልስ ሌላ!

ተ= ጥንቃቄ የሌለው መሆኑን

መ= ጥንቃቄ የሚባል ነገር የለም ለምሳሌ

ተ= ማለት ሲጋራ ያጨሳል ለበሽተኛም ለሱም ስርዓት የሌለው መሆኑን ያሳያል

መ= ስርዓት የሌለው አለባበሳቸውና ሲጋራ ማጨሱ ጥንቃቄ ያልተሟላ መሆኑን ያሳየናል ማለት ነው። ሁለተኛው ጥያቄ የተቀመጣችሁ ተነሱ የሚለው ትዕዛዝ ምንን ያመለክታል የተቀመጣችሁ በሙሉ ተነሱ አለ ገረመው ሲያዛቸው ምንን ነው የሚያመላክተን

ተ= አክብሩት

መ= ማንን ነው የሚያከብሩት

ተ= ሰውን (ሐኪሙን)

መ= ሐኪሙ ሲመጣ አክብሩት ምንድን ነው የሚያከብሩት የመንደሩ መርፌ ወጊ ትእዛዝ ካልተከበረ የሚሰጣቸው መድሐኒት በአግባቡ አይወስዱም ነው የሚለው። ሌላ

ተ= በሰፈር ውስጥ ያለው መርፌ ወጊ እሱ ብቻ ስለሆነ

መ= እነሱ እኮ አልተነሱለትም ታዘው ነው በሰፈር ውስጥ ያለውማ እሱ ብቻ ቢሆን ኖሮ ሰዎቹ እራሳቸው ናቸው አክብረው የሚነሱት አሁን እኮ አክብሩት የተባለው በትእዛዝ ነው።

ተ$_1$= በቀላል ገንዘብ ስለሚያክም ነው

ተ$_2$= ከበሽታቸው ስለሚያድናቸው

መ= ከበሽታቸው ስለሚያድናቸው ብለህ ትገምታለህ ትልቅ ሰው አድርገው እንዲያዩት ትልቅ እንዲሆንለት ገረመው ሰውየው ትልቅ ካልሆነና ካልተከበረ ምንድ ነው የሚሰጠው መድሐኒት የሚያደርገውን ድርጊት በሙሉ ያቀለበታል ስለዚህ ገረመው የግድ እንዲከበርና እንዲፈራ ማድረግ አለባቸው እሱ ገረመው እኮ ምንድ ነው ከዚህ እዚህ የሚል ቅስቀሳ የሚያከሂድና የሱ ጋሻ ጃገሬ ነው ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ካልተሟሉ ገንዘብ አያገኙም ሁለቱም ሁለተኛ በሽተኞች እነ ቢሰውርን በእልልታና በጭብጨባ የተቀበሉበት ምክንያት ምን ይሆናል ትላላችሁ መልሱ ምንድን ነው። በእልልታ በጭብጨባ የተቀበሉት

ተ= ብቸኛው መርፌ ወጊ ስለሆነ

መ= ብቸኛው መርፌ ወጊ እሱ ስለሆነ

ተ= ከበሬታ ስለ|ሚፈልግ

መ= ከበሬታ ስለሚፈልግ ይመስላል ሌላ? በሽተኛ እንዴት ነው? አንድ ነገር ሲያገኝ የዳነ የሚመስለው ለዚህ መምጣቱ አርፍዶ ነው የመጣው ቆይቶ ነው የመጣው አሁን ስለመጣላቸው ደስታ ያዛቸው ቶሎ ቶሎ መርፌያቸውን ተወግተው ወደ ስፍራቸው ለመሄድ ችኩለው ነው ሌላ ጥያቄ የመጀመሪያው በሽተኛ እንደገባ አይን አይኑን እያየን ቆሞ የነበረው ለምን ነበር ቢሰውርን አይን አይኑን ቆሞ እያየው ነበር ለምን እሺ ይላል

ተ= ሰግቶ

መ= ሰግቶ ሌላ? በሽታው ምንድን ነው ብሎ እንዲጠይቀው በሽታውን ሳይጠይቅ ነው ወደ መርፊ የሄደው በሽታው ምን እንደሆነ አልገለጸም እሱ አሁን ምናልባት ከዛ በፊት በሽታው ምን እንደሆነ ሊጠይቀኝ ነው ብሎ ነበር የቆመው (ሌላ ጥያቄ) አምስተኛው ጥያቄ ሚስት አለህ ተብሎ የተጠየቀው ሕመምተኛ እንዴታ ያውም የልጆች እናት በማለት የመለሰው ከምን የተነሳ ይመስላኂል?

ተ= ከሚስቱ ጋር ለወር ያህል ምን አለው

መ= ሚስት አለህ ሲል ምንድነው ያለው?

ተ= አዎ ለዛውም የልጆቼ እናት

መ= ስለዚህ ለወር ያህል ያለው ከዛ በኂላ ነው ለምን ጠየቀኝ ሚስት አለህ ብሎ እድሜ ትልቅ ነው ይድረኛል ብሎ አስቦ ይሆን እንዴ አይደለም ሚስት መኖሩን በከበሬታ ለመግለጽ ነው። አዎ እንዴታ ያውም የልጆቼ እናት እድሜ ትንሽ አይደለም አግብቻለሁ ብሎ ለመመለስ ነው የተናገረው ነው። (ትዕዛዙን አነበቡ) ይህም በቃል ነው የምንመልሰው አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ብዙን ጊዜ በቃል ስለሚመለሱ ገረመው ለረጅም ጊዜ ለሚያደርሰው ብሎ የጠየቀበት ምክንያት ምንድን ነው

$ተ_1$= "ለ" በማለት መለሰ

$ተ_2$= "መ" በማለት መለሰ

መ= ለምንድን ነው "ለ" ያልነው ብዙ ጊዜ ታውሮ የቆየ ሰው ነገ ይበራልሃል ቢሉት ዛሬ እንዴት አድሬ አለ የሚለውን ነው የተከተለው አባባላቸውን ለመንቀፍ ነው። ስለዚህ "ለ" ነው ትክክለኛ መልስ። ገረመውና ቢሰውር የሚመሳሰሉት በምንድን ነው

ተ= "መ"

መ= እስቲ ይህንን ምንባብ እኮ ሁለቱ ነው ያነበባችሁት

ተ=ሁለቱም ሲጋራ ያጨሳሉ

መ= ሁለቱም ሲጋራ ያጨሳሉ? ይሆናል? ገረመው ያጨሳል ብሎ ነው

ተ= ሁለቱም ካቦርት ለብሰዋል።

መ= ሁለቱም ካቦርት ለብሰዋል? እሱ የለበሰው ቱታ ነው

ተ= በመንጫጫት መለሱ

መ= ሁለቱም ሸበት ጣል ጣል አድርጓቸዋል። ህመምተኞች እሺ! አዳምጡ (2) እንደማመጥ ህመምተኞች በደንበኝነት መዝገብ ላይ የሚፃፉት ለምንድን ነው?

ተ= "ሐ"

መ= “ሐ” ለሕመማቸው መርፌ ሳያቋርጡ ሲወጉ ነው (ሌላ ጥያቄ አነበቡ)

ተ$_1$= “መ”

ተ$_2$= “ሐ”

መ= እሺ “መ” የምትሉ “መ” የሚለው ከአንድ በስተቀር መልሱ ነው ይላል አንዱ የቱ ነው?

ተ= “ሐ” “ሀ”

መ= ስለዚህ መልሱ የቱ ነው “መ” ነው እሺ ይሄ ከምንባብ የወጣ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ናቸው። ከናንተ ያልገባችሁ ጥያቄ ካለ ይህንን በድራማ መልክ ብትሰሩት ሌሎችም ንባቦች አትስሩ ማለት አይደለም መገደቤ አይደለም ድራማ ስትሰሩት ወደ ድራማ ብትለውጡት ትችላላችሁ የምንባቡን ጥያቄዎች አልቀዋል። ጥያቄ ካላችሁ በምንባብ ላይ የለም! (ትምህርቱን አጠቃለሉ)።

አባሪ 2

የንባብ ትምህርት ሲሰጥ መምህሩ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለመከታተል የተዘጋጀ የምልከታ መከታተያ ቅጽ (Checklist)

የመምህሩ መለያ ኮድ_____ ት/ቤት_____

ክፍለ ጊዜ _____ የትምህርቱ ርዕስ_____

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ _____ የግምገማ ጊዜ _____

መመሪያ፡- በዝርዝር የቀረቡት ሀሳቦች የተከናወኑ ከሆነ ይህን ምልክት"✓" በመጠቀም አመልክት/ች፡፡

ይዘት-የክፍል ውስጥ አቀራረብ	ተከናውኗል	አልተከናወነም	አስተያየት
1. ቅድመ ንባብ ተግባራት			
1.1 ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት አሳውቀዋል፡፡			
1.2.ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አድርገዋል፡፡			
1.3.ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን አሁን ከሚማሩት ንባብ ጋር እንዲያያይዙት አነቃቅተዋቸዋል፡፡			
1.4.የዕለቱን ርዕስ አስተዋውቀዋል፡፡			
1.5.በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል እንዲገምቱ አድርገዋል፡፡			
1.6.ተማሪዎችን በቡድን አደራጅተው እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡			
1.7.ተማሪዎች እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡			
1.8.ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ሰጥተዋል፡፡			
2.ጊዜ-ንባብ ተግባራት 2.1.ጥያቄዎችን በመስጠት የአሰሳ ንባብ እንዲያከናውኑ አድርገዋል፡፡			
2.2.መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ አድርገዋል፡፡			
2.3.ለንባቡ ጊዜ ወስነው (ደቂቃ ወስነው) ሰጥተዋል፡፡			
2.4.ለተጠየቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡			
2.5.ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽ መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙላት መልመጃዎችን እንዲሰሩ አድርገዋል፡፡			
2.6.ንባብን በገዘምታ ንባብ እንዲያነቡ አድርገዋል፡፡			
2.7.ከንባቡ ዝርዝር መረጃን እንዲያወጡ አድርገዋል፡፡			
2.8.ተማሪዎች የጽሁፉን አደረጃጀት መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል፡፡			
2.9.የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ አድርገዋል፡፡			
3.ድህረ-ንባብ ተግባራት 3.1.ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን መምህሩ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል፡፡			
3.2.ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት አድርገዋል፡፡			
3.3.ተማሪዎች ምንባቡ እንዲገመግሙ አድርገዋል፡፡			
3.4.ከንባብ ጋር ሌሎችን ክሂሎች ጋር በማጣመር ጥያቄ አቅርበዋል፡፡			

አባሪ 3

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ክፍል ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በጥቁር አንበሳ፣ ድላችን እና ቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

የዚህ ጥናት ዓላማ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በሚል ጥናት ለማካሄድ ነው።

ውድ መምህር! ጥናቱ የታለመለትን ግብ በትክክል ሊመታ የሚችለው ትክክለኛውን መረጃ ከእርሰዎ ማገኘት ሲቻል በመሆኑ ለእያንዳንዱ መጠይቅ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጡኝ እጠይቃለሁ።ይህን መጠይቅ ለመሙላት ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለምታደርጉልኝ ትብብር ሁሉ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ። በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያሰፈልግም።

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>1.አጠቃላይ መረጃ</u>

1.1 የምታስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም _____

1.2 የምታስተምሩበት የክፍል ደረጃ _____

1.3 ጸታ_____

1.4 ዕድሜ_____

1.5 የትምህርት ደረጃ _____

1.6 የተመረቁበት የትምህርት አይነት

ሀ. ዋና ትምህርት_____

ለ. ንዑስ ትምህርት _____

1.7 የአገልግሎት ዘመን _____

ADDIS ABABA UNIVERSITY ALS LIBRARY

<u>ክፍል ሁለት</u>

2. <u>የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አጠቃላይ መረጃን ይመለከታል።</u>

መመሪያ፡- ከዚህ ቀጥሎ ለተሰጡት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች የሚስማሙበትን ሀሳብን ፊደሉን በመምረጥ በማክበብ መልሱ።

2.1 በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ይሰጣል?

ሀ.አዎ ይሰጣል ለ. አይሰጥም

2.2. ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ፍላጎታቸው ምን ያህል ነው?

ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ.ከፍተኛ ሐ. መጠነኛ መ. ዝቅተኛ

2.3 ለጥያቄ ቁጥር 2.2 የሰጡት መልስ "መ" ከሆነ ምክንያቱ ምን ይሆናል ብለው ይገምታሉ?

_____::

2.4. የአማርኛ ቋንቋ ንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ጽሑፍ ምንጭ የትኛው ነው? ከአንድ በላይ መምረጥ ይቻላል::

ሀ. የመማሪያ መጽሐፍ ለ. በመጽሔት የሚታተሙ ወቅታዊ ጽሑፎች

ሐ. ጋዜጣ መ. የራስን ጽሑፍ በማዘጋጀት

2.5. የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ ከመማሪያ መጽሐፉ መልመጃ ውጭ የራስዎን ተጨማሪ ጥያቄዎች ያዘጋጃሉ::

ሀ. ዘወትር አዘጋጃለሁ ለ. አብዛኛውን ጊዜ አዘጋጃለሁ

ሐ. አልፎ አልፎ አዘጋጃለሁ መ.ፈፅሞ አላዘጋጅም

2.6. የንባብ ትምህርት ሲሰጡ ለየትኞቹ የንባብ ንዑሳን ክሂሎች ትኩረት ይሰጣሉ? በቅደም ተከተል ዘርዝሯቸው::

_____ _____

_____ _____

_____ _____

_____ _____

_____ _____

_____ _____

ክፍል ሶስት

3. ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሀሳቦች በክፍል ውስጥ የንባባ ትምህርት ሲሰጡ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የሚመለከቱ ናቸው:: ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ሲሰጡ በየትኛው ደረጃ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ይህን ምልክት /✓/ በመጠቀም አመልክቱ::

የትምህርቱ አቀራረብ	ሀ	ለ	ሐ	መ
	ዘወትር እጠቀማለሁ	አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ	አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ	ፈፅሞ አልጠቀምም
1. ቅድመ ንባብ ተግባራት 1.1.ተማሪዎች ንባብ የሚያነቡበትን ምክንያት ያሳውቃሉ::				
1.2.ተማሪዎች የንባብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው:: ጥረት ያደርጋሉ::				
1.3. የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ስተዋውቃሉ::				

የትምህርቱ አቀራረብ	ሀ	ለ	ሐ	መ
	ዘወትር እጠቀማለሁ	አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ	አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ	ፈፅሞ አልጠቀምም
1.4.የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ከሚማሩት ጋር በማያያዝ እንዲገምቱ ያደርጋሉ።				
1.5.ተማሪዎችን በቡድን ያደራጃሉ።				
1.6. ተማሪዎች እንዲወያዩ ያደርጋሉ።				
1.7.ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ።				
2. ጊዜ-ንባብ ተግባራት 2.1.ተማሪዎችን ተራ በተራ በማስነሳት ያስነብባሉ።				
2.2 ጥያቄዎችን በመስጠት (ከ2-3) የአሰሳ ወይም የገረፍታ ንባብ እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ።				
2.3 ራስዎ ንባቡን በማንበብ ተማሪዎች እንዲያዳምጡ ያደርጋሉ።				
2.4.ለንባቡ ደቂቃ ወስነው በመስጠት ተማሪዎች እንዲያነቡ ያደርጋሉ።				
2.5. ተማሪዎች ለሚጠይቁት ጥያቄ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ።				
2.6.ስዕልን ማገናዘብ ወይም ቅጽን መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን ተማሪዎች እንዲሰሩ ያደርጋሉ።				
2.7. ተማሪዎች ንባቡን በገለምታ ንባብ እንዲያነቡ ያደርጋሉ።				
2.8. ተማሪዎች ከንባቡ ዝርዝር መረጃን				

እንዲያወጡ ያደርጋሉ።				
2.9.ተማሪዎች የጽሑፉን አደረጃጀት እንዲናገሩ ያደርጋሉ።				
2.10 ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንዲገምቱ ያደርጋሉ።				
3. ድህረ-ንባብ ተግባራት 3.1.ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ሃሳብ መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጠዋል።				
3.2. ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት ያደርጋሉ				
3.3. ተማሪዎች ምንባቡን እንዲገመግሙ (ጥሩ መሆኑንመስማማታቸውን፣ አለመስማማታቸውን) ያደርጋሉ።				
3.4. የንባብን ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ያቀርባሉ።				

<u>ክፍል አራት፡-</u> ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

4.1. በንባብ ትምህርት ጊዜ ያጋጠመዎት ችግር ካለ ይግለጹ።

_____

_____

_____ ::

4.2. ለችግሩ መፍትሔ ነው የሚሉት ሀሳብ ካለ ይግለጹ።

_____

_____

_____ ::

4.3. በአጠቃላይ ስለ ንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ የሚሰጡት አስተያየት ካለ ይግለጹ።

_____

_____

_____ ::

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
ሚያዝያ 1999

አባሪ አራት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሁፍ ክፍል

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በጥቁር አንበሳ፣ ድላችን እና ቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

የዚህ ጥናት ዓላማ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በሚል ጥናት ለማካሄድ ነው።

ውድ ተማሪዎች! ጥናቱ የታለመለትን ግብ በትክክል ሊመታ የሚችለው ትክክለኛውን መረጃ ከእናንተ ማግኘት ሲቻል በመሆኑ ለእያንዳንዱ መጠይቅ ትክክለኛውን መረጃ እንድትሰጡ እየጠየቅሁ ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ለምታደርጉልኝ ትብብር ሁሉ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁኝ።

በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም።

<u>ክፍል አንድ</u>

1.አጠቃላይ መረጃ

1.1 የምትማርበት/ሪበት ትምህርት ቤት ስም _____

1.2 የምትማረበት/ሪበት የክፍል ደረጃ _____

1.3 ጾታ_____

1.4 ዕድሜ_____

1.5. አፍ የፈታህበት/ሽበት ቋንቋ _____

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>2. ይህ ክፍል አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት መረጃን ይመለከታል።</u>

<u>መመሪያ</u>፡- ከዚህ ቀጥሎ ለተሰጡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ፊደሉን በመምረጥ በመክበብ መልሱ።

2.1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ይሰጣል?

ሀ.አዎ ይሰጣል ለ. አይሰጥም

2.2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የንባብ ትምህርት ለማስተማር የሚጠቀሙበት የጽሑፍ ምንጭ የትኛው ነው? (ከአንድ በላይ መልስ መስጠት ይቻላል)።

ሀ. መማሪያ መጽሐፍ

ለ. በመጽሔት ላይ የሚወጡ ወቅታዊ ፅሁፎች

ሐ. ጋዜጣ

መ. የራሳቸውን ጽሑፍ በማዘጋጀት

2.3. በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለመታተል ያለህ/ሽ ፍላጎት ምን ያህል ነው?

ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ.ከፍተኛ ሐ. መጠነኛ መ. ዝቅተኛ

2.4. ለጥያቄ ቁጥር 2.3. የሰጠኸው/ሸው መልስ መ ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው?በአጭሩ ጻፍ/ፊ።

ክፍል ሶስት

3. ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሀሳቦች የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባብን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ያለውን ሁኔታ ይመለከታል። ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት ሲሰጡ በየትኛው ደረጃ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ይህን ምልክት /✓/ በመጠቀም አመልክቱ።

የትምህርቱ አቀራረብ	ሀ ዘወትር ይጠቀማሉ	ለ አብዛኛውን ጊዜ ይጠቀማሉ	ሐ አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ	መ ፈፅሞ አይጠቀሙም
1. ቅድመ ንባብ ተግባራት 1.1.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባብን የምትማሩበትን ዓላማ ያሳውቋችኋል።				
1.2.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ንባብን የማንበብ ተነሳሽነት እንዲያድርባችሁ ያነቃቋችኋል።				
1.3.የዕለቱን ምንባብ ርዕስ ያስተዋውቃሉ።				
1.4.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በርዕሱ ዙሪያ ምን ሊነገር እንደሚችል እንድትገምቱ ያደርጋሉ።				
1.5.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከንባብ ትምህርት በፊት በቡድን (በጥንድ)እንድትወያዩ ያደርጋሉ፡				
1.6.ለቁልፍ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ።				
2.1.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የንባብ አይነቶችን (የአሰሳ፣ግርፍ) እንደአስፈላጊነታቸው እንድትቀጠሙ ያደርጋሉ።				
2.2.ምንባቡን ስታከናውኑ ደቂቃ ወስነው ይሰጣሉ።				
2.3.ስዕል ማገናዘብ ወይም ቅጽ መሙላት ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን በሰንጠረዥ መሙላት የመሳሰሉ መልመጃዎችን እንድትሰሩ ያደርጋሉ።				
2.4.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ በዝምታ ንባብ እንድታከናውኑ ያደርጋሉ።				
2.5.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ከንባቡ ዝርዝር መረጃዎችን ለይቶ ማውጣት ጥያቄ ያቀርባሉ።				
2.6.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የጽሑፉን አደረጃጀት እንድትናገሩ ያደርጋሉ።				

2.7.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የቃላትን ፍቺ ከአውድ አንጻር እንድትገምቱ ያደርጋሉ።				
2.8.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ በመስጠት ያስተካክላሉ።				
3.1.ከንባብ በኋላ አጠቃላይ የንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ መምህራችሁ ጥያቄ ያቀርባሉ።				
3.2.ተማሪዎች ምንባቡን ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያይዙት ያደርጋሉ።				
3.3.ምንባቡን እንድትገመግሙ (ጥሩ መሆኑን፣ መስማማት አለመስማማታችሁን) ያደርጋሉ።				
3.4.መምህራችሁ የንባብን ትምህርት ከጽህፈት፣ ከንግግር ከማዳመጥ ጋር በማያያዝ እንድትማሩ ያደርጋሉ።				

ክፍል አራት፡- ከዚህ ቀጥሎ ላሉት ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ ስጥ/ጭ።

4.1. በንባብ ትምህርት ጊዜ ያጋጠመህ/ሽ ችግር ካለ በአጭሩ ግለጽ/ጭ።

_____

_____

_____ ።

4.2. በአጠቃላይ የክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ንባብ አቀራረብ የምትሰጠው /ጭው/ አስተያየት ካለ በአጭሩ ጻፍ/ፊ።

_____

_____

_____ ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሚያዝያ 1999

አባሪ 5

ለቃለ መጠይቅ (1) የተዘጋጁ ጥያቄዎች

ለ9ኛ ክፍል መምህራን የቀረበ

1.በትምህርት ስልጠና ጊዜ ስለ ክሂሎች (የንባብ ክሂል) ማስተማሪያ ዘዴ በበቂ ሁኔታ ስልጠና አግኝቻለሁ ብለው ያስባሉ?

2. በስልጠና ጊዜ ያገኙትን ትምህርት ተግባር ላይ ለማዋል ችለዋል? ካልቻሉ ችግሩ ምንድን ነው?

3. የንባብ ትምህርት ሲያስተምሩ አዘውትረው የሚጠቀሙት የትኞቹን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ነው?

4. በንባብ ትምህርት ጊዜ ለማስተማር ቀለል ያሉ የሚሏቸው ንዑሳን የንባብ ክሂሎች የትኞቹ ናቸው?

5. የተማሪዎቹ ንባብን የመማር ፍላጎት በመምህሩ ጥረትና አቀራረብ ይወሰናሉ ብለው ያስባሉ?

6. ከሌላ የስራ ባልደረባዎ ጋር ስለትምህርቱ አሰጣጥ ለመወያየት ፈቃደኛ ነዎት? አዳዲስ አመለካከቶችን ለመቀበልስ ፈቃደኛ ነዎት?

ለቃለ መጠይቅ (2) የተዘጋጁ ጥያቄዎች

ለአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ኃላፊዎች

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርቱ አሰጣጥ ላይ የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ በክፍለ ትምህርቱ የሚደረገው አነሳሽነት ምን ያህል ነው? የመምህራኑስ ፍቃደኝነት አለ?

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል የሚደርጉት ጥረት ካለ በክፍለ ትምህርቱ ምን ያህል ድጋፍ ያገኛል?

3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጎልቶ የሚታይ ችግር ካለ ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት የተደረገው ጥረት ምን ያህል ነው? መምህራን ያላቸው ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸው የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ መሆኑና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን የመረጃ ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም መዲና ዳኜ

ፊርማ

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የማስረከቢያ ቀን ኅዳር ፰ ፲፱፻፱ ዓ.ም

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY